# ትምህርተ ክርስትና

(የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያን
እምነትና ትምህርት ፡)

ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ሊማረውና ሊያስተምረው
የሚገባ ፣ በተለይም ለሰንበት ትምህርት ቤት መማ
ሪያና ማስተማሪያ እንዲሆን

ከሊቀ ሥልጣናት
ሀብተ ማርያም ወርቅነህ
ተዘጋጀ ።

አ. አ. ፲፱፻፷፱ ዓ/ ም

ፀትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org

በሙሉም ሆነ፣ በከፊል መልሶ ማሳተም
መብቱ የአዘጋጁ ብቻ ነው ።

# ማውጫ ።


| ተራ ቁ. | ርእስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | መቅድም | ፩—፮ |
| ፪ | መግቢያ | ፯—፲ |
| ፫ | ዐቢይ ክፍል ፩ ትምህርተ ክርስትና | |
| | ክፍል ፩ የእምነት አንቀጽ | ፲፩—፲፬ |
| ፬ | ክፍል ፪ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን | ፲፬—፳ |
| ፭ | ክፍል ፫ የእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት | ፳—፴፪ |
| ፮ | ክፍል ፬ ስለ ጸሎት | ፴፪—፶፩ |
| ፯ | ክፍል ፭ ስለጾምና ምጽዋት | ፶፩—፶፫ |
| ፰ | ክፍል ፮ ስለ በዓላት | ፶፫—፶፭ |
| ፱ | ዐቢይ ክፍል ፪ የቅዱስ መጽሐፍ ጥናት | |
| | መቅድም | ፶፮—፶፯ |
| ፲ | ምዕራፍ ፩ ቅዱስ መጽሐፍ | ፶፰ |
| ፲፩ | ምዕራፍ ፪ ቅዱስ መጽሐፍ የአምላክ ስጦታ መሆኑ | ፶፱—፷ |
| ፲፪ | ምዕራፍ ፫ ቅዱስ መጽሐፍ እስትንፋሰ እግዚአብሔር መሆኑ | ፷—፷፪ |


www.ethiopianorthodox.org

## ማ ው ጫ


| ተራ ቊ. | ር እ ስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፲፫ | ምዕራፍ ፬ | |
| | የቅዱስ መጽሐፍ ቊጥርና ተራ | ፳፪ |
| ፲፬ | ምዕራፍ ፭ ቀኖና ቅዱስ መጽሐፍ | ፳፪—፳፫ |
| ፲፭ | ምዕራፍ ፮ የሁለቱ ኪዳናት ግንኙነት | ፳፫—፳፭ |
| ፲፮ | ሀ/ የብሉይ ኪዳን ክፍል | |
| | መቅድም | ፳፮—፳፯ |
| ፲፯ | ምዕራፍ ፯ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት | ፳፯—፳፱ |
| ፲፰ | ምዕራፍ ፰ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አከፋፈል | ፳፱-፷፯ |
| ፲፱ | ለ/ የሐዲስ ኪዳን ክፍል | |
| | መቅድም | ፷፰-፷፱ |
| ፳ | ምዕራፍ ፩ ወንጌል (ኢቫንጌልዮን) | ፷፱-፸፩ |
| ፳፩ | ምዕራፍ ፪ የወንጌል ጸሐፍት | ፸፩-፸፫ |
| ፳፪ | ምዕራፍ ፫ የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል | ፸፫-፸፯ |
| ፳፫ | ምዕራፍ ፬ የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል | ፸፯-፸፱ |
| ፳፬ | ምዕራፍ ፭ የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል | ፸፱-፹፩ |
| ፳፭ | ምዕራፍ ፮ የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል | ፹፩—፹፬ |
| ፳፮ | ምዕራፍ ፯ የሐዋርያት ሥራ | ፹፬—፹፭ |


## ማ ው ጫ


| ተራ ቊ. | ር እ ስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፳፯ | ምዕራፍ ፰ መልእክታት | ፹፭—፺፯ |
| ፳፰ | ምዕራፍ ፱ ራእየ ዮሐንስ | ፺፯-፺፰ |
| ፳፱ | ዐቢይ ክፍል ፫ የቤተ ክር/ ታሪክ | |
| | መቅድም | ፺፱-፻፪ |
| ፴ | ምዕራፍ ፩ | |
| | የፍልስጥኤም ጂኦግራፊ በአጭሩ | ፻፩-፻፬ |
| ፴፩ | ምዕራፍ ፪ | |
| | በፍልስጥኤም ምድር ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦችና አስተዳደራቸው | ፻፬-፻፲፮ |
| ፴፪ | ምዕራፍ ፫ | |
| | የዓለም ሃይማኖትና ሥነ ምግባር | ፻፲፮-፻፲፰ |
| ፴፫ | ምዕራፍ ፬ | |
| | የእስራኤል እምነትና ማኅበራዊ ኑሮ | ፻፲፰-፻፳፩ |
| ፴፬ | ምዕራፍ ፭ | |
| | የመሲሕ መምጣት ተስፋ | |
| | ክፍል ፩ የዓለም ድኅነት | ፻፳፩ |
| ፴፭ | ምዕራፍ ፩ የጌታችን የኢየሱስ ልደት | ፻፳፪-፻፳፭ |
| ፴፮ | ምዕራፍ ፪ የክርስቶስ | |
| | የሕፃንነቱ ጊዜ | ፻፳፭-፻፳፮ |
| ፴፯ | ምዕራፍ ፫ የክርስቶስ ጥምቀት | ፻፳፯-፻፳፱ |


www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ


| ተራ ቍ. | ርእስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፴፰ | ምዕራፍ ፲፩ የክርስቶስ የይፋ ሥራ | ፻፲፱-፻፳፯ |
| ፴፱ | ምዕራፍ ፲፪ | |
| | የክርስቶስ ንጉሥነት በመስቀል | ፻፳፯-፻፴ |
| ፵ | ምዕራፍ ፲፫ የክርስቶስ ትንሣኤ | ፻፴-፻፴፪ |
| ፵፩ | ክፍል ፪ የቤተ ክርስቲያን መሠረት | |
| | ምዕራፍ ፩ ርደተ መንፈስ ቅዱስ | ፻፴፪-፻፴፭ |
| ፵፪ | ምዕራፍ ፪ የሐዋርያት ተአምራት | ፻፴፭-፻፴፱ |
| ፵፫ | ምዕራፍ ፫ | |
| | የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ኑሮ | ፻፴፱-፻፵፩ |
| ፵፬ | ምዕራፍ ፬ የ፯ቱ ዲያቆናት ምርጫ | ፻፵፩-፻፵፬ |
| ፵፭ | ምዕራፍ ፭ | |
| | የዲያቆኑ ፊልጶስ ወንጌላዊ ሥራ | ፻፵፬-፻፵፯ |
| ፵፮ | ምዕራፍ ፮ | |
| | የሐዋርያት ለስብከት ሥራ መበተን | ፻፵፯-፻፶፩ |
| ፵፯ | ምዕራፍ ፯ | |
| | የቅዱስ ጳውሎስ መጠራት | |
| ፵፰ | ምዕራፍ ፰ ልዩ ልዩ ደቀ መዛሙርት | ፻፶፩-፻፶፫ |
| ፵፱ | ምዕራፍ ፱ የሴቶች አገልግሎት | ፻፶፫-፻፶፱ |
| | በቤተ ክርስቲያን | ፻፶፱-፻፷፩ |
| ፶ | ምዕራፍ ፲ | |
| | የክርስትናው በዓለም መስፋፋት | ፻፷፩-፻፷፫ |


# መቅድም

ልዑል እግዚአብሔር ሀልውና፥ ስለፈጣሪነቱና ስለ መግቦቱ ማወቅ ፣ እንደአርሱነቱም ማመንና ማምለክ ፣ ለእርሱም የሚገባ ምስጋና ማቅረብ ፣ሕጉንም ፀሚገባ መጠበቅ ለሰው ልጅ ሁሉ የግዴታ ተግባሩ ነው ፤ በተለይ ግን የኢየሱስን አዳኝነት የምናምንና የተቀበልን ክርስቲያኖች ሁሉ ክርስቶስ በአስተማረው ትምህርት ጸንተን መንፈሱም የገለጠልንን ያህል ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ለሌላውም ማሳወቅ ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው ።

ማንኛውም ምእመን ስለ ራሱ እምነት ጠንቅቆ ካላወቀ ለሌላውም ካላስረዳ የክርስቶስ ተከታይ ነኝ የሚለው በአፍ ብቻ እንጂ የጸና እምነት የለውም ። ይኸም ከሆነ እንኳን ለሌላ ሊተርፍ እርሱንም ያስጋዋል ፤ ማለት የሌላ ምርኮኛ ይሆናል ።

እንግዲህ በዕድሜ በአእምሮም ሕፃን የሆነ ሁሉ የራሱ ሃይማኖት የትኛው እንደሆነ ፣ ምን ማለትም እንደሆነ አስቀድሞ ለይቶ ማጥናት ማወቅም ስላለበት ለዚህ መማሪያ ትሆናለች በማለት ይኸች መጽሐፍ ተዘጋጀች ።

ከዚህም ጋር ወላጅ የሆኑ ሁሉ አስቀድመው ለራሳቸው፥ ቀጥሎም ለልጆቻቸው፥ እንዲሁም የክርስትና አባትና እናት የሆኑ ሁሉ የመንፈስ ልጆቻ



www.ethiopianorthodox.org

ቸውን እንዲያስተምሩባት ፣ ወደ መንፈሳዊውም ዓለም እንዲመሩባት፣በተለይም የሰንበት ትምህርት ቤት መምህራን አጠቃላይ ትምህርት እንዲሰጡባት በማለት አጠቃላይ ክርስቲያናዊ እምነት፣ክርስቲያናዊም ሥርዓት ተጠቃሎ ይገኝባት ዘንድ የተዘጋጀች መጽሐፍ ናት ።

ይኸችን መጽሐፍ አንድ ክርስቲያን ያጠናት እንደሆነ በአንድ በኩል የራሱን እምነት በሚገባ ይጠብቅባታል ፤ ይመሰክርባታል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች ይተርፍባታል ፤ ሌሎችንም ያስተምርባታል ።

እንግዲህ ሁሉንም በቃል ለማጥናትና ለመያዝ በሚያስችል መልክ የተዘጋጀች መጽሐፍ ስለሆነች በትምሮ ማስተማር እንድንጠቀምባት አስገነዝባለሁ ።

ይህች መጽሐፍ ለመጀመሪያ ደረጃ ልመነሻ የተዘጋጀች ስለሆነ ሌላው በደረጃው ከፍ ስለሚል ከዚሁ አብሮ ለመሄድ እንዲችል ይኸችን በጥንቃቄ መያዝና ማጥናት አሁንም የመጀመሪያ ደረጃ ነው።

የአምልኮት ነገር እንደ ፪ኛ ነገር የሚታይ ባለመሆኑ ሁላችንም ለሃይማኖታችንና ለአምልኮታችን ቅድሚያ መስጠት አለብን ፤ እንግዲያውስ እስኪ ወደ ውስጥ ገባ ብለን እንመልከታት ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ

አዲስ አበባ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.



# መግቢያ

አንድ ክርስቲያን እንዴት እንደሚያምን ፣ በምን እንደሚያምን ፣ የራሱን እምነት ከመነሻው እስከ መድረሻው ለይቶ ማወቅ ፣ ያንንም መጠበቅ ፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ደግሞ ያንኑ መመስከር ፣ መናገር ፣ (መናዘዝ) ገልጦም ማስረዳት አለበት ።

አንድ የማያምን ወይም መንፈሱ ያልረጋ ሁሉም ጨለማ የሆነበት ሰው ልማወቅ ወይም ለመፈተን ብሎ እውነተኛውን ሃይማኖት ሲጠይቀው አፍሮ ፣ ፈርቶ ዝም ሊል ከቶ አይገባም ፤ እንዲህ የሆነ እንደሆነ ገና እምነት የሌለው በምንም የማያምን መስሎ ይታያል ። ስለዚህ እንደዚህ ያለ አጋጣሚ በገጠመው ጊዜ ስለራሱ ሃይማኖት፣ስለ እግዚአብሔር ሀልዎት ሰፋ አድርጎ ሊመልስልት ሊመሰክርም ይገባል ። እንዲህ ያደረገ እንደሆነ ፈታኙ አፍሮ ይመለሳል ፤ ጠያቂው የማያምን እንደሆነ ወደ ሃይማኖት ይስበዋል ።

እንግዲህ መጽሐፍዋ ለዚህ እንድትስማማ ፣ በቃልም ለማጥናት እንዲቻል በማለት በአጭር ፀረፍተ ነገር ምሥጢሩ እንዳይረቅ በኅላ ማስረጃ የተደገፈ ፣ አርእስቶችም ሳይበዙ በማጠቃለል የተዘጋጀች ስለሆነ ፣ አንባቢዎች ሁሉ እንዲረዱትና በእነርሱ አገላለጥ ለማስረዳት በሚችሉበት መልክ ያጥኑት ።



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ መጽሐፉን የመጀመሪያውን በ፱ ክፍሎች ከፋፍየለሁ ይኸውም ፤

፩/ ሀልዎተ እግዚአብሔር ፤ ይኸም ክፍል የሚያስረዳው የሁሉ መገኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሀልዎትና ማመን እንዳለበትና አምልኮት ማቅረብ ግዴታ መሆኑን የሚገልጥ ነው ።

፪/ የእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት ፤ ይኸም ክፍል እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ እንደ መሆኑ ንጉሠ ነገሥት ነው ፤ ስለዚህ ሕገ መንግሥት አለውና ያን ማወቅ መጠበቅም ተገቢ መሆኑን ያስረዳል ።

፫/ ስለ ጸሎት ፤ እግዚአብሔር ሁሉን ሰጭ መሆኑን አምኖ ልመና ፥ ምልጃ ወደ እርሱ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ፥ እንዲሁም የምስጋና አምላክ እንደመሆኑ አምልኮት ፥ ምስጋና ማቅረብ ተገቢ ስለ መሆኑ ።

፬/ ጸሎተ ቅዳሴ ፤ ይኸውም ማንኛውም ምእመን በቤተ ክርስቲያን በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ መገኘት የምሥጢረ ቍርባንም ተካፋይ መሆን እንደሚገባ የሚያስረዳ ነው ።

፭/ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ፤ አንድ ምእመን የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ተካፋይ ይሆን ዘንድ የምሥጢራትን ስማቸውን ዓይነታቸውን ፥ ማወቅ ፥ እንዴት እንደሚፈጸሙ አውቆ ተሳታፊ ለመሆን የሚችልበትን መንገድ ለመቀየስ እንዲችል ለማድረግ ፤



፮/ ስለ ክብረ ቅዱሳን ፤ ቅዱስ የሚባለው ለምን እንደሆነ ፥ ማን ቅዱስ እንደሆነ ፥ ቅድስና ለአርአያ የሚሰጥ መሆኑን ገልጦ ለማሳየት ፤

፯/ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ፤ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ድርጅት እንደመሆኗ ሥርዓት ያላት መልክ ያላት መሆኗን ለመግለጥና ሁሉም ሥርዓቷን ማወቅና ማክበር እንዳለበት ለማስረዳት ።

፰/ ሥነ ምግባር ፤ የእምነታችን መግለጫው ፤ ከታወቂያው ምግባር በመሆኑ ማንኛውም አማኝ እምነቱን በምግባሩ ለመግለጥ የሚችል መሆኑን ለማስረዳት ።

ክርስቶስ ሰው በመሆኑ የመጀመሪያውን ርኅራኄ ያመለክታል ፤ ስለዚህ የክርስቶስ ተከታይ የሆነው ሁሉ ሰብአዊ ርኅራኄ ያለው ፥ በጎ አድራጎትን የሚፈጽም በሥነ ምግባር ያጌጠ መሆን አለበት ።

እንዲሁም ሌላ የቅዱስ መጽሐፍ ጥናት የሚል የተለየ ራሱን የቻለ ክፍል ይገኛል ። ይኸም ክፍል ቅዱስ መጽሐፍ በቅዱስ መንፈስ የተጻፈ ፤ ለሰው ልጅ ሁሉ መመሪያ ፥ መማሪያም ይሆን ዘንድ ከቅዱስ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የተሰጠ ከፍተኛ ስጦታ ነው ።

ማንኛውም የሰው ነገድ ሁሉ ይኸን ስጦታ አክብሮ ተቀብሎ ሊያጠናው ፥ ሊጠብቀው የሚገባ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህም ልዩ ክፍል ውስጥ የቅዱሳት መጻሕፍት ቊጥር ፣ ቅደምና ተከተላቸው፣ ቀኖናነታቸውም ተገልጦ ይገኛል ፤ እንዲሁም እያንዳንዱን መጽሐፍ ማን እንደጻፈው ፣ መቼ እንደተጻፈ ዓላማውስ ምንና ምን እንደሆነ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች መልሶቻቸው ተብራርተው ተገልጠው ይገኛሉ ።

ሌላ ክፍል ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚል እንዲሁ ራሱን የቻለ ክፍል ይገኛል ። በዚህም ክፍል ከክርስቶስ ልደት በፊት በዓለም ላይ ይታይ የነበረው የአስተዳደር ፣ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ይዞታ ምን ይመስል እንደነበር እን ረዳለን ።

ይኸም ክፍል ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ እስከ ፳ኛው ምእት ዓመት ያለውን የክርስትና ይዞትና ሂደት አጠቃሎ በአጭሩ የሚያስረዳ ሲሆን ለትን ተናው ያመች ዘንድ የተለያዩ ንኡሳን ክፍሎችን ይዞ ይገኛል ።

በአጠቃላይም ሙሉ ክርስቲያናዊ ምስክርነት እንዴት እንደሆነ ለማወቅና ለመመስከር እንድታ ስችል ሁና የተዘጋጀች መጽሐፍ ናት ።

እንግዲህ አንድ ሰው የሚመሰክረውን ደኅና አድርጎ ማወቅ ፣ በእውነትም መመስከር አለበት ፤ ስለዚህ አስቀድሞ ይህን ሁሉ ማወቅና ማመን አለ በት ። የሚናገረውን የሚያምን ፣ የሚያምነውንም የሚናገርና የሚመሰክር መሆን አለበት ፤ ታዲያ አስቀድሞ ማወቅ ስላለበት ይኸን የመሰለ መጽሐፍ መዘጋጀት አስፈለገ ።

አዘጋጁ



# ፀቢይ ክፍል ፩ ትምህርተ ክርስትና

## ክፍል ፩ የእምነት አንቀጽ

### ፩ እምነት ፤ በ፩ አምላክ ማመን

፩/ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አምናለሁ ፤ እርሱም የነበረ ፣ ያለ፣ የሚኖርም ነው ። ከእርሱ በፊት ማንም አልነበረም ፤ እርሱም ከፈጠረው ውጭ የተገኘ ነገር ከቶ የለም ፤ ሁሉም በእርሱ ተፈጠረ እንጂ ።

፪/ ሁሉም በእርሱ ሆነ ፤ ያለ እርሱ ግን ምንም የሆነ የለም ። የሚታየውም የማይታየውም በእርሱ ፈጣሪነት ተፈጠረ እንጂ (ጸሎተ ሃይ ፤ ዮሐ ፩ ፣ ፪) ።

፫/ ሁሉን የሚጠብቅ፣የሚያስተዳድርና የሚመግብ እርሱ ብቻ እንደሆነ አምናለሁ ።

ስለዚህም እርሱ ሳያውቀው የሚሆን ነገር ከቶ የለም ። እርሱ ብቻ በዓለም ሙሉ ነው ፤ ሁሉን ያያል ሁሉንም ያውቃል ፤ እርሱ ብቻ ረዳት የማይሻ ድካ ምም የማይሰማማው ፍጹም ከሃሊ አምላክ መሆኑን አምናለሁ ። ለእርሱ ተረስቶት የሚቀር ምንም ነገር የለም፤አስታዋሽም አይሻም ፤ ስለዚህም አምልኮት፣ ስግደት ፣ ምስጋና ለእርሱ ብቻ ይገባል ።

### ፪/ እምነት በሥላሴ ።

፩/እግዚአብሔር በባሕርይ፣በህልውና፣በመለኮት አንድ ሲሆን በአካል በስም፣በግብር ሦስት መሆ



www.ethiopianorthodox.org

ኑን እምናለሁ ። ስማቸውንም እንደሚከተለው አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ብዬ እጠራለሁ (ማቴ- ፳፰-፲፱) ።

የአካል ምስትንቶቻቸውም እንደሚከተለው ነው ፤

ለአብ ፍጹም አካል አለው ፤ ለወልድም ፍጹም አካል አለው ፤ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል አለው ።

፪/ ምንም ለአስተይቆ አካላት ፫ ብሎም በባሕርይ በህልውና በሥልጣን ፩ አምላክ መሆኑን እምናለሁ ። ስለዚህም በሦስትነት ያለውን አምላክ እምናለሁ እርሱንም ብቻ አመልካለሁ ።

፫/ ሥላሴ በቀድምናቸው አንድ ናቸው ፤ ቀዳሚና ተከታይነት የለባቸውም ፤ የሥላሴ ቅድምና ቸው አንዲት ናትና ። በሥላሴም የበላይና የበታች የለባቸውም ፤ ህልውናቸው አንድ ነውና ።

፬/ የክርስቲያን እምነት ልዩ ማንተም በሥላሴ ምስትንትና አንድነት ማመን ነው ፤ ስለዚህ በዚህ እምነቴ ጸንቼ እኖራለሁ ።

## ፫/ እምነት በሥጋው ቃል ።

፩/ ቃል አስቀድሞ እንደነበር እምናለሁ (ዮሐ ፩፡፩) ። ቃልም እግዚአብሔር እንደሆነ እምናለሁ ። (ዮሐ. ፩:፩ ።)

፪/ ቀዳማዊ ቃል በፍጻሜ ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው መሆኑን ሥጋንም መልበሱን እምናለሁ (ዮሐ.፩.፲፬) ። ስለዚህም ክርስቶስ ፍጹም ሰው ነው ። እንዲሁም በመለኮቱ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እኩል በመሆኑ ፍጹም አምላክ ነው ።

፫/ ቀዳማዊ አምላክ ደኃራዊ ሥጋን ሲዋሐድ፣ ደኃራዊ ሥጋም ቀዳማዊ መለኮትን ሲዋሐድ፣ ውላጤ የሌለበት ፍጹም አምላክ፣ ፍጹም ሰው መሆኑን እምናለሁ ።

፬/ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለአባት እንደተወለደ እምናለሁ ። ቀዳማዊ ልደቱን በደኃራዊ ልደቱ ገለጠው ፤ ስለዚህም ወልድ ዋሕድ ዘበኩር አደረገ ። በአንድ በኩል የአብ የባሕርይ ልጅ እንለዋለን እርሱም ነው ። (ዮሐ.፫. ፲፰ ፤ ማቴ. ፲፯.፲፭) ። እንዲሁም የሰው ልጅ ይባላል ፤ እርሱም ነው ። (ማቴ.፳፭.፴፩ ፤ ም ፳፯-፳፬ ፤ ም.፲፯-፳፪) ።

፭/ ክርስቶስ ሰው የሆነው ሥጋንም የለበሰው እኛን ለማዳን ሕማምን ሞትን ለመቀበል እንደሆነ እምናለሁ ። (ዕብ.፪.፱) ። ስለዚህም በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን ። (፩.ጴጥ. ፪-፳፬) ።

፮/ ክርስቶስ እንደሞተ ፣ በሥልጣኑም እንደ ተነሣ ፣ በባሕርይ ክብሩም እንዳረገ ፤ በአባቱም ቀኝ እንደተቀመጠ እምናለሁ ። (ጸሎተ ሃይ.) ።

## ፬/ እምነት በክርስቶስ ፪ኛ መምጣት ።

፩/ ክርስቶስ የሰውን ወገን ለማዳን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደዚህ ዓለም እንደመጣ፣ ይኸንም ዓለም አሳልፎ ለመኖር ለፍርድ፣ ፪ኛ ጊዜ ወደዚህ ዓለም





www.ethiopianorthodox.org

እንደሚመጣ እምናለሁ ። ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጣ በትሕትና ነበር ፤ ዳግኛው ጊዜ ሲመጣ ግን በግርማ መለኮት እንደፈራጅነቱ መሆኑን እምናለሁ ።

፪/ ክርስቶስ የሕያዋንም የሙታንም አምላክ እንደሆኑ ፣ ስለዚህ ሁሉንም እንደሚገዛ እምናለሁ ። ክርስቶስ የሁሉም ገዥ እንደመሆኑ እውነተኛም ፈራጅ ነው ፤ ስለዚህም ለያንዳንዱ እንደሥራው ይከፍለዋል ።

፫/ የሙታንን ትንሣኤ አምናለሁ ፤ ስለዚህ እያንዳንዱ ነፍስና ሥጋ የተዋሐደለት ፍጹም ሰው ሆኖ፣ተነሥቶ በክርስቶስ አደባባይ ለፍርድ ይቀርባል።

፬/ ሰማይና ምድር እንደሚያልፉ፣ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደምንወርስ እምናለሁ (ራእ. ፳፩፣፩)።ጻድቃን የክብር ትንሣኤ ተነሥተው አዲሱን ሰማይ፣አዲሱን ምምድር ይወርሳሉ ። ኃጥአን ደግሞ የኃሣር ትንሣኤ ተነሥተው፣ ወደ ዘለዓለም ዅነኔ ይሄዳሉ (ማቴ.፳፭፣፵፮) ።

## ክፍል ፪-ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን

### ፩ የምሥጢር ተካፋይነታችን ፤

፩/በበደል ምክንያት ጠፍቶ የነበረው የእግዚአብሔር ጸጋና ልጅነት በምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን አማካይነት እንደሚገኝ እምናለሁ ።

እነዚህም ምሥጢራት ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ከፈጸመው ቸርነት የመነጩ ናቸው ። በነዚህም ምሥጢራት አማካይነት ሁላችን እንታደሳለን፤ጸጋን እናገኛለን ።

፪/ ከእነዚህ ምሥጢራት አብዛኛዎቹ ክርስቶስ የመሠረታቸው እርሱም የፈጸማቸው ናቸው ። ስለዚህም የሰው ልጅ የሆነው ሁሉ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ናቸው ። እነርሱም ጥምቀት ፣ ሜሮን ፣ ቅዱስ ቍርባን ፣ ንስሐ ናቸው ።

፫/ ሌሎች ደግሞ ለተወሰኑ ብቻ የሚሰጡ ናቸው ። እነርሱም ተክሊል ፣ ክህነት ፣ ቀንዲል ናቸው ፤ በተወሰኑት ሰዎች ዘንድ በሚገባ መፈጸም አለባቸው ።

፬/ የቤተ ክርስቲያኔ አባል እንደመሆኔ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንም ተካፋይ መሆን ተገቢነቱን አምኜ ሁሉንም በተገቢው መንገድ እፈጽማለሁ ።

### ፪/ ምሥጢረ ጥምቀት ፤

፩/ ምሥጢረ ጥምቀት ክርስቶስ የመሠረተው ምሥጢር እንደሆነ ለኃጢአት ማስተሥርያ እንደሚሆን እምናለሁ ።

፪/ ከሥላሴ ለመወለድ፣ ከሰይጣን ቁራኝነት ለመላቀቅ ጥምቀት አስፈላጊ መሆኑን አምናለሁ ፤ ስለዚህም በአብ ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ አምኜ እጠመቃለሁ ።

፫/ ያመነ የተጠመቀ ብቻ እንደሚድን እምናለሁ፤(ማር.፲፮.፲፮) ። ስለዚህ በጥምቀት የእግዚአ



www.ethiopianorthodox.org

ብሔር ልጅነቴን የመንግሥቱ ወራሽነቴን አረጋግጣለሁ ።

## ፫/ ምሥጢረ ሜሮን ፤

፩/ ሜሮን ለክርስትና የመታወቂያ ማኅተመ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እምናለሁ ።

፪/ በጥምቀት ከሥላሴ እወለዳለሁ ። መንፈሳዊ ልደቴንም በሜሮን ማኅተምነት አረጋግጣለሁ ። ለዚህም ምስክሬ መንፈስ ቅዱስ ነው ።

## ፬/ ምሥጢረ ቊርባን ፤

፩/ ቊርባን ማለት የክርስቶስን ሥጋ በመብላት ደሙንም በማጠጣት እኛ ወደ ክርስቶስ እንቀርባለን ፤ እንዲሁም ሥጋው ከሥጋችን ፤ ደሙ ከደማችን በመዋሐዱ ፤ እግዚአብሔርም እኛን ይቀርበናል ፤ ይዋሐደናል ፤ ስለዚህም ቊርባን ይባላል ።

፪/ ሥጋውን ብልተን ደሙን ጠጥተን ፤ የዘለዓለም ሕይወት ልናገኝ እንደምንችል እምናለሁ ። (ዮሐ.፮. ፶፫-፶፮) ። ስለዚህም ሁልጊዜ ከሥጋውም መብላት ከደሙም መጠጣት አስፈላጊ መሆኑን እምናለሁ ።

፫/ በምሥጢረ ቊርባን አማካይነት የምእመናን ከእግዚአብሔርና ከክርስቲያን አንድነት ይገኛል ። ስለዚህም የዚህ የክርስቲያን አባል ሁሉ አንድነቱን የሚገልጠው ሥጋውን በመብላት ደሙን በመጠጣት ነው ።

፬ ፤ ቅዱስ ቊርባን ስንል ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ፤ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት እንደሚሆን



እምናለሁ ፤ ስለዚህ ንስሐ ገብቼ ፤ ከኃጢአት ነጽቼ መቅረብ እንዳለብኝ እምናለሁ ።

## ፭ ፤ ምሥጢረ ንስሐ

፩/ በደሌን ሁሉ ለካህኑ በመናዘዝ ፤ ንስሐም በመግባት የኃጢአት ሥርየት እንደማገኝ እምናለሁ ።

፪/ ካህኑ ኃጢአቱን የያዘበት እንደሚያዝበት ካህኑ ይቅር ያለው እንደሚቀርለት እምናለሁ ።

፫/ ንስሐ የበደለውን እንዳልበደለ ፤ ኃጥኡንም ጻድቅ የሚያደርግ መሆኑን እምናለሁ ። ስለዚህ አንድ በደለኛ ሲሠራ ያላፈረውን ያልፈራውንም በደል ለካህኑ ሲናገር ሳያፍር ሳይፈራ መናዘዝ አለበት ። እንዲሁም አንድ ጊዜ በደል መሆኑን አውቆ የተጸጸተበትን ኃጢአት ተመልሶ ላለመሥራት ሐሳቡን ቆርጦ መጣል አስፈላጊ ነው ።

፬/ ካህኑ አውጥቶ ፤ አውርዶ የሰጠው ቀኖና በትክክል መፈጸም አለበት ።

፭/ ሰው የሆነ ሁሉ ከበደል የማይርቅ ስለ ሆነ ማንኛውም ሰው በየጊዜው መናዘዝ ፤ ንስሐም መግባት አስፈላጊ መሆኑን እምናለሁ ፤ ስለዚህ እርሱም ካህኑም በወሰኑት ሰዓት መፈጸም አለበት ።

## ፮/ ምሥጢረ ክህነት

፩/ ምሥጢረ ክህነት ማለት ምሥጢራቱን ሁሉ የሚቀድስ የሚያከብር ፤ ክርስቶስ የመሠረተው ለቅዱሳን ሐዋርያት ያስተላለፈው ፤ ከእነርሱም



www.ethiopianorthodox.org

በአንብሮተ እድ ሲተላለፍ የነበርና የሚኖር ምሥጢር እንደሆነ እምናለሁ ።

፪/ ክህነት የአደፈውን የሚያነጻ የረከሰውን የሚቀድስ ምሥጢር እንደሆነ እምናለሁ ። ስለዚህ የታሠረውን ይፈታል ፤ በደለኛውን ያሥራል ። ካህኑም ያሠረውን ከቶ ሊፈታው የሚችል የለም ፤ እግዚአብሔርም ያነኑ ያጸናዋል ፤ ካህኑም ይቅር ያለው ይቀርለታል ፤ ሌላ የሚያሥረው የለም (ማቴ.፲፮ ፲፱ ፤ ም.፲፰፡፲፰፣ ዮሐ.፳፡፳፫) ።

፫/ ክህነት በእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኝ ሀብት እንጂ በወርቅ የማይገዛ፤በትውልድ የማይወረስ፤በወገንም የማይገኝ ነው ፤ ስለዚህ ለሥልጣነ ክህነት ብቁ የሆኑ ሰዎች ብቻ ይቀርባሉ ፤ እነርሱም ብቻ ያገኛሉ ። እርሱም በንጽሕና በጥራት መያዝ አለበት ፤ ድቀት ከአገኘው በኋላ የማይታደስ ነውና ።

፬/ ክህነት ለማንኛውም ሰው የማይናኝ ምሥጢር ነው ፤ በመጀመሪያ ለተባዕት ጾታ ብቻ ይሆናል ፤ ከዚያውም ብቃት ላላቸው ብቻ ይሆናል ።

፯/ ምሥጢረ ተክሊል ።

፩/ ተክሊል ማለት በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል በሚደረገው የስምምነት ጋብቻ ላይ የሚፈጸም ጸሎቱና ቡራኬ ነው ።

፪/ ሁለቱ የተለያዩ ጾታዎች በእግዚአብሔር ቃል በካህኑ ጸሎትና ቡራኬ አንድ አካል እንደሚሆኑ እምናለሁ ፤ (ማቴ.፲፱፡፮) ። እግዚአብሔር አንድ



ያደረገውን ሊለይ የሚችል የለም ፤ ስለዚህ ባልና ሚስት አንድ አካል ናቸው ።

፫/ በጸሎተ ተክሊል ተፈጽሞ የተጋቡት ጋብቻ ከሞት በቀር ሊለያዩ የማይገባ መሆኑን በዚች መጽሐፍ አስረጅነት መሠረት እምናለሁ ።

የሰው ዘር ይበዛ ዘንድ ምትክም ለማትረፍ ለመረዳዳትም ጋብቻ አስፈላጊ ነው ፤ ግን ሁልጊዜ በቤተ ክርስቲያን በጸሎተ ቡራኬ መፈጸም አለበት ።

፬/ ለባልና ለሚስት የጋራ የሆነ ኃላፊነት ስላለባቸው በጋራ ለመወጣት አብሮ ማሰብ፣ መነጋገር ፣ መሥራትም አለባቸው ፤ ይኸም ከግዴታቸው ፩ኛው ነው ።

፰/ ምሥጢረ ቀንዲል

፩/ ምሥጢረ ቀንዲል ማለት በበሽተኞች ላይ የሚጸለይ ጸሎትና የሚቀቡት የድኅነት ዘይት ነው ።

፪/ በሃይማኖት የሚጸልዩት ጸሎት በሽተኛውን እንደሚፈውስ ፣ ኃጢአቱንም እንደሚያስተሠርይለት እምናለሁ (ያዕ.፭፡፲፬—፲፭) ። ስለዚህ ከምእመናን ውስጥ አንድ ሰው በታመመ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት የተለየ ጸሎት ሊያደርጉለት ይገባል ።



www.ethiopianorthodox.org

፫/ ቅዱሳን ሐዋርያት ሲፈጽሙት የኖሩ እኛም ልንፈጽመው የሚገባን ምሥጢር ነው (ማር. ፮፥፲፫) ።

፬/ በዚህ ምሥጢር መፈጸም የነፍስም የሥጋም በሽታ ያለበት ፈውስ እንደሚያገኝ እምናለሁ። (ያዕ. ፭፥፲፬) ።

## ክፍል ፫ የእግዚአብሔር ሕገመንግሥት

### ሀ—አሠርቱ ቃላት፡አሥራት

እግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር መገናኛ ያደረገው ቃል ኪዳንም የተጋባበቸው፡ ዐሠርቱ ቃላት አሥራት የሚባሉት ናቸው ።

እነዚህን ሕግጋት በመጠበቃችን ከአምላክ ጸጋን፥ በረከትን ፥ እንደምናገኝ እነዚህንም በማፍረሳችን መቅሠፍት እንደሚደርስብን አምላክ እውነተኛ ቃሉን ማስጠቱን እምናለሁ።እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

፩/ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ ፤ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ፤ በፊትህም አይኑር፤ (ዘጸ.፳፥፪-፫) ።

፪/ የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርግ ፤ ስሙን ከንቱ ያደረገውን እግዚአብሔር ሳይቀሥፈው አይቀርምና ። (ዘጸ፥፳፥፯) ።

፫/ የሰንበትን ቀን አስብ፤ ትቀድሰው ዘንድ ፤ (ዘጸ.፳-፲-፲፩) ።



፬/ አባትህንና እናትህን አክብር ዕድሜህ ይረዝም ዘንድ እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር ፤ (ዘጸ.፳.፲፪) ።

፭/ ነፍስ አትግደል ፤ (ዘጸ.፳.፲፫) ።

፮/ አታመንዝር ፤ (ዘጸ.፳.፲፬) ።

፯/ አትስረቅ ፤ (ዘጸ.፳.፲፭) ።

፰/ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር። (ዘጸ.፳.፲፮) ።

፱/ የባልንጀራህ ንብረት የሆነውን ሁሉ አትመኝ፤ (ዘጸ.፳.፲፯) ።

፲/ ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ። (ዘሌዋ.፲፱.፲፰) ።

### ማብራሪያ ፤

እግዚአብሔር አምላክ ከሁሉ በላይ የሆነ ንጉሠ ነገሥት አምላክ አማልክት ነው ፤ የሚታየውም የማይታየውም ዓለም ፈጣሪና ገዥ እርሱ ነው ። በተለይ የሰውን ልጅ የሚያስተዳድርበት ሕገ መንግሥት አለው ፤ ስለዚህም እርሱ የሠራውን ማንም ሊሽረው ሊያሻሽለው ስለማይችል እንዳለ አድርጎ መጠበቅ የሁሉ ግዴታ ነው ። እነዚህም ሕግጋት ፀ፲ ሕናቅጽ የተከፈሉ ሲሆኑ ከነርሱ ውስጥ ፫ቱ አና ቅጽ አምላክ አማልክቱን ንጉሠ ነገሥቱን እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ናቸው ። እነርሱም ፤

፩/ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ።ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ፤ በፊትህም አይኑር።



www.ethiopianorthodox.org

፫/ የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርግ፤ ስሙን ከንቱ ያደረገውን እግዚ አብሔር ሳይቀሥፈው አይቀርምና ።

፬/ የሰንበትን ቀን አስብ ትቀድሰው ዘንድ የሚሉ ናቸው ።

በዚህም አገላለጥ የእግዚአብሔርን አምልኮት ለጣዖት፣ለሚርት ልንሰጥ የማይገባ መሆኑን ያስጠን ቅቃል ፤ ይኸም ከሆነ መመለክ ያለበት እርሱ ብቻ ነው ፤ አምልኮት የባሕርዩ የግሉም ነውና ።

እርሱ ብቻ የነበረ ነው ፤ እርሱ ብቻም ያለ ነው ፤ እርሱ ብቻም ለዘለዓለም የሚኖር አምላክ ነው ።

ስለዚህ ለእርሱ ተወዳዳሪ፣ ተመሳሳይም ስለሌለው ለእርሱ የሚገባውን ክብርና አምልኮት ለባዕድ ልንሰጥ አይገባንም ።

እንዲሁም ስሙን በሆነውም ባልሆነውም ምክንያት እንዳንጠራው ያስጠንቅቀናል ፤ የእግዚአብሔር ስም በምስጋና ብቻ ይነሣል ይጠራልም እንጂ ።

፬ኛው አንቀጽ አምላክ ለሰው ልጅ ክብር ዕረፍት አድርጎ የሠራትን የአምላክን ቀን ሰንበትን እንድናከብራት፣የዕረፍትን ቀንም እንድናደርጋት ያሳስበናል ።

በዚህችም ዕለት ፀጎ አድራጎትን በመፈጸም ቅዱስ ቃሉን በመስማት በማሰማት መዋል እንጂ



ሌላ ሥጋዊ ተግባራችን እንዳንፈጽምባት ያስጠን ቅቀናል ።

ሌሎች ፅባቱ አናቅጽ ግን ሰው የሆነ ሁሉ ለዚያው ለሰው ልጅ ለመሰሉ ሊያደርገው የሚገባው ሊሠራቸውና ሊፈጽማቸው የሚገቡ ናቸው ፤ እነርሱም ፥

፭/ አባትህንና እናትህን አክብር ይላል ፤ ይኸም ማለት ወላጆች ስላንተ ሕይወት፣ ምግብ፣ ጤና የደከሙትን ድካም፣ ያወጡትን ወጭ አስብ፤ባለውለታነታቸውንም አውቀህ ብድራት መክፈል ፥ ውለታም መመለስ አለብህ ማለት ነው ።

ወላጅን ፀማክበር የሰው አዋቂነቱ፣ ከፍተኛም ፍጥረት መሆኑ ይገለጣል ፤ ማለት ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ልጆቻቸውን በአምላካዊ የተፈጥሮ ግዴታ ያሳድጋሉ ፤ ግን በኋላ ፀልጆቻቸው ከቶ አይረዱም ፤ እንዲያውም አይተዋወቁም ። ወላጆች ልጆችን በብዙ ጥንቃቄ ያሳደጓቸውን ያህል ልጆች ደግሞ ወላጆቻቸውን በሚገባ የረዱ እንደሆን ተፈጥሯቸውን አስከበሩ ፤ ክብራቸውን ገለጡ ማለት ነው ።

አንተም ነገ ከልጆችህ ብድራትን እንደምትከፈል አምነህ አሁን አንተ ልጆችህን ርዳ ተከባከብ ።

፮/ አትግደል ፤ ይኸም ማለት የእግዚአብሔርን ሕንጻ አታፍርስ ማለቱ ነው ፤ ማንኛውም ሰው በፈቃዱ ወደዚህ ዓለም የመጣ አይደለም ፤ አምላኩ አመጣው ፈጠረውም እንጂ ፤ እንግዲህ አምላክ



www.ethiopianorthodox.org

ለክንቱ አልፈጠረውም ለተቀደሰ ተግባር ሊያውለው እንጂ ። እንግዲያውስ አምላክ ለአንድ ቅዱስ ተግባር የፈጠረውን ሰው በከንቱ ማጥፋት፣ (ነፍስ መግደል) ትልቅ ጥፋት ነው ። ያልሠሩትን ሕንጻ እንዴት ሰዎች ያፈርሳሉ ? የሕንጻው ባለቤት ይከሳል ፤ ያስቀጣል ፤ እንግዲያውስ ከሕንጻው የሰው ተፈጥሮ ይበልጣል ፤ የሰው አካል ከግንብ ይበልጣልና ማንም ሊያፈርሰው አይገባውም ።

አንተ ለሌላው ነፍስ ስትጠነቀቅ፣ ሌላው ደግሞ ስለ አንተ ነፍስ ይጠነቀቅልሃል ። አንተ ስለሌላው ነፍስ ግድ ከሌለህ የአንተንም ነፍስ ያስጋታል ።

፫/ አታመንዝር ፤ ይኸም ማለት የራስህ ወዳልሆነችው ሴት አትሂድ ፤ የአንተንም የእርሷንም የጋብቻ እምነት አታጥፋ ።

ሚስቱ ወዳልሆነችው ሴት መሄድ ዓመፅ ነው፤ ማለት ሀብቱ፤ ገንዘቡ ያልሆነውን እንደ መዝረፍ፣ እንደመቀበጥም ይቆጠራል ።

የእርሱንም ሚስት እንዲሁ ሌሎች ሊይዚት ይችላሉና ፤ እንዲሁም ማንኛዋንም ሴት ማሳሳት፣ በልትወጹ ላይ ዓመፅ መሥራት፣ በእርሱም በእናቱ፣ በሚስቱ፣ በእኅቱ ላይ ዓመጽ እንዲሠሩባቸው ፈቅዷል ማለት ነው ።

ለወንድ እንቀጽ ሸለቶናገርነው ለወንዱ ብቻ አተቱነው እንጂ ሴትም ባሏ ወዳልሆነ ወንድ መሄድ እንዲሁ ዓመፅ ነው ።



፬/ አትስረቅ ፤ ይኸም ማለት ያልደከመበትን፣ ንብረቱ፣ ሀብቱ ያልሆነውን መውሰድ እንደማይገባ ያስጠነቅቃል ። መስረቅ ቢሰውር ነፍስ እንደመግደል ነው ፤ ማለት የአንዱን ሀብት የሚበላውን የሚጠጣውን፣ ሕይወቱ የሚደገፍበትን ወስዶበት ይኸ ሰው የሚበላው የሚጠጣው አጥቶ ይሞታልና ።

እንዲሁም አንተ የሌላውን ሀብት እንደሰረቅህ የአንተንም ሌሎች ይሰርቁሃል ፤ እንዲህም ከሆነ ሀብት ያለው ሰው አይኖርም ፤ ሰላምም በምድር ሊኖር አይችልም ። ከለዚህ ያንተም ሀብት ሕይወትህም ይጠበቅልህ ዘንድ አትስረቅ ።

፭/ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር ፤ ይኸም ማለት የባልንጀራህ ሀብቱ የሚባክንበትን፣ ሕይወቱ የሚጠፋበትን፣ መብቱን የሚያጣበትን በመፈለግ፣ በሌላም ይኸን በመሳሰለ ቢሆን በሐሰት አትመስክርበት ።

እንዲሁም ለግል ጥቅምህ ስትል በገንዘብ ተደልለህ ፣ ለወገንህ ብለህ በሐሰት አትመስክር ፤ ነገ በአንተም ላይ እንዲሁ የሐሰት ምስክር አስመስክረው ሀብትህን ንብረትህን ያስወስዱብሃል ። ከዚህም የበለጠ ሕይወትህን ያስጠፉሃል ፤ እውነቱን እውነት፣ ሐሰቱን ሐሰት በል እንጂ ።

፮/ የባልንጀራህን ሀብት አትመኝ ፤ እያንዳንዱ ሰው ወጥቶ፣ ወርዶ፣ ወዙን አፍስሶ፣ ሠርቶ ብቻ እንዲበላ እንጂ የሌላውን ሀብት መመኘት ከፍተኛ ወንጀል



www.ethiopianorthodox.org

ነው ፤ ምክንያቱም ምኞት የኃጢአት ሁሉ ሥር ስለሆነች ምኞቱ ወደ ፍጻሜ ሊደርስ ይችላልና ።

አዋቂ ሰው ኃጢአትን ገና ከምኞት ቀርጦ የጣላት እንደሆነ ከበደል ይድናል ፤ ስለዚህ አትመኝ አለ።

፯/ ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ ፤ ባልንጀራ ማለት በተፈጥሮ ሰው የሆነው ሁሉ ነው ። ከሩቅም ይምጣ፤ጎረቤትም ይሁን ሰው ለሰው ባልንጀራው ስለሆነ ፤ ሁሉንም አስተካክሎ መውደድ አለበት ፤ ሰው ለሰው ወንድሙ ባልንጀራውም ነው ፤ ስለዚህ ሁሉም መፋቀር ፣ መተዛዘን ፣ መረዳዳት አለባቸው ።

ፍቅሩም ደግሞ የቃል ሳይሆን የይዩልኝና የይስሙልኝም ሳይሆን በሥራ የሚገለጥ በርዳታ የሚታይ ፍቅር ሊሆን ይገባል ፤ አንተን እንደሚርብህ ሌላውንም ይርበዋል በል፤አንተንም እንደሚቸግርህ ሌላውንም ሰው ይቸግረዋል በል ። እንዲሁም አንተ በዚህ መልክ ስትፈጽመው ሌላውም ለአንተ በዚህ መልክ ይፈጽምልሃል ። በዚህን ጊዜ ችግር ከሰው ወገን ይጠፋል፤ «ዘመድ ቢረዳዳ ችግርም አይጎዳ» ነውና ።

ይኸ የመጨረሻው አንቀጽ ሌሎቹን ዘጠኙን አንቀጾች ሁሉ ያጠቃልላል ፤ ማለት እርሱ በመፈጸሙ ሌሎች ሁሉ ይፈጸማሉ፤እርሱ በመፍረሱ ሌሎች ሁሉ ይፈርሳሉና ። ለምሳሌ አንድ ሰው አምላኩን ከወደደው አምልኮቱን ለባዕድ አይሰጥበትም ፤ ስሙንም በከንቱ አይጠራውም ፤ ሕግጋቱንም በጠቅ



ላላ አያፈርስም ፤ እግዚአብሔር ከብዙ ስሕተት ይጠብቃልና ።

እንዲሁም ባልንጀራውን ከወደደ አይገድለውም ፤ ሀብቱን፤ንብረቱን አይመኝበትም ፤ አይሰርቀውም ፤ ፀሐሰትም አይመሰክርበትም ፤ እንዲያውም በዚህ ፈንታ ለባልንጀራው ያስባል፤ ይናገራል ፤ ይሠራል ።

እንግዲህ በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ ዐሥሩ ቃላት ሊጠበቁ ሊፈጸሙም ይችላሉ (ማቴ.፳፪.፵) ይኸንም አማናዊ የሚያደርግ ክርስቶስ ሲያስተምር «የሚወደኝ ሕጌን ይጠብቃል» ይላል ፤ (ዮሐ.፲.፲፭) የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫ ሕጉን መጠበቅ ነውና ።

ክርስቶስን ከሞት ያደረሰው ፍቅረ ሰብእ ነው፤ ራሱን «ለሰው ልጅ ቤዛ አድርጎ ከመስጠት በላይ ፍቅር የለምና» (ዮሐ.፲፭.፲፫) ።

ለ/ ፯ቱ ቃላተ ወንጌል ።

፩/ በወንድምህ ላይ በከንቱ አትቆጣ (ማቴ.፭.፳፪.፳፮) ።

፪/ ወደሴት አትመልከት በልብህም አታመንዝር (ማቴ.፭.፳፰) ።

፫/ ሚስትህን ያለዝሙት ምክንያት በሌላ ነውር አትፍታት (ማቴ.፭.፴፪) ።



www.ethiopianorthodox.org

፬/ ፈጽመህ አትማል (ማቴ.፭.፴፬) ።
፭/ ክፉውን በክፉ አትቃወም ፤ (ማቴ.፭.፴፱) ።
፮/ ጣላቶችህን ውደድ ፤ (ማቴ.፭.፵፬) ።

## ማ ብ ራ ሪ ያ ።

፩/ በወንድምህ ላይ በከንቱ አትቆጣ ፤ ሰው የሆነው ሁሉ ወንድምህ ወዳጅህ ነው ፤ ስለዚህ አትጥላው ፤ አትጣላውም ፤ በሆነውም ባልሆነውም አትቆጣው ፤ ከድንገተኛ ቁጣ ተነሥተው እስከ ነፍስ ግዳይ ይደርሳሉና ፤ ስለዚህ በመጀመሪያ ቍጣህን ከአንተ አርቅ ፤ በቍጣ ሰው ተዋሕዶት የሚኖር መንፈስ የለምና ።

፪/ ወደሴት አትመልከት በልብህም አታመንዝር ፤ ማለት በዓይንህ አይተህ ለሚኝ አይዶርህ ፤ በልብህም አታመንዝር ማለት ነው ።

ዓይን ሁሉን ይመለከታል ፤ ግን ወደ ልቡናው የሚልከው የሚፈቅደውን ነው ፤ ስለዚህ ሴትን በክፉ ምኞት አትመልከታት በልብህም ለዝሙት ሥራ አትመኛት ማለት ነው ። ሐሳብ ሁልጊዜ ወደ ተግባር ይለወጣልና ።

ዓይን ብዙ ነገርን እንደሚመለከት እልፍትም የሚሄደው ብዙ እንደመሆኑ ማንኛዋንም ሴት ያያል ግን ምንም ስሜት ሳይኖረው እልፍ ሲሄድ ይገባዋል ።



፫/ ሚስትህን ያለዝሙት ምክንያት አትፍታ ፤ ይኸም ማለት ባልና ሚስት አንድ አካል ናቸው ፤ እግዚአብሔር አንድ ያደረጋቸውንም ማንም ሊለይ አይችልም (ማቴ ፲፱.፮) ። ስለዚህ ይኸ አንቀጽ በምንም ምክንያት ቢሆን ሚስቱን ማንም እንዳይፈታ ያስጠነቅቃል ።

ሥነ ፍጥረትን ስንመለከት ለአዳም ሔዋንን ፤ ለሔዋንም አዳምን ብቻ ነው እግዚአብሔር አምላክ የሰጠው ፤ ይኸም የሚያመለክተው ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት ብቻ ፤ ለአንዲት ሴትም አንድ ወንድ ብቻ ስለሆነ እነርሱ ተስማምተው ከተጋቡ በኋላ መፋታት መለያየትም እንደማይገባቸው የሚያመለክት ነው ።

፬/ ፈጽመህ አትማል ፤ ይኸም ማለት በሀብትህ፣ በንብረትህ፣ በመብትህ፣ በሕይወትህም ሳይቀር ክርክር ተነሥቶብህ እንድትምል ብትጠየቅ ፈጽመህ አትማል ማለቱ ነው ።

መሐላ እንኳን በሐሰት በእውነትም ቢሆን ፈጽሞ ክልክል መሆኑን ያመለክታል ፤ የእግዚአብሔርን ስም ከንቱ ማድረግ ነውና (ዘሌዋ፡፲፱፡፲፪) ።

፭/ ክፉውን በክፉ አትቃወም ፤ ይኸም ማለት ክፉ ነገር ከሰው ዘንድ ቢደርስብህ በትዕግሥት ለማሳለፍ ሞክር እንጂ ክፉ እንደሠራብኝ እኔም ክፉ ልሥራበት አትበል ፤ ክፉውን ሰው በክፉ ነገር ልበቀለው አትበል ማለቱ ነው ፤ ከሁሉ ጋር በሰላም



www.ethiopianorthodox.org

በስምምነትም መኖር አስፈላጊነቱን ሲገልጥ እንዲህ አለ ።

፯/ ጠላትህን ውደድ ፤ ይኸም ማለት ከሁሉ ጋር ተስማማ፤ ተፋቀር እንጂ ጠላት ከቶ አይኑርህ ፤ የተጣላህም ሰው ቢኖር እንደ ጠላት አትየው ፤ አቅርበው ፤ እንደ ወዳጅህም እየው ማለቱ ነው ።

ክርስቶስ ሁሉን በመውደድ ፍጹም ነው ፤ አንተም የእርሱ ተከታይ እንደመሆንህ ሁሉን በመውደድ ፍጹም ሁን (ማቴ.፭.፵፬.፵፰) ።

## ሐ/ ፰ቱ ቃላተ ወንጌል ።

አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚሉት ፰ቱ ቃላተ ወንጌል እነዚህ ናቸው ።

፩/ ብራብ አብልታችሁኛልና ፤ (ማቴ.፳፭.፴፭) ።
፪/ ብጠማ አጠጥታችሁኛልና ( » » »
፫/ እንግዳ ብሆን ተቀብላችሁኛልና (ማቴ. ፳፭.፴፭) ።

፬/ ብታረዝ አልብሳችሁኛልና (ማቴ.፳፭.፴፮።
፭/ ብታመም ጎብኝታችሁኛልና (» » »
፮/ ብታሰር ጠይቃችሁኛልና (ማቴ.፳፭.፴፮) ።

## ማ ብ ራ ሪ ያ

፩/ ብራብ አብልታችሁኛልና ማለቱ ብድራት ይከፍሉናል ውለታ ይመልሱልናል ሳትሉ ፣ ወይም ሰው ይይልን፣ ይመስክርልን ሳትሉ ችግረኞችን አብልታችኋልና ማለቱ ነው ። በኃላፊው ገንዘብና ጊዜ የማያልፍ ሥራ ሠርተውበታልና ።



ይኸም ነገ እነርሱ ተመሳሳይ ችግር ቢደርስባቸው ሌሎች ይረዷቸዋል፤ ከዚህም በቀር ክርስቶስ በኋለኛው ዓለም ዋጋቸውን ይከፍላቸዋልና ።

፪/ ብጠማ አጠጥታችሁኛልና ማለቱ የተጠሙትን ወገኖች ብድራት ሳትሹ አጠጥታችኋልና ፤ የተራቡትን፣የተጠሙትን ነግ በኔ ብላችሁ፣ አዝናችሁ የርኅራኄ ሥራን ሠርታችሁላቸዋልና ።

፫/ እንግዳ ብሆን ተቀብላችሁኛልና ማለቱ የተቸገረውን ፣ ቀን የጣለውን ሰው የማውቀው ነው ፣ ባለውለታየ ነው ፣ ሳትሉ፣ ወይም ወደፊት እንዲህ ያለ ውለታ ይውልልኛል ሳትሉ በቤታችሁ ተቀብላችሁ አስተናግዳችኋልና ።

ቤት የእግዚአብሔር ነው ፤ ሰውየው ጊዜያዊ አስተናባሪ ነው ፤ ስለዚህ እርሱ ለብዙ ዘመናት በማይቆይበት ቤት ለእግዚአብሔር ብሎ እንግዳን መቀበል ተገቢ ነው ።

ቀን ተለዋዋጭ ነውና ነገም አንተ ከሞቀ ቤትህ፣ ከተደላደለ ንብረትህ ትፈናቀልና ወጥተህ ትዞራለህ ፤ ዛሬ አንተ እንግዳን የተቀበልክ እንደሆነ ነገ ደግሞ ለአንተ ተቀባይ እግዚአብሔር ያዝልሃል ፤ በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር የመንግሥቱ ወራሽ ያደርግሃል።

፬. ብታረዝ አልብሳችሁኛልና ማለቱ ፣ ብዙዎችን ችግረኞች ረድታችኋል ፤ ነውራቸውን ሸፍናችኋል ፤ ኃፍረታቸውን ሠውራችኋል ፤ ለሰው ልጅ ክብር ሰጥታችኋል ማለቱ ነው ። ሰውን መርዳት ራስን መርዳት ነው ፤ ማለት የሰው ተፈጥሮ አንድ ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

፫/ ብታመም ጎበኛችሁኛልና ፡ ማለቱ ሰው ከታመመ ይሞታልና፤ምን ያደርግልኛል ሳትሉ በሽተኛ ችን ጎበኛችሁኛልና ። ሰው በአካሉ በጤናው አያዝ በትም ፤ስለዚህ ጤነኛ የነበረው ሰው በሽተኛ ይሆ ናልና ፤ ያንን መርዳት ተገቢ ነው ።

፬/ ብታሠር ጠይቃችሁኛልና ፤ ማለቱ ሰው አጥፍቶም ሳያጠፋም ድንገት ይታሠራል ፤በዚህን ጊዜ ወንጀለኛ ነው ብሎ ሳይጠሉ በእሥራቱም ሳያ ፍሩ መጠየቅ ተገቢ መሆኑን ያመለክታል ።

አንተም ነገ አጥፍተህም ሳታጠፋም ልትታሠር ትችላለህ ፤ ስለዚህ አንተ ለሰው ያዘንከውን ያህል ለአንተም ሰዎች ያዝኑልሃል ። ለሰው የረዳኸውን ያህል ለአንተም ይረዱሃል ፤ ስለዚህ የታሠሩትን በር ኅራኄ በበጎ አድራጎት ጎብኙቸው ማለቱ ነው ።

ይኸን ፮ቱን ቃላተ ወንጌል የፈጸመ አስቀድሞ ዓለም ሳይፈጠር እግዚአብሔር ያዘጋጃትን መንግ ሥት ይወርሳል (ማቴ ፳፭.፴፬.፴፮) ።

## ክፍል ፫ ስለ ጸሎት

፩-፤ ጸሎት በፈጣሪና በፍጡር መካከል የሚ ደረግ ግንኙነትና ንግግር ነው ። (ፍት ነገ አንቀጽ ፲፬) ።

ሰው ሰፈጣሪው እምነ የችግሩ ረዳት እንዲሆ ንለት ይለምነዋል ፤ ስለክብሩና ገናንነቱም ምስጋና ያቀርብለታል ፤ እግዚአብሔርም ደግሞ የፍጥረቱ ሁሉ አባት እንደመሆኑ የጸለዩትን ጸሎት ሰምቶ



ያቀረቡትን ምስጋና ቅዳሴ ተቀብሎ የሰዎችን ፍላ ጎት ያሟላል ።

፪/ በማንኛውም ጊዜ ፣ በታ ሁናቴ ለእግዚአብ ሔር ልመና ፣ ምስጋና ማቅረብ ለሰው ሁሉ ተገቢ መሆኑን እምናለሁ ፤ ከአምላክ ፊት በቀረብን ጊዜ እርሱም እንደሚቀርብን እንደሚሰማን አምነን እን ጸልያለን ፤ ስለዚህ ከቂም፣ከበቀል ርቀን ከኃጢአት ነጽተን ወደእርሱ መቅረብ አለብን ።

፫/ በግልም ፣ በቤተ ሰብም ፣ በማኅበርም መጸ ለይ ተገቢ መሆኑን አምናለሁ ። ስለዚህ በደስታም በኀዘንም ጊዜ በግሌም፣ ከቤተሰቦቼ ጋርም፣በቤቴም፣ ቢሆን በቤተ ክርስቲያንም ተገኝቼ መጸለይ ግዴታዬ መሆኑን አምናለሁ ።በግልና በቤተ ሰብእ ጸሎት ጊዜ በቤቴ ፣ በማኅበር ጸሎት ጊዜ ግን በቤተ ክርስ ቲያን መገኘት ግዴታዬ ነው ።

፬ ፤ በየዕለቱ መጀመሪያ ማለት በጧት ከሰው ጋር ከመነጋገር በፊት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩ ተገቢ መሆኑን በማመን የነግህ ጸሎቱን እንደሚ ከተለው አደርሳለሁ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ጸሎተ ነግህ (ዘዘወትር)

(ገጽህን በማማተብ የሚከተለውን ጸሎት በል) ።

ሀ/ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ

በቅድስት ሥላሴ እንዘ አአምን ወእትመሐጸን፥እክ ሕደከ ሰይጣን ፀቅድመ ዛቲ እምየ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፥ እንተ ይእቲ ስምዕየ ማርያም ጽዮን ለዓለመ ዓለም ።

ለ/ ነአኵተከ እግዚእ ወንሴብሐከ ፥
ንባርከከ እግዚአ ወንትአመነከ፥ንገኒ ለከ እግዚአ ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ ።

ንሰግድ ለከ ኦ ዘለከ ይሰግድ ኵሉ ብርክ፥ወልከ ይት ቀነይ ኵሉ ልሳን ።

አንተ ውእቱ አምላከ አማልክት ወእግዚአ አጋእ ዝት ወንጉሠ ነገሥት አምላክ አንተ ልኵሉ ዘሥጋ ወለኵላ ዘነፍስ ።

ወንጼውአከ በከመ መሐረነ ቅዱስ ወልድከ እንዘ ይብል አንትሙሰ ሶበ ትጼልዩ ከመዝ በሉ ።

—፲፰—

## የነግህ ጸሎት (የዘወትር) ።

ሀ/ በአብ በወልድም በመንፈስ ቅዱስም ስም አንድ አምላክ በሚሆን ፥ በቅድስት ሥላሴ እያመን ኩኝና እየተማጸንኩኝ ዕይጣን እክድሃለሁ ፤ እናቴ በምትሆን በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፊት፥ይኸች ውም ምስክሬ ማርያም ናት ፤ ለዘለዓለም መጠጊያ የምትሆን ።

ለ/ አቤቱ ፈጽመን እናመሰግንሃለን ፤ አቤቱ እንባርክሃለን ፤ እንተማመንብህምአለን ፤ አቤቱ እንገዛልሃለን ፤ ለቅዱስ ስምህም እንቀኛለን ። እንሰግድልሃለን ፤ ጉልበት ሁሉ የሚሰግድልህ ሆይ ! አንደበትም ሁሉ ለአንተ ይገዛልሃል ።

አንተ የአማልክት አምላክ ነህና ፤ የገዢዎችም ገዥ ነህ ፤ የነገሥታትም ንጉሥ ነህና ፤ የሥጋም ሁሉ፥ የነፍስም ኹሉ እምላክ አንተ ነህና ።

ቅዱስ ልጅህም እንዳስተማረን እንዲህ ስንል እን ጠራሃለን ፤ እናንተስ ስጸለያችሁ ጊዜ እንዲህ በሉ ቢል ።

—፲፱—

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ ላይ በየዕለቱ ማንኛውም ሰው በራሱ የሚመስለውን ሁሉ እንደሁኔታው ከዚህ ላይ አስ ጥቦ ሊጸልይ ይችላል ። ለጊዜው ከዚህ እንደሚ ከተለው አሳያለሁ ።

ሐ/ የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሚታየውንና የማይታየውን የፈጠርክ አምላካችን እግዚአብሔር ! አንተ የምስጋና ጌታ የክብርም ባለቤት ነህ ፤ ስለ ዚህ ንጹሕ ምስጋናን በዚች ንጋት ለአንተ አቀርባ ለሁ ፤ ለአንተ ብቻ ጉልበት ሁሉ ይሰግዳል ፤ እንደ በጎም ሁሉ አንተን ብቻ ያመሰግናል ። አንተ የጌቶች ጌታ የነገሥታትም ንጉሥ ነህና ። ልዩ ልዩ የሆነውን ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሰውን ፍጥረት ሁሉ የፈ ጠርክ ፥ ከዚህም ውስጥ እኔን በአርአያህ የፈጠርከኝ ፥ ንባብን እእምሮን ያሳደርክብኝ ፥ በሰጠኸኝ አንደ በት ንጹሕ ምስጋናን አቀርብልሃለሁ ። በየጊዜውና በየሰዓቱ ብዙ በጎ አድራጎትን አድርገኽልኛል ፤ ብዙም ውለታም ውለኽልኛል ፤ ይህንም አብዝተህ ፀንቶ አድለኸኛል ።

አሁንም ሌሊቱን በሰላም አሳልፍ ዘንድ እንደረዳኸኝ መዓልቱንም በሰላም አሳልፈው ዘንድ ርዳኝ ፤ ዕለቷን በረከት አድርገህ አድለኝ ። አምላክ ሆይ ! በዚህች ዕለት የምሠራው ሁሉ በአንተ ዘንድ የተወደደ የተፈቀደም ይሁንልኝ ። በዚህች ንጋት ከእኔ ጋር አብረኸኝ ተነሥ ፤ ወደ ልዩ ልዩ ሥራም እሠማራ ዘንድ አንተ ምራኝ ፤ በአንተ ፈቃድ ልራ መድ ፥ በአንተም መሪነት ልመራ ፥ ኃይልና ሥልጣን የባሕርይህ የሚሆን ፥ አምልኮትና ስግደት አሁንም ለአንተ ይሁን ፤ ለዘለዓለሙ አሜን ።

(የቤተ ሰብ አስተዳዳሪ የሆነ እንደሆነ ቀጥሎ ያለውን ይበል ። )

የሰጠኸኝን ቤተሰብ ባርክልኝ ፤ ለሁሉም ሕይ ወትን ፥ ጤንነትን አድልልኝ ፤ ሁሉም የአንተ ወገን ይሆኑ ዘንድ አንተ ምረጣቸው ። በጠቅላላም ወገኔን ሕዝቤንም ሁሉ ባርክ ፤ የሁሉም ኑሮ የሰላም ፥ የጸጥታም ይሆን ዘንድ ሰላምህን ስጠኝ ። ሀገራችንን ባርክ ፤ ያንተ ስም ይቀደስባት ፥ አምልኮትህም ይገለጥባት ፥ ለዘለ ዓለሙ አሜን ።





www.ethiopianorthodox.org

## መ/ አቡነ ዘበሰማያት

ይትቀደስ ስምከ ፤ ትምጻእ መንግሥትከ ፤ ወይኩን ፈቃድከ፤በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ። ሲሳየነ ዘለለዕለትነ ሀበነ ዮም ። ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ፤ ከመንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ።ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ፤ አላ አድኅነነ፤ ወባልሐነ እምዙሉ እኩይ ።

እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት፤ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ሠ/ በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ፤ ድንግል በሕሊናኪ፤ ወድንግል በሥጋኪ ፤ እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላምለኪ ፤ቡርክት አንቲ እምአንስት፤ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ ።

ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ። ሰአሊ ወጸልዩ ለነ ምሕረተ ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ ።

## ረ/ ጸሎተ ሃይማኖት ፤

ነአምን በአሐዱ አምላክ፤እግዚአብሔር አብ አኀዜ ኵሉ ፤ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ።

ወነአምን በ፩ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ፤ ዘሀልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ፤ ብርሃን ዘእምብርሃን፥አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን ።



መ. አባታችን ሆይ !በሰማያት የምትኖር ፥ ስምህ ይቀደስ ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን ። የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ ። በደላችንንም ይቅር በለን፤ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል ። ወደ ፈተናም አታግባን ፤ከክፉ አድነን እንጂ ።

መንግሥት ያንተ ናትና፤ኃይል ምስጋናም ለዘለዓለሙ አሜን ፤

ሠ/ እመቤቴ ማርያም ሆይ ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ ። በሐሳብሽ ድንግል ነሽ ፤ በሥጋሽም ድንግል ነሽ ፤ የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ለአንቺ ይገባል ። ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ። ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ፤እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ። ከተወዳጁ ልጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታን ለምኝልን፤ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ።

## ረ/ የሃይማኖት ጸሎት ፤

ሁሉን በያዘ፥ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ።

ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር በነበረ የአብ ልጅ በሚሆን በ፩ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ፥



www.ethiopianorthodox.org

ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ፤ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ ። ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ፤ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ ። ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወ በእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት ። ተሰብአ ፤ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እ፝ቅድስት ድንግል ። ኮነ ብእሴ ፤ ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ ። ሐመ ፤ ወሞተ ፤ ወተቀብረ ፤ ወተንሥአ ሙታን እመ ሣልስት ዕለት ፤ በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት ።

ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ፤ ወነበረ በየማነ አቡሁ ።

ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ፥ ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ ።
ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረፀ እምአብ ፤

ንሰግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት ።

ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት ።

ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት ። ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ፤ ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም አሜን

ል/ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ እግዚአብሔር ጸባኦት ፍጹም ምሉእ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ ።



የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል፥ ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለርሱ ግንምንም የሆነ የለም ከሆነው ሁሉ ፤ በሰማይም ቢሆን በምድርም ቢሆን ።
ስለእኛ ስለሰዎች ፥ ስለመዳናችንም ከሰማይ ወረደ ፤ ከቅድስት ድንግድል ማርያም ተወለደ ።
ሰውም ሁኖ በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመን ስለኛ ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤ ሞተም ፤ ተቀበረም ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ ።

በክብር ወደሰማይ ዐረገ ፤
በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ።
ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ይመጣል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ።
ጌታና አዳኝ በሚሆን ከአብ በሠረጸ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ፤
እንሰግድለት ዘንድ፥ እናመሰግነውም ዘንድ፥ ከአብና ከወልድ ጋር ፥ በነቢያት የተናገረ ።
ከሁሉ በላይ በምትሆን፥ ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ።
ኃጢአትን ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ።
የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን ፤ የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ አሜን ።

ሰ/ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ ፍጹም የክብር ምስጋናህ ሰማያትንና ምድርን የመላ ፤



www.ethiopianorthodox.org

እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐተ ስግደተ ፫ (ጊዜ በል ) ።

እንዘ ፩·፫ቱ፣ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ፤ ይሤለሱ በአካላት፣ ወይትዋሐዱ በመለኮት ።

እሰግድ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ።

እሰግድ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተቀደሰ በደሙ ክቡር ።

መስቀል ኃይልነ ፤ መስቀል ጽንዕነ ፤
መስቀል ቤዛነ ፤ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ ፤
አይሁድ ክሕዱ ንሕነሰ አመነ ወእለ አመነ በኃይለ መስቀሉ ድኅነ ።

ቂ/ ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ (፫ ጊዜ በል) ።

ስብሐት ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ። ስብሐት ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ክርስቶስ በምሕረቱ ይዘከረነ ። አመ ዳግም ምጽአቱ ኢያስተኀፍረነ ።
ለስብሐተ ስሙ ያንቅሐነ ፤
ወበእምልኮቱ ያጽንዐነ ።
እግዝእትነ ማርያም አዕርጊ ጸሎተነ
ወአስተሥርዪ ኃጢአተነ ፤ ቅድመ መንበሩ ለእግዚእነ ።
ለዘአብልዐነ ዘንተ ኅብስተ ፤
ወለዘአስተየነ ዘንተ ጽዋዐ ።



ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም አንዲት ስግደትን እሰግዳለሁ ፤ (፫ ጊዜ በል) ።
አንድ ሲሆን ሦስት፣ሦስትም ሲሆኑ አንድ የሚሆን ፤ በአካላት ሦስት ሲሆኑ በመለኮት አንድ ናቸው ።
ለአምላክ እናት ለእመቤታችን ለቅድስት ማርያም እሰግዳለሁ ።
ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እሰግዳለሁ በከበረ ደሙ ለተቀደሰው ።

መስቀል ኃይላችን ነው ፤ መስቀል ጽናታችን ነው ። መስቀል ቤዛችን ነው ፤ መስቀል የነፍሳችን መድኃኒት ነው ።
አይሁድ ካዱ እኛ ግን አመን ፤ ያመን እኛም በመስቀሉ ኃይል ዳን ።

ቀ/ ለአብ ምስጋና ይገባል ፤ ለወልድም ምስጋና ይገባል ፤ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል ። (፫ ጊዜ በል) ።
አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም ምስጋና ይገባል ።
ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ምስጋና ይገባል ።
ክርስቶስ በምሕረቱ ያስበን ።
በ፪ኛ ጊዜ መምጣቱም አያሳፍረን ።
ስሙን ለማመስገን ያንቃን ።
በአምልኮቱም ያጽናን ።
እመቤታችን ማርያም ጸሎታችንን አሳርጊ ፤ ኃጢአታችንንም አስተሥርዩ በጌታችን መንበር ፊት ።
ይህን ኅብስት ላአበላን ፣ ይኸንንም ጽዋዕ ላአጠጣን ።



www.ethiopianorthodox.org

ወለዘሠርዐ ለነ ሲሳየነ ወአራዝነ ፤
ወለዘተዐገሠ ለነ ኵሎ ኃጢአተነ ።
ወለዘወሀበነ ሥጋሁ ቅዱሰ ወደሞ ክቡረ ። ወለዘአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት ።

ነሀብ ሎቱ ስብሐተ ወአኰቴተ ለእግዚአብሔር ልዑል ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር ። ይትአኰት ወይሰባሕ ስሙ ለእግዚአብሔር ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ። ፤

## ፪ ጸሎተ ማዕድ

በማንኛውም ጊዜ ለምግብ በተቀመጥክ ጊዜና ምግብህንም በፈጸምክ ጊዜ ምስጋና ለእግዚአብሔር ለአምላክህ አቅርብ ፤ ከምግብ በፊትና በኋላ የምትለው እንደሚከተለው ተለይቶልሃል ) ።

### ሀ/ ቅድመ መብልዕ

(ይበሉ በኅብረት)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ
ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን ።

(ይበል በዓለ ቤት)

እግዚአብሔር አምላክነ ወፈጣሪነ
ዘትሁብ ሠናያቲክ ለኵሉ ፍጥረት ።
እኩት አንተ ወስቡሕ ስምከ ፤
ወንሕነኒ ነአኵተከ ወንሴብሐከ በእንተ ፍጹም ጸጋከ ። ዓይነ ኵሉ ነፍስ ይሴፎ ኪያከ ፤ እስመ አንተ ትሁብ ሲሳየ ለኵሉ በጊዜሁ ፤ ትሰፍሕ የማነከ ወታጸግብ ኵሎ ።



ሲሳያችንንና ልብሳችንን ለአዘጋጀልን፣ኃጢአታችንንም ሁሉ ለታገሠን ፥ ቅዱስ ሥጋውንና የከበረ ደሙን ለሰጠን ፥ እስከ ዚችም ሰዓት ለአደረሰን ።

ፍጹም ምስጋናን እንዕጠው ለልዑል እግዚአብሔር ለወለደችውም ድንግል ፤ ለክቡር መስቀሉም ፤

የእግዚአብሔር ስም ፈጽሞ ይመስገን ዘወትር በየጊዜው ሁሉና በየሰዓቱም ሁሉ ።

## ፪ / የማዕድ ጸሎት

### ሀ/ ከመብል በፊት

(ሁሉም በኅብረት ይበሉ) ።

በአብ፣በወልድም ፥ በመንፈስ ቅዱስም ስም ፩ አምላክ አሜን ።

(በዓለ ቤት ይበል) ።

ጸጋህን ለፍጥረቱ ሁሉ የምትሰጥ አምላካችንና ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አንተ ምስጉን ነህ ፤

ስምህም የተመሰገነ ነው ፤ ስለሰጠኸን ፍጹም ጸጋህ ፈጽመን እናመሰግንሃለን ። የፍጥረት ሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል ።

አንተ በየጊዜው ለሁሉ ምግብ ትሰጣለህና ፤ ቀኝህን ትዘረጋለህ ፤ ሁሉንም ታጠግባለህ ።



www.ethiopianorthodox.org

ወይእዜኒ አምላክነ ሰፋሕ የማነከ ቅድስተ፤ ወባርክ ዘንተ መብልዐ ወመስቴ ዘአስተዳለውከ ለነ ከመ ይኩን ኃይለ ወጽንዐ ለሥጋነ ወለነፍስነ እስመ አንተ ኄር ወምእመን መጋቢ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

## ለ/ ድኅረ መብልዕ

፩/ (እምነ ቤተ ሰብእ ይበል ዘንተ) ስብሐት ለአብ ፣ ስብሐት ለወልድ ፣ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ። ለዘአብልዐነ ዘንተ ኅብስተ ፣ ወለዘአስተየነ ዘንተ ጽዋዐ፣ ወለዘሦርዐ ለነ ሲሳየነ ወዐራዘነ፣ ወለዘተዐገሠ ለነ ኵሎ ኃጢአተነ ፣

ወለዘ አድኀነነ እሞት፤ ወለዘአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት ።

(ወይበሉ ኵሎሙ ኅቡረ)

ነሀብ ሎቱ ስብሐተ ወአኰቴተ -
ለእግዚአብሔር ልዑል ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ

ሰዓት ። አሜን ፤

አቡነ ዘበሰማያት) ።



አሁንም አምላካችን የተቀደሰች እጅህን ዘርጋንና ይህ ንንም ያዘጋጀኸልንን ምግብና መጠጥ ባርክ ለሥጋ ችንና ለነፍሳችን ኃይልና ጥናት ይሆነን ዘንድ። አንተ ቸር የታመንክም መጋቢ ነህና ለዘለዓለሙ አሜን ።

## ለ/ ከምግብ በኋላ

(ከቤተሰብ አንዱ ይኸንን ይበል) ።
ምስጋና ለአብ ፣ ምስጋና ለወልድ ፣ ምስጋና ለመን ፈስ ቅዱስ ይገባል ።

ይኸንን ምግብ ላበላን፣ ይኸንንም ጽዋዕ ላጠጣን ፣ ምግባችንና ልብሳችንን ለሠራልን ፣ ኃጢአታችን ንም ለታገሠልን ።
ከሞትም ላዳነን እስከዚህ ሰዓትም ላደረሰን ፤

(ሁሉም በኅብረት ይበሉ)
በየጊዜውና በየሰዓቱ ዘወትር ለልዑል እግዚአብ ሔር ፍጹም ምስጋና እንስጠው ። አሜን ፤

(አባታችን ሆይ) ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፫/ የሠርክ ጸሎት ።

ሀ/ በስመ አብ - - - ። ለ/ ነአኩተከ - - - ።

ሐ/ ቀዳማዊ አምላክ፣ደኃራዊም የምትሆን፣ለብቻህ ቅዱስ ኀያል የምትሆን ሁሉን የፈጠርክ ሁሉንም የምትመግብ አንተ መሆንህን አምናለሁ ። ስለዚህ አሁንም ምስጋናን ለአንተ ብቻ አቀርባለሁ።ዕለቱም፣ሰዓቱም፣ደቂቃውም የአንተ ገንዘብ ነው ፤ ለእኔም እጠቀምበት ዘንድ በነጻ አደልከኝ። አምላክ ሆይ! ይኸን ሁሉ ከሰፊ ቸሮታህ የተነሣ እንዳደረግኸው አምናለሁ ፤ ስለዚህም ለአንተ ብቻ ምስጋናን ዝማሬንም!አቀርባለሁ።እንዲሁም የጸጋ ሁሉ መገኛ አንተን እማልዳለሁ፤እለምናለሁም፤መዓልቱን ባርከህ በሰላም እንዳዋልከኝ፣ይኸንም ምሽት እንድትባርክልኝ፣በሰላም አሳልፈውም ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልኝ።

እምልኮት፣ ስግደት ፤ክብርም፤ ምስጋናም ለአንተ ለቸሩ አምላክ ይሁን ። ለዘለዓለሙ አሜን ።

አቡነ ዘበሰማያት ። - - - - - አባታችን ሆይ ።

## ፬/ የንዋም ጸሎት ።

ሀ/ በስመአብ ።
ለ/ ነአኵተከ ።

ሐ/ የሕይወት ራስ የሆንክ አምላኬ እግዚአብሔር! ለሰው ልጅ ስለሠራኸውና ስለምትሠራው በጎ አድራጎት ሁሉ አመሰግንሃለሁ ።

ለሰው ልጅ በምድር ላይ ሥልጣንን ሰጠኸው፤ በዚህም መሠረት እኔም ከሰጠኸው ጥቅም ስካፈልና ስሠራም ዋልኩኝ ፤ ሥራዬንም ፈጽሜ ወደቤቴ በሰላም ገባሁ ፤ ዕረፍትም አገኘሁ ፤ ይኸም ሁሉ ጥጹም ጸጋሀ እንደሆነ አምናለሁ ።

አሁንም አምላክ ሆይ! ሌሊቱን፣ ጨለማውንም ባርክልኝ ፤ በሰላምም አሳልፈው ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልኝ ።

የሕይወትም እንቅልፍ አድርግልኝ ፤ በጧትም በሰላምና በሕይወት እነቃ ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልኝ ፤ የሞት እንቅልፍ እንዳላንቀላፋ በመላእክትህ እጠበቅ ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልኝ ።

ሁሉን የሰጠኸኝ አምላክ፣ በሰላም አሳድረኸ የነገ ሰው አድርገኝ ። የመዓልቱን ብርሃን አይ ዘንድ አድለኝ ፤ ኃይል ጽንዕ ገንዘብህ የሆነ አምላክ አንተ ነህና ስግደት ለአንተ ይገባል ፤ አምልኮትም ለዘለዓለሙ አሜን ።

አቡነ ዘበሰማያት - - -

## ፭/ ጸሎተ ቅዳሴ ።

፩/ ጸሎተ ቅዳሴ ማለት ካህኑ ኅብስቱን በጻሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ በሚያከብርበት ጊዜ የሚጸለየው ጸሎት፣ የሚቀርበውም ምስጋና ነው ።

፪/ ጸሎተ ቅዳሴው ለምእመናን ድኅነት ተብሎ እንደሚደረግ አምናለሁ ፤ ስለዚህ የጸሎተ ቅዳሴው ተሳታፊ መሆን ግዴታዬ እንደሆነ አውቄ ይኸንኑ እፈጽማለሁ ።

፫/ ጸሎተ ቅዳሴው ሲጀመር ተገኝቶ እስከ ቅዳሴው ፍጻሜ ቆሞ ማስቀደስ ተገቢነቱን አምናለሁ ፤





www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ጸሎተ ቅዳሴውን አቋርጦ መግባት በተለይም አቋርጦ መውጣት ታላቅ ድፍረት መሆኑን ተረድቼ በደጀጠኝነት ቀደም ብሎ መገኘቱን አምናለሁ ።

፬/ የቤተ ክርስቲያን አባልነቴን በቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት ሁሉ እየተገኘሁ ማስመስከር እንዳለብኝ አምናለሁ ። ስለዚህ ሁልጊዜ በቤተ ክርስቲያን ጸሎት ሁሉ በተለይም በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ መገኘት ግዴታዬ መሆኑን አምናለሁ ።

፭/ በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ ቁሞ ማስቀደስ፤ተስጥዎውንም መቀበል ተገቢ መሆኑን አምናለሁ ። ስለዚህ ሁልጊዜ በየበዓላቱ በየቤተ ክርስቲያኑ መገኘትና ማስቀደስ ግዴታዬ ነው ።

፮/ በቤተ ክርስቲያኑ ተገኝቶ የጸሎቱ ተሳታፊ መሆን ተገቢነቱን አምናለሁ፤ጸሎተ ቅዳሴውም እያንዳንዱ ክፍል ተሳታፊ በሚሆንበት መልክ የተዘጋጀ ነው ፤ ይኸውም ይበል ካህን ፣ ይበል ዲያቆን ፣ ይበል ሕዝብ እያለ ሲያውጅ የሕዝቡ ወገን እንደመሆኔ እኔን የሚመለከተውን መፈጸም አለብኝ ።

፯/ በጻሕሉ የቀረበው ኅብስት በጽዋውም የቀረበው ወይን በካህኑ ጸሎትና ምልጃ በእግዚአብሔርም ቃል ተለውጦ ኅብስቱ ፍጹም ሥጋ መለኮት፣ ወይኑም ፍጹም ደመ መለኮት እንደሚሆን አምናለሁ።

፰/ ማንም ሰው ከክርስቶስ ሥጋ ካልበላ ፣ ከደሙም ካልጠጣ ተዋሕዶት የሚኖር ሕይወት እንደሌለው አምናለሁ ፤ ስለዚህ በየጊዜው ከሥጋው እበላለሁ ፤ ከደሙም እጠጣለሁ ።



፱/ ቍርባን በየጊዜው መሆን እንደሚገባው ክርስቶስ ሲያስተምር «ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜን የሚጠጣ «የዘለዓለም ሕይወት አለው» ብሎ እንደተናገረ አምናለሁ ። ስለዚህ ጸሎተ ቅዳሴው በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ከቅዱስ ሥጋው እበላለሁ ፤ ከክቡር ደሙም እጠጣለሁ ።

## ክፍል ፬ ስለ ጾም ና ምጽዋት

፩/ ጾም፣ጾም ማለት ለቅዱስ አምላክ ተገዥነትን ለመግለጥ ፣ አምልኮትም ለማቅረብ ሲል ፩ ሰው ከመብልና ከመጠጥ ፣ እንዲሁም ከሚወደው ነገር ሁሉ መራቅ፣ ከእርሱም መከልከል እንደሆነ አምናለሁ ፤ ስለዚህ ፈቃደ ነፍስን ለመከተል ከፈቃደ ሥጋ ለመራቅ ጾም አስፈላጊ በመሆኑ እንደ ትእዛዙ እፈጽማለሁ ።

፪/ ጾም የማንኛውም ሰው ውሳጣዊ አምልኮትና እምነት መግለጫ ትሩፋት ነው ፤ ስለዚህ እኔ ብየጊዜው ከመብልና ከመጠጥ እከለከላለሁ እጾማለሁም፤ በበለጠ ግን ክፉ ከማየትና ከመስማት ክፉ ከማሰብና ከመናገር መከልከል ይገባኛል ።

ረቂቁን አምላክ ለመዋሐድ በጾም በትሕርምት መኖር፣ ከፈቃደ ሥጋም ሁሉ ተለይቶ መገኘት አስፈላጊ መሆኑን አምናለሁ ።

፫/ በመብልና በመጠጥ ልቡናውን አደንድኖ፣ አእምሮውን አፍዝዞ፣ ሕገ እግዚአብሔርን አፍርሶ መኖሩ የተፈጠረበትን ዓላማ እንደለወጠ የሚያስ



www.ethiopianorthodox.org

ቍጥር ነው ፤ ስለዚህ ሥጋዊ ስሜቱን ገቶ፥በፈቃደ ነፍሱ ጸንቶ ለመኖር ጾም በግድ ያስፈልጋል ። ሉቃ ፳፩ ፥ ፴፬—፴፮) ።

፰፤በመብልና በመጠጥ ፈንታ መንፈስን ለመሙላት ጾም አስፈላጊ መሆኑን እምናልሁ ። ስለዚህ ሊበላውና ሊጠጣው ይገባው የነበረውን ለችግረኞች ሰጥቶ፥እርሱ በመንፈስ ተሞልቶ ይኖራል ።

## ለ/ ምጽዋት

፩/ ከአምላክ ዋጋውን እንደሚያገኝ አምኖ ሳያመነታ ከሀብቱና ከንብረቱ ለችግረኞች መስጠት፥ ራሱን ስለሰው ልጅ ሕይወት ማስቸገር ክርስቲያናዊ ተግባር መሆኑን እምናለሁ ። ስለዚህ ሀብት ሁሉ ኃላፊ መሆኑን ተረድቶ ኃላፊው ሰው ዓለሙን ቢይዝ፥ ሁሉንም ቢገዛ፥ገንዘቡም ቢያደርግ የሚጠቅመው እንደሌለ አውቆ ከአለው ሀብቱ ውስጥ ምጽዋት መስጠት በሰማይ መዝገብ ማጠራቀም ነው (ሉቃ. ፲፪.፴፫) ።

፪/ አንድ ሰው ለነፍሱ ቤዛ ለማግኘት ምን ቢያደርግ ምንስ ቢከፍል ይበጀዋል ፤ ለድሆች፥ለችግረኞች ከገንዘቡ ምጽዋት የሰጠ ችግረኞችንም የረዳ እንደሆነ ለነፍሱ ቤዛ ይሆንለታል ፤

፫/ ምጽዋት ለሰጡ፥ ችግረኞችን ለረዱ ሰዎች ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀውን መንግሥቱን አምላክ እንደሚያወርሳቸው፥ በግርማ መጥቶ ኃጥአንን በሚወቅስበት ዕለት የምስጋና ቃልን እንደሚያገኙ ክርስቶስ ተናግሯል ። (ማቴ. ፳፭.፴፬—፵) ።



፬/ ምጽዋትም ምግብ፥መጠጥ በመስጠት፥ወርቅ፥ብር፥ ማንኛውንም ገንዘብና ልብስ በመስጠት ይፈጸማል ፤ ግን ይኸም ላለው ሰው እንጂ ድሀም በጉልበቱ ፣ ምሁሩ በማስተማሩ ፣ ሌላውም እንዲሁ በተቻለው ሰውን ከረዳ ምጽዋት ይሆናል ፤ ምጽዋትም ይባላል ።

# ክፍል ፮ ስለ በዓላት

## ሀ/ የሰንበት ክብር

፩/ ሰንበተ ክርስቲያን የምትባለው እሑድ ስለ ሆነች እርሷን የዕረፍት ዕለት አድርጎ፥አክብሮ መዋል አስፈላጊ መሆኑን እምናለሁ ። ይኸችም ዕለት የጌታ ዕለት እንደሆነች ወንጌላዊ ዮሐንስ ያስረዳል ። (ዮሐ.ራእ.፩.፲) ።

፪/ የሰንበት በዓልም አከባበር ተኝቶ በመዋል አይደለም ፤ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት በማስማትም፥ ክርስቲያናዊ በጎ አድራጎትንም በመፈጸም መሆኑን እምናለሁ ።

፫/ ሰንበተ ክርስቲያን በሰንበተ አይሁድ እግር የገባች መሆኗን እምናለሁ ። ስለዚህ እንደ ክርስቲያንነቴ በቤተ ክርስቲያን በመገኘት ጸሎተ ቅዳሴውን በመከታተል በጎ አድራጎትንም በመፈጸም አከብራለሁ ።

## ለ/ በዓለ ማርያም

፩/ የቅድስት ማርያም መታሰቢያ ዕለታት የሆኑትን በሚገባ አከብራለሁ፤በነዚህም ዕለታት የእር



www.ethiopianorthodox.org

ሷን የሕይወት ታሪክ በመንገር፥ በመስማት ማሳለፍ ተገቢ መሆኑን እምናለሁ ።

፪/ የቅድስት ማርያምን መታሰቢያ ዕለታት ስና ክብር የአምላክን ምሕረትና ቸርነት የቅድስት ማር ያምን ክብርና ወላዲተ አምላክ መሆኗን በመረዳት፥ የዘለዓለም ክብርን ለማግኘት፥ በቃል ኪዳኗም በመ ማጸን ነው ።

፫/ የቅድስት ማርያምን መታሰቢያ ዕለት አከ ብራለሁ ፤ በቃል ኪዳኗም እማጸናለሁ ፤ ምስጋና ዋንም እናገራለሁ ።

## ሐ/ የቅዱሳን መላእክት በዓል ።

፩/ ቅዱሳን መላእክት የአምላክ ባለሟሎች፥ የሰውም ባለውለታዎች ስለሆኑ ክብር ይገባቸዋል ፤ ስለዚህም ቃል ኪዳን የተቀበሉበትን፥ተአምራትም የሠሩበትን ዕለት መታሰቢያ በማድረግ አከብራለሁ፤ ምስጋናም አቀርባለሁ ።

፪/ መላእክት የሰው ጠባቂዎች መሆናቸውን እምናለሁ (ማቴ-፲፰-፲) ። እንዲሁም የአምላክ መል እክተኞች ናቸው፤ስለዚህ እንደባለሟልነታቸው እንደ አገልግሎታቸውም ክብር ይገባቸዋል ።

## መ/ የልዩ ልዩ ቅዱሳን በዓል ።

፩/ አምላክ የቀደሳቸውን፥ ቃል ኪዳን የገባላ ቸውን ቅዱሳንን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ታከብራለች ። ስለዚህ የተወለዱበትን ፥ ያረፉበትን ፥ አንዳንድ ተአምራትም ያደረጉበትን ዕለት በማክበር እነርሱን በማመስገን ፥ ዝናቸውን በመንገር እናሳልፋለን ።



፪/ ቅዱሳን የሚባሉ ከሐዋርያት ጀምሮ ጻድቃን ሰማዕታት ደናግል ሌሎችም በጾታ በዕድሜ፥በኃላ ሳይወሰኑ፥የቅድስና፥የቢዕዐና ማዕርግ የተሰጣቸው ሁሉ ናቸው ። ስለዚህ የሁሉንም መታሰቢያ አከብ ራለሁ፡-ስማቸውንም እጠራለሁ፤በቃል ኪዳናቸውም እማጸናለሁ ።



www.ethiopianorthodox.org

# ዐቢይ ክፍል ፪

## የቅዱስ መጽሐፍ ጥናት

### መ ቅ ድ ም ፤

ቅዱስ መጽሐፍ ወይም በብዙ ቍጥር ቅዱሳት መጻሕፍት ፥ ወይም መጻሕፍት አምላካውያት ብለን የምንጠራቸው ቤተ ክርስቲያናችን ከመሠረቱ የተቀበለቻቸውን፥የእውነት ምንጭ የሆኑትን ፥ በመላ በመንፈሰ እግዚአብሔር የተጻፉትን መጻሕፍት ነው ፤ እነዚህም መጻሕፍት በሃይማኖትና በሥነ ምግባር የሰው ልጅ ሁሉ እንዲታነጽባቸው፥በነዚህም መመሪያነት ጸንቶ ይኖር ዘንድ አምላክ በጽሑፍ ለሰው ልጅ ያስተላለፋቸው ናቸው ።

እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡን በተለያየ ጊዜና በተለያየ መልክ ጐብኝቶታል፤ይኸም ማለት በጥንት ዘመን በ፩ አምላክ የሚያምኑትን የእግዚአብሔርምርጥ ሕዝብ እየተባሉ የሚጠሩትን ፳ኤልን ጐብኝቷል ፤ ለጊዜው ለነርሱ መመሪያ መማሪያም የሚሆነውን ሕግ ሰጥቷል፤ከሕዝቡም ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል ። ይኸም ብሉይ ኪዳን ተብሎ የሚጠራው ነው ።

እንዲሁም፥ በፍጻሜ ዘመን አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፥ከድንግል ማርያም ተወልዶ፥ሕጉን አድሶ ሌላ አዲስ መመሪያ አዲስ መማሪያ ለአዲሱ ፳ኤል ዘነፍስ ሰጥቷል ፤ ይኸም ሐዲስ ኪዳን ይባላል ። እነዚህ ሁለቱ ኪዳኖች ሲገናኙ በ፩ ጥራዝም ሲጠረዙ በ፩ ስም ቅዱስ መጽሐፍ የሚባለውን ስም ለማግኘት ችለዋል ።

ይኸ ቅዱስ መጽሐፍ የሰው ልጅ የሆነው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ ያውቅበት፥ወደ ሥነ ምግባርም በትክክል ይመራበት ዘንድ ከታላቁ አምላክ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሁሉ ተሰጠ ። በዚህ ቅዱስ መጽሐፍ አማካይነት የሚመራ ይኸንም ቅዱስ መጽሐፍ ዘወትር በጧትና በማታ በመዓልትና በሌሊት የሚያነብ ሁሉ ችግርአይገጥመውም።እንዲያውም በወንዝ ዳር እንደተተከለች፥ፍሬዋንም በየጊዜው እንደምትሰጥ ዛፍ ይሆናል ፤ ማለት ሁል ጊዜ ፍሬ ትሩፋት፥ፍሬ ክብርንና ምግባርን ያፈራል ( መዝ.፩.፫) ።

ስለዚህ የሰው ልጅ ሁሉ የቅዱስ መጽሐፍ ባለቤት ይሆን ዘንድ ፥ ቅ/ መጽሐፍን በተለየ ጥንቃቄ ያጠና ዘንድ፥ከልጅነትም ዕድሜ ጀምሮ በዚህ መልክ ይማር ዘንድ የተለየ ዝግጅት ተደርጎ በዚህ መልክ ሊቀርብ ቻለ ።

ማንኛውም ነገር ከሥሩ ከመሠረቱ ማለት ከሕፃንነቱ የተለመደ እንደሆነ በአደገ ጊዜ ልማዱ ወደ ሥነ ምግባር ይመራዋል ፤ የቅዱስ መጽሐፍ ማንበብ ፍላጎት በልቦናው ይሰፍናል፤ስለዚህ ሁል ጊዜ ወደ ቅዱስ መጽሐፍ ያዘነብላል ።

እንግዲህ ማንኛውም ሰው በሚቀጥለው መልክ ቅዱስ መጽሐፍን ወደ ማጥናት እንዲመለስ እያስገነዘብኩ ይችን መጽሐፍ አዘጋጅቼ አቀርባለሁ ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ፤





www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፩ ቅዱስ መጽሐፍ ።

ቅዱስ መጽሐፍ ማለት ከሌላው መጽሐፍ ሁሉ የተለየ የተቀደሰ ፣ የከበረ መጽሐፍ ማለት ነው ።

ይኸ ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ ስለሆነ ዘመን አይሽረውም ፤ ዓላማውንም ጊዜ አይለውጠውም ፤ ጥቅሙም ለተወሰነ ማኅበር ወይም ለግል ሰው አይደለም፤ዓላማው ቀዋሚ የሆነ ሕጋዊ መጽሐፍ ነው።በቅዱሱ አምላክ ወደ ሰው የተላለፈ ስለሆነ ቅዱስ የሚለውን ስም ገንዘቡ አደረገ ።

ይኸ ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ለሰው ልጅ ይገልጻል ፤ በዚህም መጽሐፍ አማካይነት የእግዚአብሔር ባሕርይ ምን እንደሆነ እኛ እናውቅበታለን ፤ ስለዚህ የመጽሐፉ ዓላማ ቅዱስ ስለሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ይባላል ።

በዚህ ቅዱስ በተባለ መጽሐፍ በልዩ ልዩ ቅዱሳን ሰዎች የተጻፉ መጻሕፍት የነርሱን ስም ተሸክመው የሚገኙ ክፍላት፣ስለ አሉበት፣እነዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት ተብለው ይጠራሉ ። እንዲሁም መጻሕፍት አምላካውያት ተብለው ይጠራሉ ፤ይኸ ማለት በተለያዩ ሰዎች ቢጻፉም በነርሱም ስም ቢጠሩም ያጻፈው ፣ ምሥጢሩንም የገለጠው አምላክ ስለሆነ የአምላክ መጻሕፍት ወይም የአምላክ ገንዘብ የሆኑ መጻሕፍት ለማለት ይኸንን ስም አግኝተዋል ፤ ግን በአጠቃላይ ቅዱስ መጽሐፍ ተብሎ ይጠራል፤ቅዱስ ስም መጽሐፍ ነው ።



## ምዕራፍ ፪ ቅዱስ መጽሐፍ የአምላክ ስጦታ መሆኑ ፡

ቅዱስ መጽሐፍ ለሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትልቅ ስጦታ ነው ፤ ይኸውም እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ስለወደደ ህልውናው የሚታወቅበትን ፣ ቅዱስ ፈቃዱ የሚገለጥበትን ፣ ረቂቅ ባሕርዩ ፀመጠኑም ቢሆን የሚረዳበትን አምላክ ለሰው ልጅ አስተላለፈ ።

አንድ ሰው ሌላውን ባልንጀራውን ሲወድ የፍቅር መግለጫ ይሆን ዘንድ የስጦታ ልውውጥ ያደርጋል፤ይኸውም ሁለቱም ወገን እውነተኞች፣ፈሊጠኞች ሰዎች የሆኑ እንደሆነ ፍቅራቸውም ልባዊ የሆነ እንደሆነ ነው ። እንዲሁም አምላክ ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ ለሰው ልጅ ይኸን ቅዱስ መጽሐፍሲያበረክት፣ የሰው ወገን ደግሞ በአምላኩ ያለውን ፍቅር ለመግለጥ ሲል ስጦታውን አክብሮ ይቀበላል ፤ ከፍቅሩም ጽናት የተነሣ እንደ ስጦታ አድርጎ በሕግ ጠባቂነት በትእዛዝ አክባሪነት ይቀርባል ።

ቅዱስ መጽሐፍ ለሰው ልጅ ሁሉ የተሰጠ በመሆኑ የዕድሜ ፣ የጾታ ፣ የጎሣ ፣ የቀለም ፣ የቋንቋ ልዩነት ሳያደርግ ሁሉን የሚመለከት ፣ ለሁሉም የሚሆን መጽሐፍ ነው ።

እግዚአብሔር የሁሉ አምላክ ስለሆነ ለማንም አያዳላም ይኸንኑ ቅሉ የምንረዳው በዚሁ እርሱ በሰጠው ቅዱስ መጽሐፍ አማካይነት ነው ።

በመጀመሪያውም የሰው ልጅ ከአንድ ምንጭ የተቀዳ ፣ አንድ ዘር ስለሆነ አምላክ ለሁሉም ትክክል ነው ፤ ሁሉንም በትክክል ያስተዳድራል ።



www.ethiopianorthodox.org

የሰውን ዘር አንድነት ፣ የሰውን ልጅ እኩልነት ሳይቀር የሚያስረዳ ይኸው ቅዱስ መጽሐፍ ነው ። እንግዲህ በአሁኑ ጊዜ በልዩ ልዩ መልክ የሚገኘውን ሰው አንድ የሚያደርገው የሚያገናኘው ይኸው ፩ዱ መጽሐፍ ነው ፤ ሁሉን ያረካ ዘንድ በሚችል መንፈስ ተጽፎ ለሁላችን ተላልፎ ይገኛል ።

## ምዕራፍ ፫ ቅዱስ መጽሐፍ እስትንፋሰ እግዚአብሔር መሆኑ

ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔር ይባላሉ ፤ ምክንያቱም ልዑል አምላክ መንፈሱን በነቢያት እያሳደረ አጽፎታልና ።

ቅዱስ ጳውሎስ ለሃይማኖት ልጁ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ፣ ልብንም ለማቅናት ፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» ሲል መጻሕፍት ሁሉ በመንፈስ እግዚአብሔር መጻፋቸውን ፣ መጻሕፍት ሁሉ እስትንፋሰ እግዚአብሔር መሆናቸውን ይናገራል (፪ ጢሞ፣፫፣፲፮) ።

መጽሐፍ ሁሉ የሚለው ቃል ቅዱስ መጽሐፍን በአጠቃላይ የሚመለከት መሆኑን፣ ስለርሱም መናገሩን ያስረዳል ። ይኸንንም አስተያየት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሁሉ ተስማምተው ይደግፉታል ። ቅዱስ መጽሐፍ በመንፈስ እግዚአብሔር መጻፉን ፣ ማንም በራሱ ፈቃድ የጻፈው አለመሆኑን ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ንባቡንም ምሥጢሩንም አጉልቶ «ይኸን በመጀመሪያ ዕወቁ ፤ በመጽሐፍ ያለውን



ትንቢት ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ፤ ከቶ ትንቢት በሰው ፈቃድ አልመጣምና ፤ ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተረድተው ተናገሩ እንጂ»ሲል ያስረዳናል ። ( ፪ ጴጥ.፩ ፳-፳፩ )።

ነቢያት ትንቢትን ከልባቸው አንቅተው፣ ከአእምሮአቸው አውጥተው አልተናገሩም፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ሁነው ፣ በእግዚአብሔርም መንፈስ ብቻ ተመርተው ተናገሩ ፣ ጻፉም እንጂ ።

እንግዲህ ቅዱስ መጽሐፍ በመንፈስ እግዚአብሔር የተጻፈ ስለሆነ ፍጹም እውነት ነው፤ ከቶ ሊለወጥ፣ ሊጨመርበትም፣ ሊቀነስበትም የማይገባ መጽሐፍ ነው (ማቴ.፭.፲፰) ።

ስለ ሐዲስ ኪዳንም ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታ ያዩትን፣የሰሙትን፣የተማሩትን፣አሁንም በመንፈስ እግዚአብሔር እየተመሩ የጻፉ እንጂ ከራሳቸው አውጥተው፣ከልባቸው አንቅተው የተናገሩት፣የጻፉት ከቶ የላቸውም ።

ሐዋርያት ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመሩ የሚናገሩ የሚሠሩ ለመሆናቸው ጌታ ሲመሰክርላቸው «የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁም፤ የአባቴ መንፈስ እንድትናገሩ ያደርጋችኋል እንጂ» ብሏል (ማቴ.፲.፳) ።

እንግዲህ በአጠቃላይ ቅዱስ መጽሐፍ በመንፈስ እግዚአብሔር የተጻፈ ስለሆነ ቅዱስ መጽሐፍ



www.ethiopianorthodox.org

እንለዋለን ፤ ቅዱስ መጽሐፍም አድርገን እንቀበለ ዋልን ።

## ምዕራፍ - ፬- የቅዱስ መጽሐፍ ቍጥርና ተራ ።

ቅዱስ መጽሐፍን ቀደም አድርገው ከተቀበሉት አገሮች አንዲቷ ቅድስት አገራችን ኢትዮጵያ ናት ፤ ስለዚህም በቍጥር በርከት ያሉ መጻሕፍትን ተቀብ ለን ይዘን እንገኛለን ፤ እነዚህም መጻሕፍት ቀደም ብለው ወደ ቋንቋችን ተተርጉመው በትምህርት ፥ በጉባኤ ውስጥ ተገኝተዋል ።

በቍጥሩም ውሳኔ ላይ ብዙ ውይይት ተካሂ ዶበታል ።

ስለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፹፩ ቅዱሳት መጻሕፍትን ትቀበላለች ።

የነዚህንም መጻሕፍት ቍጥር ብሉይን በምንዘ ረዝርበት ጊዜ ከነስማቸው የብሉያትን ቍጥር ሐዲስ ኪዳንን በምንዘረዝርበት ጊዜ የሐዲስ ኪዳን መጻ ሕፍትን ቍጥር እንናገራለን ።

## ምዕራፍ ፭. ቀኖና ቅዱስ መጽሐፍ ፤

ቅዱስ መጽሐፍ እስትንፋስ እግዚአብሔር ስለ ሆነ ቤተ ክርስቲያን በሕጋዊነት ስትቀበለው ቀኖ ናንነቱን አምና ነው ።

የቅ.መጽሐፍ ቀኖናነቱን የሚያረጋግጡ ብዙ ዎች መረጃዎች አሉ ፤ እነዚህም በቍጥር የተወሰኑ ስለሆነ ።

፩/ የተራው ቅደምና ተከተሉ ስለተጠበቀ ፥
፪/ የትርጉሙ ትክክለኛነት ስለታመነበት ፥



ሌላም ይኸን የመሰለ ምስክር ስላለበት የተቀበሉና ቸው መጻሕፍት ሁሉ ቀኖና እንደሆኑ አምነን ነው ።

ቅዱስ መጽሐፍ ቀኖና ከሆነ ዘንድ ባዕድ ነገር አይገባበትም ፤ አንድ ነገርም አይቀነስበትም ፤ ስለዚህ የጸና ሁኖ ይኖራል ።

በዚህ ቅዱስ መጽሐፍ የተመሠረተው እምነት እውነተኛ ኦርቶዶክስም ነው ፤ ስለዚህ ለዘለዓለሙ የማይናወጥ ፥ የማይለወጥ እምነት ሁኖ ይኖራል ።

## ምዕራፍ ፮ የሁለቱ ኪዳናት ግንኙነት ፤

ቅዱስ መጽሐፍ በአንድ ስም ሲጠቃለል የሚ ጠራበትን ስም በመናገር ቅዱስ መጽሐፍ አልን እንጂ በኪዳንነቱ የሄድን እንደሆነ በ፪ ይከፈላል ፤ ይኸ ውም ብሉይ ኪዳን ፥ ሐዲስ ኪዳን የሚለው ነው ። ብሉይ ኪዳን የሚለው ስም የኪዳኑን ጥንታዊነት፥ ቀደምትነት ያመለክታል ፤ ምክንያቱም ቀደም ብሎ አምላካችን እግዚአብሔር ለአባቶች ቃል ኪዳን ገብቶ ፥ መሐላ ምሎ ነበርና ያን ይመለክታል ።

ሁለተኛው ክፍል ሐዲስ ኪዳን የተባለው ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ በፍጻሜ ዘመን ሰው ሁኖ ሥጋንም ለብሶ፥ በዚህ ዓለም ተመላልሶ ፥ የመጣበትንም ዋና ነገር አስተምሮ ፈጽሞ ለአዲሱ ሕዝብ ለእስራኤል ዘነ ፍስ የማለውን መሐላ የገባውንም ቃል ኪዳን ያመ ለክታል ።

ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ ያለውን ዘመን ሁሉ ሐዲስ ይለዋል ፤ በእርግጥም ሐዲስ ነው ። ክርስቶስ



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉን አድሶታልና ። ሕጉም አዲስ ነው፤አዲስ ሕገ ወንጌል ተተክቷል ፤ ቃል ኪዳኑም የማዳን ኃይል ያለው አዲስ ሁኗል፤ስለዚህ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት፣ሐዋርያት የጻፉትም በጠቅላላ የምሥራች ይባላል ። በሌላ አጠራር ግን ሁሉን አጠቃሎ ሐዲስ ኪዳን ይለዋል ፤ ሐዲስ ኪዳንም ይባላል ።

እነዚህ ሁለት የኪዳን መጻሕፍት ተጠቃለው ቅዱስ መጽሐፍ ተብለው በአንድ ስም ይጠራሉ፤ግን ኙነታቸውም ደግሞ እንደሚከተለው ነው ፤

፩/ አስገኙ እግዚአብሔር አንድ በመሆኑ ዓላማቸውም አንድ ነው ። የዓለም ድኅነት፣በእግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መምጣት ሆነ፤ይኸንንም ዓላማ ነቢያት በትንቢት ፣ ሐዋርያት በትምህርት መልክ ጻፉት፤ አዘጋጁም ፤ ስለዚህ መሠረተ ዓላማው አንድ ነው ።

፪/ ያለ ብሉይ ኪዳን ሐዲሱ ጎደሎ ይሆናል፤ ጎደሎም ያደርገዋል ፤ እንዲሁም ያለ ሐዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳን ጎደሎ ይሆናል ፤ ጎደሎም ያደርገዋል ፤ ስለዚህ ብሉይ ኪዳን መነሻ ሐዲስ ኪዳን መድረሻ ሁኖ አንድ ይሆናል ። እንዲሁም ብሉይ ኪዳን በሐዲስ ኪዳን ይተረጐማል ፤ ይገለጣል ፤ ለሐዲስ ኪዳንም ብሉይ ይጠቀሳል አስረጅም ይሆናል ። ስለዚህ ሁለቱ ኪዳናት አንድ ይሆናሉ ።

እንግዲህ ለእውነተኛ ክርስቲያን እውነተኛ መጽሐፍ ይኸ ቅዱስ መጽሐፍ ብቻ ነው፤ስለዚህም ቅዱስ መጽሐፍ የመጻሕፍት ሁሉ ራስ ይባላል፤እንዲሁም እርሱን



መስለው ፤ ከእርሱም ተቀድተው የተጻፉ ብዙዎች የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ይገኛሉ ፤ እነርሱንም ቤተ ክርስቲያን አክብራ ትቀበላቸዋለች ፤ ታስተምርባቸዋለች ። ቤተ ክርስቲያን አብዛኛውን የምትገለገልባቸው፤ቅዱስ መጽሐፍን ሳይቀር የምትተረጐምባቸው በነዚህ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት በሆኑ መጻሕፍት ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

## ሀ—የብሉይ ኪዳን ክፍል ፤

### መቅድም ፤

የተመረጠውና ሕዝበ እግዚአብሔር የተባለው እሥራኤል ፈጣሪውን በእውነተኛው መንገድ ያመልክ ዘንድ ሕግ ሠራላቸው ፤ እንዲሁም የእርሱና የሕዝቡቹ መገናኛ የሚሆን ቃል ኪዳን ገባላቸው ፤ ይኸም ቃል ኪዳን ብሉይ ኪዳን ተባለ ።

ብሉይ ኪዳንን እግዚአብሔር አምላክ የእሥራኤል ሕዝብ ታሪክ የእምነታቸውም መሠረት ይሆን ዘንድ ገልጠላቸው በጽሑፍም አዋሉት ።

እግዚአብሔር አምላክ በጠቅላላ የሰውን ነገድ ሊታረቅ ቢል በእሥራኤል አማካይነት ፈቃዱ ምን እንደሆነ ገለጠ ፤ ቃል ኪዳንም ገባ ። ይኸ የእግዚአብሔርና የሰው መገናኛ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር የገለጠው ፤ በጽሑፍም የሰጠው መጽሐፍ ብሉይ ኪዳን ተብሎ ይጠራል ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላክ ለአባቶች መሐላን ምሏል ቃል ኪዳንም ገብቷል ና ኪዳን ተባል ።

ከዓለም ፍጥረት አንሥቶ እስከ ክርስቶስ መምጣት የሚናገረው ይኸ መጽሐፍ ኪዳን ተብሎ ኪዳንም ሁኖ እንደ ዐይን ብሌን እንዲጠበቅ እሥራኤልን በማስጠንቀቅ ቀብሮቷቸዋል ።

ከሊቀ ነቢያት ሙሴ ጀምሮ እስከ ነቢዩ ሚልክያስ ያሉ ነቢያት ሁሉ የጻፉት በእግዚአብሔር መንፈስ



እየተመሩ ነው ፤ ማለት በእግዚአብሔር ገላጭነት የጻፉት ስለሆነ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ይባላል ። መሐላ ወይም ቃል ኪዳን ስላለበት ብሉይ ኪዳን ይባላል ። ይኸውም መጽሐፍ በመጀመሪያ በዕብራይስጥ ተጻፈ፤ለጊዜው ለእሥራኤል ሕዝብ ብቻ ተሰጠ፤ ቆይቶ ግን ወደ ግሪክኛ በጽሑፍ ሊቃናት ተተረጐመ ፤ ከዚያ በኋላ ግን ክርስቲያኑ ዓለም በየቋንቋው ተርጉሞ፣ ቅዱስ መጽሐፍ አድርጎ፣ ቅዱሳ መጻሕፍም ብሎ ይጦት ይገኛል ። እኛም ኢትዮጵያውያን በዚሁ መልክ ቀደም ብሎ ተተርጕሞልን ብሉይ ኪዳን ደርሶን ይገኛል ።

ይኸ ብሉይ ኪዳን የእሥራኤል ታሪክ ያለበት ሲሆን የሃይማኖትም ታሪክ ነው ፤ ማለት የሰው ልጅ ወደ ሃይማኖት እንዴት እንደደረሰ ይናገራልና ። ለኛ ለክርስቲያኖችም የእምነቱ መነሻ እንደመሆኑ ጥቅሙ ከፍ ያለ ነው ፤ ምክንያቱም እኛ የምናመልከው ያኑ አንዱን የእሥራኤል አምላክ ነውና ።

ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን መግለጫ መነሻ ስለሆነ ክርስቲያኑ ሕዝብ አስቀድሞ ሊያውቀው፣ ሊያጠናው ይገባል ፤ ስለዚህ እንዴት አድርገን ማወቅ ማጥናትም እንዳለብን በሚቀጥለው አገላለጥ እንገልጻለን ።

### ምዕራፍ ፩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

ብሉይ ኪዳን የተባለው በቀደመው ወይም በአለፈው ዘመን እግዚአብሔር አምላክ ለእሥራኤል



www.ethiopianorthodox.org

የገለጠው ምሥጢር የገባውም ቃል ኪዳን ምንና ምን እንደሆነ የሚገልጥ መጽሐፍ ነው ።

ብሉይም ሲባል ሕጉ ወይም ቃል ኪዳኑ ያረጀ ነው ማለት አይደለም ፤ ቃል ኪዳኑ ሁልጊዜ አዲስ ነው ፤ ግን ዘመኑ አርጅቷል ፤ ብዙ ጊዜም አልፏል ፤ በዚያን ጊዜ የነበረ መሆኑን ለማስረዳት ሲል ብሉይ ኪዳን ይለዋል ።

ብሉይ ኪዳን በመባል የሚጠሩት መጻሕፍት እግዚአብሔር በተለያየ መልክ መገለጡን የሚናገሩ መጻሕፍት ናቸው፤ይኸም አገላለጥ ከሙሴ ጀምሮ በተለያዩ ነቢያት የተደረገ ነው ።

ይኸም የእግዚአብሔር አገላለጥ የሚባለው የሰውን ልጅ ለሚመጣው ተስፋ ለማዘጋጀትና ለመ ምራት ነው፤ይኸውም ይመጣ ዘንድ ያለው መሢሕን ሳመቀበል የሚችሉበትን የሚገልጥ፣የሚያብራራም ነው ። መጽሐፉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለው ዓላማ ይኸው ብቻ ነው ። ይኸንም ለማስረዳት በለስ ላሳ ቃል በሥነ ፍጥረት ይጀምራል ፤ ዓለም እንዴት እንደተፈጠረች፣ሰው ደግሞ የፍጥረቱ ሁሉ ገዥ እን ደሆነ ይናገራል ።

እንዲሁም ሰው ደስተኛ ሁኖ እንደሚኖርና ከእግዚአብሔር ቅርብ እንደነበር፣ግን በሕግ አፍራሽ ነቱ ከእግዚአብሔር እንደራቀ፣ከክብሩም እንደተዋ ረደ ያስረዳል ።

በመላው የሰው ልጅ ሁሉ በዚያን ጊዜ ይቅበዘበዝ እንጂ ብሉይ ኪዳን አጥልቶ የሚናገረው በእሥራኤል



ላይ ይደርስ የነበረውን ብዙ ግፍ ነው ፤ ይኸውም ከአብርሃም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መምጣት የነበረውን ግፍ ገልጦ ያሳያል ።

ብሉይ ኪዳን የተጻፈበት ቋንቋ ፣ የጻፉት ሰዎች፣ የተጻፈበት ጊዜ የተለያየ ነው ። የመጀመሪያዎቹ አም ስቱ የሙሴ መጻሕፍት በጣም ቀደም ብለው እንደ ተጻፉ የታወቀ ነው ፤ ቋንቋውም ዕብራይስጥ እንደ ሆነ ይነገራል ።

ቆይተው ከተጻፉ መጻሕፍት ውስጥ ጥቂቶች በአረማይክ ቋንቋ እንደተጻፉ ይገመታል ፤ ይኸም ቋንቋ ወደ ዕብራይስጥ የቀረበ ፣ ጌታ ኢየሱስ ሲናገር ያደገበት ቋንቋ ነው ፤ በሌላ አነጋገር ደግሞ ሱርስት የሚባለው ነው ።

በዘመንም የኪዳን እንደሆነ እስከ ፫ኛው ምእት ዓመት ከክርስቶስ በፊት ድረስ ሲያዘግም እንደመጣ የታወቀ ነው ።

## ምዕራፍ ፪ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አከፋፈል

### ክፍል ፩ ሕግ

አምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ ፤ ወይም አምስቱ የሕግ መጻሕፍት (ኦሪት) ወይም አምስቱ ብሔር እየተባሉ የሚጠሩት በሙሴ የተጻፉ ከሲና ምድረ በዳ እስከ ደብረ ናባው በአለው የጉዞ ጊዜ የተጻፉ ናቸው ፤ በግምት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፲፫ኛው ምእት ዓመት ገደማ የተጻፉ ናቸው ። እነዚህም ፤

፩/ ዘፍጥረት ፶፱ ምዕራፍ አለው ፤

፪/ ዘጸአት ፵ ምዕራፍ አለው ፤



www.ethiopianorthodox.org

፫/ ዘሌዋውያን ፳፯ ምዕራፍ አለው ፤
፬/ ዘኍልቍ ፴፮ ምዕራፍ አለው ፤
፭/ ዘዳግም ፴፬ ምዕራፍ አለው ፤

## ክፍል ፪ ታሪክ

፮/ መጽሐፈ ኢያሱ ፤ ይኸ መጽሐፍ በጸሐፌው ሰው የተሰየመ ነው ፤ ይኸውም ከሙሴ ቀጥሎ የእስራኤል መሪ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር የመረጠው፣እስራኤልን እየመራ ምድረ ርስት ይዞ የገባው ሰው ኢያሱ ነው ። የመጽሐፉም ዓላማ የእርሱን አሠራር፣ የሕዝቡን ጉዞ፣ የምድረ ርስትን አወራረስ ያስረዳል ። ይኸም መጽሐፍ ፳፬ ምዕራፍ አለው ።

## ፯/ መሳፍንት

፰/ ሩት እነዚህ ሁለት መጻሕፍት በነቢዩ በሳሙኤል እንደተጻፉ ይነገራል ። የተጻፉበትም ዘመን ከክርስቶስ በፊት በ፲፩ኛው ምእት ዓመት ገደማ ነው፤ በመሳፍንት ዘመን የነበረው የእሥራኤል ኑሮ ፣ የመሳፍንት ይዞታ እንዴት እንደነበር በነዚህ መጻሕፍት እንረዳለን ። ይኸም መጽሐፈ መሳፍንት የተባለው ፳፩ ምዕራፍ አለው ።

በመጽሐፈ ሩት ደግሞ የአንዲት ሙአባዊት ሴት ታሪክ እናገኛለን፤ ይኸችም ሩት የተባለች ናት። ከቲዕፋሙ ውጭ የነበረች የአረማውያን ዘር ስትሆን ከክርስቶስ ልደት ውስጥ ገብታ እንድትቈጠር የሆነች የተስፋ ሴት መሆኗን ይናገራል ፤ ይኸም መጽሐፍ ፬ ምዕራፍ አለው ።

፱/ ነገሥት ቀዳማዊ ፴፩ ምዕራፍ አለው
፲/ ነገሥት ካልዕ ፳፬ ምዕራፍ አለው ፤



፲፩/ ነገሥት ሣልስ ፳፪ ምዕራፍ አለው ።
፲፪/ ነገሥት ራብዕ ፳፭ ምዕራፍ ያለው ሁኖ

እነዚህ አራቱ መጻሕፍተ ነገሥት የተለያየ ስም አላቸው፤የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ መጻሕፍተ ሳሙኤል ሲባሉ ሁለቱ ደግሞ ነገሥት ይባላሉ፤ ሌላው አስተያየት ደግሞ መጻሕፍተ ነገሥት ቀዳማዊ ካልዕ ፤ ሣልስ ፤ ራብዕ ፤ እያለ ጽፎ እናገኛለን ( ፍ /ነ )

እነዚህን መጻሕፍት ማን እንደጻፋቸው በትክክል አይታወቅም ፤ የሚተርኩት ግን የ፭፻ ዘመን ታሪክን ነው ፤ ይኸውም ከሳኦል ጀምሮ እስከ ሰሎሞን ያለውን ዘመነ ነገሥት ነው ፤

በዚህ ዘመን እሥራኤል እንዴት ይኖሩ ምንስ ይሠሩ እንደነበር የሚናገር ነው ።

፲፫/ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
፲፬/ ዜና መዋዕል ካልዕ፤እነዚህ መጻሕፍት በዕዝራ እንደተጻፉ ይነገራል፤ዘመኑም ከክርስቶስ በፊት በ፬፻፶ ዓመት መሆኑ ነው ።

በነዚህ መጻሕፍት እንደአስተዋዕኦ ሁኖ ከአዳም ጀምሮ እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስ ያለውን የእሥራኤል ታሪክ ይነግረናል ። ዜና መዋዕል ቀዳማዊ ፳፱ ምዕራፍ አለው፤ዜና መዋዕል ካልዕ ፴ ምዕራፍ ያለው ሆኖ ይገኛል ።

፲፭/ ዕዝራ ፩ኛ/ ይኸም መጽሐፍ የዕዝራ ጸሐፊ ነው ፤ ዓላማውም ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ያለውን የእሥራኤልን ታሪክ ለማስረዳት ነው ፤ ፲ ምዕራፍ አለው ።



www.ethiopianorthodox.org

፲፮/ ዕዝራ ነህምያ ይባላል ፤ ይኸም ሥራ የዕዝራ ነው ፤ ከስደት መልስ በኋላ የእሥራኤ ልን መንግሥት ለማቋቋም እሥራኤል ምን ያህል ጥረት እንዳደረጉ ይነግረናል ። ስለዚህም ከ፭፻፴፰—፬፻፵፬ ዓ/ም ስለነበረው ዘመንሁኔታ በሰፊው ያስረዳል ። ይኸም መጽሐፍ ፲፫ ምዕራፍ አለው ።

፲፯/ የዕዝራ ፪ኛ መጽሐፍ ፲፫ ያህል ምዕራፍ አለው ዕዝራ ሱቱኤልም ይባላል ።

፲፰/ ጦቢት
፲፱/ ዮዲት
፳/ አስቴር
፳፩/መቃብያን ፩ኛ
፳፪ መቃብያን ፪ኛ
፳፫/መቃብያን ፫ኛ እነዚህ ስድስቱን መጻሕፍት ማን እንደጻፋቸው፣መቼ እንደተጻፉ ግልጥ የሆነ ማስረጃ የለም ፤ ሁናም ከጥንት ጀምሮ ከቀኖና ብሉይ ኪዳን ገብተው ተቈጥረው የሚኖሩ መጻሕፍትናቸው፤ በዕብራውያን መጻሕፍት ግን ከአስቴር በቀር ሌሎች ከቊጥር ያልገቡ ናቸው ።

እነዚህ መጻሕፍት ስማቸው የተጠሩትን ሰዎች ታሪክና ሥራ በሰፊው ይገልጣሉ ፤ ይኸም ማለት እነርሱ ስለ እሥራኤል ሕዝብ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ይገልጣሉ ።

እነዚህ ሰዎች ስለወገናቸው ፥ ስለ ሀገራቸው ምን እንደሠሩ፣ምን እንዳበረከቱ፣ለሌላው ምሳሌነት እንዲሰጡ በማለት የተጻፉ ናቸው ። ጦቢት ፲፬ ምዕራፍ



አለው፡፡ዮዲት ፲፮ ምዕራፍ አለው፡፡አስቴር፲፩ምዕራፍ አለው ። መቃብያን ቀዳማዊ ፴፮ ምዕራፍ አለው ። መቃብያን ካልዕ ፳፩ ምዕራፍ አለው፤ መቃብያን ሣልስ ፲ ምዕራፍ አለው ።

## ክፍል ፫ መዝሙር ወይም ትምዐርት

እነዚህ መጻሕፍት በግጥም፣በመዝሙር መልክ የተጻፉ ናቸው ፤ ዓላማቸው ግን ሰውን በለሰለሰ መንገድ ለመሳብ፥ለማስተማር ወደ መልካም ጠባይ ለመለወጥ ነው ። አንድ ሰው ከሌላው ጋር እንዴት በስምምነትና በመግባባት መኖር እንደሚችል ፥ እንዲሁም ለእግዚአብሔር በእንዴት ያለ መልክ ምስጋና፤መዝሙር ማቅረብ፤እያንዳንዱ ሰው እንደሚገባው ግዴታውም እንደሆነ በመግለጥ ነው ። የነዚህም የግጥም ወይም የመዝሙር መጻሕፍት የሚባሉ ተራ እንደሚከተለው ነው ።

፩/ ኢዮብ ፤ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ግልጥ ሁኖ የሚታወቅ አይደለም ፤ ሁኖም በእግዚአብሔር ላይ ክፍተኛ እምነት የነበረውን ፥ በትእግሥቱም ፍጹም የነበረውን የኢዮብን ታሪክ ልብን በሚነካ መልክ ይገልጣል ። እርሱም ፵፪ ምዕራፍ አለው ።

፪/ መዝሙረ ዳዊት ፤ በነቢዩ በዳዊት ስም የቀረቡ ፻፶፩ መዝሙሮች ያሉት መጽሐፍ ነው ። እነዚህም በእሥራኤል ሕዝብም በክርስቲያኑም ዓለም ለምስጋና፥ለጸሎት ተስማሚ ሁነው ጥንትም አሁንም የታወቁ ሲሆኑ፥የሚበዙትን ግን ራሱ ዳዊት እንደጻፋቸው የታወቀ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

፫/ ምሳሌ ሰሎሞን ፤ የነዚህም ምሳሌዎች ጸሐፊ የዳዊት ልጅ ጥበበኛው ንጉሥ ሰሎሞን ነው ፤ በዚህም መጽሐፍ የእሥራኤል ሕዝብ ምሳሌዎችና የራሱ የጥበበኛው የንጉሥ ሰሎሞን አስተያየትም እንደሚገኝበት ይታመናል ። ለነርሱም ፴፩ ምዕራፎች አሏቸው ፤ከ፳፩ ምዕራፍ ጀምሮ ያለው ፺፥ ምዕራፍ ግን በግእዝ መጽሐፋችን ተግሣጽ ይባላል ፤ ራሱንም ችሎ ይቈጠራል ።

፬/ መክብብ ፤ ይኸም የሰሎሞን ጽሕፈት ነው፤ በዚህም የሰውን ተፈጥሮና የሥራውን ከንቱነት ከተመለከተ በኋላ ለሌሎቹለመግለጥ የጻፈው፣ያስረዳውም ነው ። ለዚህም መጽሐፍ ፲፪ ምዕራፎች አሉት ።

፭/ መሐልየ መሐልይ ፤ ይኸም መሐልይ የሰሎሞን ጽሕፈት ነው፤ምሥጢራዊ በሆነ ፍቅር መልክ የትስብእትንና የመለኮትን ተዋሕዶ በጠቅላላም የክርስቶስን ሰው መሆን የሚገልጥ ነው ። እንዲሁም ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ምእመናን በምሳሌ እንደተናገረ ይተረጐማል ። ይኸም መጽሐፍ ፰ ምዕራፍ አለው ።

፮/ ጥበበ ሰሎሞን ፤ ይኸም አነስተኛ የሰሎሞን መጽሐፍ ነው ፤ ይህም መጽሐፍ ስለጥበብ እውነተኛነት ያረጋግጣል ። ይህም መጽሐፍ ፲፱ ምዕራፎች አሉት ። በጠቅላላ ጥበበኛው ሰሎሞን ፭ መጻሕፍት ጽፏል ፤ ሁሉንም ተቀብለናቸዋል ።

፯/ ጥበበ ሲራክ ፤ ይኸምመጽሐፍ ሲራክ በተባለ ጥበበኛ ሰው እንደተጻፈ ይነገራል ፤ የነበረበት ዘመንበ፩፻፹፱ዓ. ዓ. ከክርስቶስበፊት እንደሆነ ይገመታል ። ይኸም መጽሐፍ የሰሎሞንን ምሳሌ ይመስላል ። ሰው የሆነው ሁሉ በሥነ ሥርዓት እንዲኖር በሥነ ምግባርም አጊጦ መኖር እንደሚገባ የሥነ ምግባርን ስልትና ጥቅም በመግለጥ ይናገራል ። ይኸም መጽሐፍ ፶፩ ምዕራፎች አሉት ።

## ክፍል ፬ ትንቢት ወይም የትምህርት

በዚህ በ፬ኛው ክፍል ነቢያት የተናገሩት ትንቢት፣ ያስተማሩት ትምህርት ምን ዓይነት እንደሆነ እናገኛለን ። በነዚህም መጻሕፍት አማካይነት እግዚአብሔር እሥራኤልን እንደሚጐበኛቸው፣እንደሚታደጋቸው እናገኛለን ። ይኸውም በእርሱ ላይ ያለው እምነታቸው የጸና እንደሆነ ነው ። በዚህ አንጻር ግን ምናልባት ከሕጉ ቢተላለፉ እግዚአብሔር እንደሚያጋልጣቸው፣ አሳልፎም ለመከራ እንደሚሰጣቸው፣ እንደሚቀጣቸውም ያመለክታል ።

እንዲሁም ሰላም ወይም ጥፋት የሚመጣ መሆኑን አስቀድመው ከመሆኑ በፊት እንደ ተናገሩ ሕዝቡን እንደ አስጠነቀቁ ያስረዳናል ። እንዲሁም የክርስቶስን ልደት የዓለሙን ድኅነት አስቀድመው እንደ ተናገሩ እንረዳለን ፤ ለምሳሌ ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ የክርስቶስን መምጣት ስም ጠርቶ መከራውንም ገልጦ ተናግሯል፤ጽፏልም ። የእርሱም ትንቢት ከ፯፻ ዓመተ ዓለም በፊት የተጻፈ ሲሆን ከክርስቶስ በኋላ የተጻፉትን ወንጌላት ይመስላል ፤ ስለዚህም የእርሱን ትንቢት ደረቅ ሐዲስ ብለው አባቶች ሰይመውታል ።



www.ethiopianorthodox.org

የነቢያት መጻሕፍት የየራሳቸውን ጸሓፊ ስም እን ደያዙ ይገኛሉ፤ስለዚህ በዚያው ይጠራሉ ። ነቢያት የተባሉትም በ፪ ክፍል ይከፈላሉ ፤ ይኸውም ፥

፩/ ዐበይት ነቢያት

፪/ ደቂቅ ነቢያት በማለት ነው ፤

—ዐበይት ነቢያት የሚባሉት ፬ ናቸው ፤ እነርሱ

፩/ ኢሳይያስ
፪/ ኤርምያስ
፫/ ሕዝቅኤል
፬/ ዳንኤል ናቸው ።

—ደቂቅ ነቢያት የሚባሉ ደግሞ ፲፪ ናቸው ። እነርሱም ፤

፩/ ሆሴዕ
፪/ ኢዩኤል
፫/ አሞጽ
፬/ አብድዩ
፭/ ዮናስ
፮/ ሚክያስ
፯/ ናሆም
፰/ እንባቆም
፱/ ሶፎንያስ
፲/ ሐጌ
፲፩/ ዘካርያስ
፲፪/ ሚልክያስ ናቸው

እነዚህም መጻሕፍት በዛም አነስም ያሉ ምዕራፎች ያሏቸው ሲሆን ሰፋ ያለ አስተያየት የረቀቀም ምሥጢር አላቸው፤በመጀመሪያ የዐበይት ነቢያትን



እንመልከት።ትንቢተ ኢሳይያስ ፷፮ ምዕራፍ አለው ፤ ሙሉና ፍጹም የሆነ ትምህርትን የያዘ መጽሐፍ ነው።
ትንቢተ ኤርምያስ ፶፪ ምዕራፍ አለው ፤ ሙሉና ፍጹም የሆነ ትምህርትን የያዘ መጽሐፍ ነው ።

ሰቆቃወ ኤርምያስ ፭ ምዕራፍ አለው ፤ ሙሉና ፍጹም የሆነ ትምህርትን የያዘ መጽሐፍ ነው ።
መጽሐፈ ባሮክ ፭ምዕራፍ አለው፤ ሙሉና ፍጹም የሆነ ትምህርትን የያዘ መጽሐፍ ነው ።

ትንቢተ ሕዝቅኤል ፵፰ ምዕራፍ አለው ፤ ይኸ መጽሐፍ ከባድ የሆነ አገላለጥ አለው ።
ትንቢተ ዳንኤል ፲፪ ምዕራፍ አለው፥ ይኸም መጽሐፍ ብዙ ታምራታዊ አገላለጥ ይገኝበታል ።
እንዲሁም በደቂቅ ነቢያት መጻሕፍት የሚገኙት እንደሚከተለው ይገለጣሉ ።

፩/ ሆሴዕ ፲፬ ምዕራፍ ይገኝበታል ።
፪/ ኢዮኤል ፫ ምዕራፍ ይገኝበታል ።
፫/ አሞጽ ፱ ምዕራፍ ይገኝበታል
፬/ አብድዩ ፩ ምዕራፍ ይገኝበታል ።
፭/ ዮናስ ፬ ምዕራፍ ይገኝበታል ።
፮/ ሚክያስ ፯ ምዕራፍ ይገኝበታል ።
፯/ ናሆም ፫ ምዕራፍ ይገኝበታል ።
፰/ ዕንባቆም ፫ ምዕራፍ ይገኝበታል ።
፱/ ሶፎንያስ ፫ ምዕራፍ ይገኝበታል
፲/ ሐጌ ፪ ምዕራፍ ይገኝበታል ።
፲፩/ ዘካርያስ ፲፬ ምዕራፍ ይገኝበታል ።
፲፪/ ሚልክያስ ፬ ምዕራፍ ይገኝበታል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ዐቢይ ክፍል ፫ የሐዲስ ኪዳን ክፍል ፤

### መቅድም ፤

ለአዲሱ እሥራኤል፡ክርስቶስ ለቀደሰው ለክርስቲያኑ ሕዝብ መመሪያ ይሆነው ዘንድ የተሰጠ መጽሐፍ ሐዲስ ኪዳን ይባላል ።

በደሙ የተቤዠውን ሕዝብ ክርስቶስ እንዲሁ አልተወውም ፤ መጀመሪያ እሥራኤል ዘሥጋን ከግብጽ ባርነት ነጻ ሲያወጣ ኪዳን እንደገባለት፣ መመሪያ ሕግም እንዳወጣለት፣ የተስፋ ቃልም እንደተናገረለት ሁሉ፡እሥራኤል ዘነፍስ የተባለውን ሕዝብ ከግብርናተ ዲያብሎስ ነጻ አውጥቶ በደሙ ተቤዥቶ እንዲሁ አልተወውም ፤ አዲስ ኪዳን ገባለት ፤ አዲስ ትእዛዝም አወጣለት ፤ የተስፋም ቃል ተናገረለት እንጂ ። ስለዚህ ይኸ ሐዲስ ኪዳን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ስምምነት፣ ቃል ኪዳን የሚገልጥ አዲስ የተስፋ ምዕራፍ የአዲስ የቃል ኪዳን መጽሐፍ ነው ።

ይኸም የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ የድኅነትና የምሥራች መጽሐፍ ይባላል ፤ ድኅነተ ሥጋን፣ ድኅነተ ነፍስን ለሰው ልጅ ሁሉ ያበሥራልና ።

አምላክ የቀደመውን ያረጀውን ዘመን አሳልፎ አዲስ ዘመን፣ አዲስ ሕግ፣ አዲስ ተስፋ ለሰው ልጅ ሁሉ ሰጠ፤አዲስ ቃል ኪዳንም ገባ፤ስለዚህ ይህን ሁሉ የሚያበሥረው መጽሐፍ ሐዲስ ኪዳን ነው ። ይኸም መጽሐፍ ከመስቀል ላይ በአፈሰሰው ደሙ የተጻፈ የሕይወት መጽሐፍ ነው ፤ (ማቴ.፳፮:፳፰.) ።



ሐዲስ ኪዳን የተባለው መጽሐፍ በአጠቃላይ ሲጠራ ነው እንጂ በዝርዝር ሲታይ በ፬ ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል ፤ ይኸውም ፤

#### ሀ/ የምሥራች ክፍል ፤

፩/ በዚህ ክፍል ፬ቱ ወንጌላት ይገኛሉ፤ወንጌል ማለትም የምሥራች ማለት ነው ፤ ምክንያቱም ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደጠፉ፣ ዓለም እንደዳነ የምሥራችን ይናገራሉና ።

፪/የታሪክ ክፍል ፤ይህ ክፍል ከወንጌላት ከፊሉንና የሐዋርያት ሥራን ይይዛል ፤ ይኸም የክርስቶስን ሕይወት ከፅንስ እስከ ዕርገት ያለውን በዝርዝር ትምህርቱን፣ ተአምራቱን፣ ጠቅላላ ሥራውንም ይናገራል ።

፫/ የትምህርት ክፍል ፤ ይኸም ፲፬ቱን የጳውሎስንና የ፯ቱን አጠቃላይ መልእክታት ይይዛል ። በዚህም ክፍል ፳፩ መጻሕፍት ይገኛሉ ፤ እነርሱንም ወደፊት እንዘረዝራለን ። በእነዚህ መጻሕፍት ሙሉ የሆነ ክርስቲያናዊ ትምህርት እናገኝባቸዋለን፤በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያን ትመራበታለች ።

፬/ የትንቢት ክፍል ፤ ይኸም ክፍል የዮሐንስ ራእይ የተባለውን መጽሐፍ ይመለከታል ።

#### ምዕራፍ ፩ ወንጌል (ኢቫንጌልዮን) ።

ወንጌል የሚለው ቃል ኢቫንጌልዮን ከሚለው ከግሪኩ ቃል በቀጥታ የመጣ ነው ፤ ትርጉሙም የም



www.ethiopianorthodox.org

ሥራች ማለት ነው፤ታላቁን የምሥራች የሰውን ልጅ ድኅነት ፤ የክርስቶስን ልደት ያበሥራልና ።

በሰው ልጅ ዘንድ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደ ጠፋ ክርስቶስ እንደነገሠ ፥ ዲያብሎስ እንደተጋዘና ኃጢአትእንደተደመሰሰ፥ጽድቅእንደነገሠ ይናገራልና።

ይኸን የምሥራች ቀድመው የተናገሩ መላእክት ናቸው ፤ እነርሱም ክርስቶስ ሲወለድ፤ዓለሙ ሲድን አይተው የእግዚአብሔርን ቸርነት አጕልተው እን ዲህ ሲሉተናግረዋል። «መልአኩ ግን እንዲህአላቸው፤ አይዟችሁ፤አትፍሩ፤ለሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ደስታ የምስ ራች የሚሆን ዜና ይገልላችሁ መጥቻለሁና ። እነሆ ዛሬ በዳዊት ከተማ አዳኝ ተወልዶላችኋልና »
ሉቃ.፪.፲—፲፩.) ።

በዚህም ወንጌል በሚለው ስም በመላ የሐዲስኪዳን መጻሕፍት ሊጠሩበት ይችላሉ ፤ ምክንያቱም ሁሉም ዓላማቸው አንድ ነውና፤ማለት የዓለሙን ድኅነት ፤ የእግዚአብሔርን ምሕረት፤ የክርስቶስን አዳኝነት ይናገራሉና።ሁናም ወንጌል የሚለው ቃል ለ፬ቱ መጻ ሕፍት፤ማቴዎስ፤ማርቆስ፤ ሉቃስ፤ዮሐንስ ለጻፉአቸው ለመጀመሪያዎቹ ክፍሎች ብቻ የጸና ይሆናል ።

የነዚህም መጻሕፍት ጸሐፍያንወንጌላውያንተብለዋል፤ ምክንያቱም ከሁሉ ቀድመው ወንጌልን ጽፈው የም ሥራቹን ቃል ለሰው አስተላልፈዋልና ።

እነዚህ ፬ቱ መጻሕፍት ብቻ ይኸን ስም ሊያገኙ የቻሉት የአዳኙን ጌታ የኢየሱስን ሙሉ የሕይወት ታሪክ ይዘው ስለሚገኙ ነው ።



ጠቅላላ የሰው ልጅ ድኅነት የተገኘው በኢየ ሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ነው ፤ ስለዚህ እነዚህ መጻሕ ፍት የእርሱን ሕይወት ከፅንሰቱ እስከ ዕርገቱ ይተ ርካሉ ፤ ተአምራቱን ፥ ትምህርቱን ይገልጣሉና ።

## ምዕራፍ ፪ የወንጌል ጸሐፍት ፤

ወንጌልን የጻፉ ሰዎች ፀሉቱ ከሐዋርያት፡ሁለቱ ደግሞ ከ፸ አርድእት ውስጥ እንደሆኑ ይነገራል ። ፪ሐዋርያት ውስጥ የጻፉ ማቴዎስ ፥ ዮሐንስ ናቸው ። ሌሎች ደግሞ ማርቆስና ሉቃስ ናቸው ።

እነዚህም ሰዎች በቦታ ተለያይተው ሲኖሩ ፤ በተለያየም ዘመን ሲጽፉ ፥ የወንጌሉ ዓላማ ፥ ቃሉ ፥ አተራረኩም ሁሉ ሳይለያይ ተገኝቷል ፤ ይኸም በ፩ መንፈስ ቅዱስ ተመርተው ስለጻፉት አንድ ዓይነት ሁኖ ለመገኘት በቅቷል ። አንዱ ወንጌል ለአንዱ ምስክር ይሆን ዘንድ ፬ሁኖ እንዲቀርብ ፈቃዱ የእግዚ አብሔር ሁኖ ተገኘና ተጻፈ እንጂ የሁሉም አቀራረብ አንድ ዓይነት ስለሆነ ፩ኛው መጽሐፍ ብቻ ቢያዝ ይበቃ ነበር ።

የመንፈስ ቅዱስ ሀብቱ ጥበቡ ብዙ በመሆኑ ፬ ሁኖ እንዲጻፍ አደረገ ፤ ግን አንድ መንፈስ ስላጻፋ ቸው ደግሞ አንድ ወንጌል ሁኖ ተገኘ ማለት አንድ ዓላማ ያለው ሁኖ ተገኘ ።

፫ኛ. ወንጌላውያን የሚለያዩበትና የሚተባበሩበት፤

የመጀመሪያዎቹ ፫ ወንጌላት በበለጠ ይገናኛሉ ይስማማሉም ፤ ሲኖብሲስ (ቅጅ) ይባላሉ ፤ አተራረ ካቸው ፩ ዓይነት ነው ፤ ለምሳሌ ፫ቱወንጌላውያን ክር



www.ethiopianorthodox.org

ቶስ በገሊላ የፈጸመውን ግብር ይናገራሉ ፤ ፬ኛው ወንጌል ግን በኢየሩሳሌም የፈጸመውን ይናገራል ።

የመጀመሪያዎቹ ፫ቱ ወንጌላውያን ክርስቶስ ፩ ጊዜ ብቻ ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ወጣ ሲናገሩ ፬ኛው ወንጌላዊ ግን ፬ ጊዜ እንደወጣ ይናገራል ።

፫ቱ ወንጌላውያን ስለ ክርስቶስ ትምህርት ፥ በምሳሌም ያለምሳሌም ለሕዝቡ ያስተላለፈውን ሲነ ግሩን፥፬ኛው ወንጌላዊ ደግሞ መንፈስ የሆነውን፥የረ ቀቀውን መለኮታዊ ትምህርት ደረቅ ቃል ያቀርብል ናል ።

፫ቱ ወንጌላውያን የክርስቶስን ምድራዊ ሕይወት በሰፊው ስለሚናገሩ ምድራውያን ይባላሉ ፤ ፬ኛው ወንጌላዊ ግን ሰማያዊነቱን አምላክነቱን አጕልቶ ስለሚናገር መንፈሳዊ ይባላል ።

እንግዲህ ይኽን በመስለ ትንሽ የተለያዩ ቢመ ስሉም በበዛው ነገር የሚስማሙ፥ አንድም የሚሆኑ ናቸው ።

የነዚህን ፬ ወንጌላት ልዩነት ወይም ግንኙነት ለማወቅ ይረዲ፥ዘንድ «በዘንብሩ፥በዘተሌለዩ» ብለው ሊቃውንት መሥመር ለይተው፥ ሠንጠረዥ አውጥ ተው ያስረዳሉ ።

በዚህ መልክ ወንጌላውያንየተለያዩ ቢመስሉም፥ በአንደኛው ወንጌል የሌለ ብሌላው መገኘቱ ደግሞ ግንኙነታቸውን ያስረዳል ፤ ይኸ ሁሉ ሲገናዘብ ደግሞ ፬ቱን ወንጌላት አንድ ሙሉ ወንጌል ያደርጋቸዋል ።



ቅዱሳን ወንጌላውያን በ፩ ቅዱስ መንፈስ ተመ ርተው ሙሉውን የክርስቶስን ምድራዊ ሕይወት ትም ህርቱንም ፥ ተአምራቱንም ተከታትለው ስላቀረቡ ልን ወንጌልን እውነተኛ የምሥራች መጽሐፍ ብለን ተቀብለን ይዘነዋል ።

ክርስቶስ ኢየሱስ እንደሆነ ለማስረዳት ከሙሉ በከፊሉ ተጽፎ እንደቀረበልን ፥ይኸንንም አምነን እንድንቀበል ግዴታችን መሆኑን ወንጌላዊው ዮሐ ንስ ያስረዳናል (ዮሐ. ፳. ፴፩ ፥ ም.፳፩፥ ፳፭ ።)

እንግዲህ እያንዳንዱ ወንጌል ምን እንደሚል፤ ምን ምሥጢር እንደያዘልን ተራ በተራ እንደሚከተ ለው እንመልከት ።

<u>ምዕራፍ ፫ የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ፤</u>

፩/ <u>ጸሓፊው ፥</u> ማቴዎስ ማለት የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው። ይኸ ሰው የሮማውያን ቅጥረኛ ሠራተኛ) ነበር፤ ሥራውም ግብር አስገባሪ (ቀራጭ) እንደነበር ራሱ በጻፈው ወንጌልእንረዳለን(ማቴ.፱.፱።

በግብር ማስገበር ሥራው እንዳለ ክርስቶስ ጥሪ አቀረበለት ፤ እርሱም ሳያመነታ ልዋልም፥ ልደርም ሳይል ወዲያውኑ ተከትሎታል (ማቴ. ፱.፱—፲) ።

ሲሄድም ዝም ብሎ አልሔደም ሀብቱን ለደሀ ሰጥቶበቤቱም ጌታን ግብር አግብቶ፥ሁሉን አሰናብቶ ነው ።

ከዚህች ዕለት ጥሪው ጀምሮ የክርስቶስ ተከታይ፥ ከ፲፪ቱ ውስጥ ፩ዱ ደቀመዝሙርበመሆንአገልግሏል ።



www.ethiopianorthodox.org

በሐዋርያት ስም አጠራር ሁልጊዜ ስምንተኛውን ቍጥር ይዞ ይገኛል፤ ጌታ ሲያርግ ከ፻፳ ቤተሰብ ጋር አብሮ እንደነበር ሉቃስ ገልጦልናል። (የሐ.ሥራ ፩.፲፫)።

፪/ ወንጌሉ ፡ የማቴዎስ ወንጌል ለዕብራውያን ክርስቲያኖች ማስተማሪያ ይሆን ዘንድ ተጻፈ ። የመጀመሪያውም ወንጌል ይኸ እንደሆነ ይታመናል ። ስለዚህም በጥራዝ ጊዜ ቅድሚያን አገኘ ።

እንዲሁም የብሉይ ኪዳን ጥቅስ በብዛት ስላለበትና አስተሳሰቡም ከብሉይ ኪዳን ጋር የተቀራረበ በመሆኑ የብሉይ ኪዳን መጨረሻ፣ የሐዲስ ኪዳን መጀመሪያ ሁኖ እንደ ተጠረዘ ይታመናል ።

ይኸ መጽሐፍ የብሉይ ኪዳን አገላለጥ በብዛት አለበት ፤ ብዙም አስረጅ ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍ የገባበት በመሆኑ በዕብራውያን ዘንድ ተቀባይነት እንደነበረው ይገለጣል ።

የተጻፈበት ቋንቋም መጀመሪያ አረማይክ ነበር በኋላ ግን ወደ ግሪክኛ ተተርጕሟል ።

፫/ የመጽሐፉ እውነተኛነት ፤ ይኸ የመጀመሪያው ወንጌል በቅ/ማቴዎስ እንደተጻፈ የጥንት ቤተ ክርስቲያን መስክራለች ። ቅ/ማቴዎስ ራሱ ጽፎ ስላስተማረበት ዘዜነወ ማቴዎስ ይባላል ፤ ወይም ማቴዎስ የጻፈው ወንጌል ለማለት የማቴዎስ ወንጌል እየተባለ ይጠራል ። ቅ/ማቴዎስ ለመጻፉ ጥርጥር ስለሌለበት እውነተኛነቱን ይመሰክራል ።



፬/ የመጽሐፉ አላማ ፡ ከዕብራውያን ውስጥ ክርስቲያኖች ብሉይ ኪዳንን እንዳቃለሉ፣ የሙሴንም ሕግ እንዳፈረሱ፣ አድርገው ይከሷቸው፣ ያጉላሏቸው ነበር፤ ይኸ ሁናቴ የጠላትነት እንጂ እውነት አለመሆኑን ለማስረዳት ጻፈው። ስለዚህም ማቴዎስ ብሉይ ኪዳንን ክርስቲያኖች እንደማይቀበሉ ለማስረዳት ፡ አባቶችንም እንደሚያከብሩ ለመግለጥ፣ «ወልደ ዳዊት፣ ወልደ አብርሃም» በማለት ከእርእስተ አበው አብርሃምን ፡ ከነገሥታት ዳዊትን በማንሣት ጻፈው ። ይኸም ጥቅስ ለሐዲስ ኪዳን መዠመሪያ የሆነው ብሉይ ኪዳንን እንደሚቀበሉ የሚያመለክት ስለሆነ ዕብራውያን ነገሩን በቀላሉ እንዲፈጽሙት ያደረጋቸዋል በማለት ነው ። እንዲሁም ከዕብራውያን ያመኑት ሁሉ የሚያነቡት ክርስቲያናዊ መጽሐፍ እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሠረት ማቴዎስ ይኸንን እንደጻፈላቸው ይነገራል ። በዚህም ሁሉ ምክንያት የማቴዎስ ወንጌል በዕብራውያን ዘንድ ተቀባይነት ነበረው፤ ስሙንም የዕብራውያን ወንጌል እስከ ማለት ይጠሩት ነበር ።

ለዓለሙ ሁሉ የምሥራች የሚሆነውን ቃል «ንስሐ ግቡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና» (ማቴ.፬.፲፯)፤ በማለት ስለጻፈ የማቴዎስ ወንጌል ለዓለም ሁሉ የሚሆን የምሥራች እንደሆነ ያመለክታል። ኢየሱስ (መሲሕ) ይመጣል እየተባለ ይጠበቅ የነበረው የዓለሙ መድኃኒት እንደሆነ ሁሉም አምነው እንዲቀበሉት ለማስረዳት ተጻፈ ።

፭/ ወንጌሉ የተጻፈበት ዘመን ፡ ይኸ ወንጌል የተጻፈበት ዘመን እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት



www.ethiopianorthodox.org

የማቴዎስ ወንጌል ጌታ ባረገ በ፰፡ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ተጻፈ ይላል ፤ (መቅድመ ወንጌል) ። ይኸም ከሆነ ይኸ ወንጌል ከሁሉ ቀድሞ ተጽፏል ማለትን ያረጋግጣል ።

ይሁን እንጂ አሁንም ይህ ወንጌል መጀመሪያነቱ የተመሰከረለት ነው ፤ በውስጡ የሚገኙት መረጃዎች በመጀመሪያው ለመጠረዝ ቀዳሚነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል ።

## ምዕራፍ ፪ የቅ/ማርቆስ ወንጌል ፤

፩/ ጸሐፊው ፥ የ፪ኛው ወንጌል ጸሐፊ ቅ/ማርቆስ እንደሆነ የታወቀ ነው ፤ ይኸም ሰው የቀደመ ስሙ ዮሐንስ ነበር ። እናቱ ደግሞ ከቅዱሳት አንስት መካከል የነበረች ስትሆን፥ስሟ ማርያም ነበር ። ይኸ ማርቆስ የበርናባስ ወንድም ልጅ እንደነበር ጳውሎስ ይነግረናል (ቈላ. ምዕ. ፬. ፲) ።

የቅ/ማርቆስ ትውልደ ሀገሩ ቀሬናዊ ይሁን እንጂ ዘሩ አይሁዳዊ ነው ፤ እናቱ ቀደም ብለው ከአመኑት ሴቶች ... መሆንዋ ከጌታ አልተለየችም ነበር ፤ ማርቆስም እናቱን እየተከተለ ከመምጣቱ የተነሣ ከጌታ ትምህርት አልተለየም ነበሩ ።

የማርቆስ እናት ትልቅ ክርስቲያናዊት ሴት ... መሆኗ ክርስቲያኖች ሁሉ ሐዋርያት ሳይቀሩ የሚሰበሰቡት በእርሷ ቤት ነበር ። ይኸ የእርሷ ቤት እንደ መጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ይቈጠራል ።

ማርቆስ ከጌታ ጋር ለመኖሩ ገና ወጣት ሁኖ ይከተለው እንዷ ነበር የሚነገርለት ጌታ በአይሁድ እጅ በተያዘ ጊዜ«አንድ ጐልማሳ ጋቢውን ጥሎ ሸሸ» ብሎ ራሱን አርቆ በመናገር ጠቅሶ የጻፈውን በመከተል ነው (ማር. ፲፬፡ ፶፩—፶፪) ።

ማርቆስ በቅ/ ጳውሎስ የሐዋርያዊ ጉዞ አብሮ እስከ ጵንፍልያ ሂዶ ነበር ፤ ከዚያ በኋላ ግን መከራውን በመሰቀቅ እንደተመለሰ ሉቃስ ያስረዳናል ። ( የሐ. ሥራ. ፲፫፡፲፫ ፤ ፲፭፡፴፮—፴፱) ።

ማርቆስ ፀግብጽ እንደሰበከና የእስክንድርያን መንበር እንደመሠረተ የታወቀ ነው ፤ ወንጌሉንም የጻፈው በዚሁ በእስክንድርያ ነው ።

የእስክንድርያን ትልቋን የካቴኪስም ትምህርት ቤት እርሱው እንደመሠረታት ይገመታል ። በዚያው በግብጽ እየሰበከ በሰማዕትነት ሞቷልና ።

፪/የመጽሐፉ እውነተኛነት፥ይኸን ፪ኛውን ወንጌል በማርቆስ ስም የመጣውን የጻፈው ራሱ ቅ/ማርቆስ እንደሆነ የታመነ ነው ።

በቅ/ጴጥሮስና በቅ/ማርቆስ መካከል ትልቅ ግንኙነት ስለነበር የማርቆስ ወንጌል በሚለው ፈንታ የጴጥሮስ እንደሆነ የሚናገሩ አሉ፤ይኸንም ለማለት የቻሉት ማርቆስን ለእስክንድርያ የሾመ ጴጥሮስ እንደሆነ ስለሚነገር እንደ መምህር እንደ ሊቀ ሐዋርያ





www.ethiopianorthodox.org

በመቅጠር ወንጌሉም የእርሱ ነው በማለት ነው ። ይሁን እንጂ ይኸ ወንጌል በማርቆስ የተጻፈ የማርቆስ ወንጌል እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሁሉ በአንድ ድምፅ ይመሰክራሉ ።

፫ኛ የመጽሐፉ ዓላማ ፤ የማርቆስ ወንጌል ለሮማውያን እንደተጻፈ የታወቀ ነው ። ቋንቋውም በሮማይስጥ እንደተጻፈ የሚናገሩ አሉ፤ ለዚኸም ማስረጃ የሚሆን የሮማይስጥ ቃላት በብዛት በወንጌሉ ውስጥ ይገኛልና ። ሁኖም በግሪክኛ ቋንቋ እንደተጻፈ የብዙዎች አስተያየት ነው ።

ወንጌሉ የተጻፈበት ዋና ዓላማ ሮማውያንን የክርስቶስ ተከታይ ለማድረግ ፥ ለሮማውያን የክርስቶስን አዳኝነት ለመግለጥ ነው ። በዚህም መሠረት ወንጌሉ በሮማውያን ግዛት ሁሉ ፈጥኖ ስለደረሰ ሮማውያንንም ፥ ግሪካውያንንም በቀላሉ ሊያስረዳ የቻለ ወንጌል ይህ ነው ።

እንዲሁም ዓላማው የክርስቶስን አምላክነት ለመግለጥ ስለሆነ ፥ የወንጌሉ መጀመሪያ «የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ» ሲል ተናግሯል ፤ ጽፏልም ፤ (ማር.፩. ፩) ።

፬/ የተጻፈበት ዘመን ፤ እንደኛ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት የቅ/ማርቆስ ወንጌል የተጻፈበት ዘመን ጌታ በዓረገ ፲፩ኛው ተፈጽሞ ፲፪ኛው ሲጀመር ነው ፤ ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በ፬ኛው ዓመት ነው፤ ሌላ የተለየ አስተያየት ግን በመጀመሪያ የተጻፈው ወንጌል የማርቆስ እንደሆነ ስለዚህም ቅዱ. እንዳነስ የሚናገሩ አሉ ። በዚህም አንጻር ደግሞ ፪ኛነቱን አጽድቀው በጥራዝም ሁለተኛ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት ይናገራሉ ።



## ምዕራፍ ፭ የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ፤

፩/ ጸሐፊው የ፫ኛው ወንጌል ጸሐፊ ቅዱስ ሉቃስ ነው ። ይህ ሰው አገሩ አንጾኪያ ዘሩ አረማዊ (ግሪክ) ነው ።

ይኸ ወንጌላዊ መቼ እንዳመነ፤በማን ትምህርት እንዳመነ ለማወቅ አስቸጋሪ ሁኖ ይገኛል ። ከ፸ አርድእት ውስጥ እንደሆነ ብዙ ጊዜ ይነገርለታል ፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ እንደተናገረው ከሌሎች ሰምቶ ያመነ እንደሆነ ነው (ሉቃ.፩. ፩—፪) ።

በዚህም መሠረት የጳውሎስ ደቀመዝሙር ሁኖ በዚያው በጳውሎስ ስብከት እንዳመነ፤ስለዚህም የጳውሎስ ደቀመዝሙር ሁኖም እስከ መጨረሻው ሕይወቱ ከጳውሎስ ጎን ተሰልፎ የኖረ ደቀ መዝሙር እንደሆነ ይነገርለታል ።

ቅ/ ሉቃስ ሐኪም እንደነበር ይነገርለታል ፤ ይኸንም ቅዱስ ጳውሎስ መስክሮ ጽፎለታል (ቈላ.፬፡፲፬።) ስለዚህም ቀድሞ ዐቃቤ ሥራይ ዘሥጋ ነበር ፤ በኋላ ደግሞ ዐቃቤ ሥራይ ዘነፍስ ሁኖ መሥራቱን ያጠይቃል ።



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም ሉቃስ ሠዓሊ እንደነበር ይነገርለታል፤ ስለዚህ በየሀገሩ የሉቃስ ሥዕል እየተባለ የሚነገርላቸው ሥዕሎች ይገኛሉ ። በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊትም«ሰላም ለሥቁልኪ እንተ ሠዓላ በእዴ፤ሉቃስ ጠቢብ እምወንጌላውያን አሐዱ» ሲል ፫ቱንም ሞያውን በ፩ ጊዜ ሲመሰክርለት ይገኛል ።

ይኸ ደቀ መዝሙር በስሙ የሚጠራውን ወንጌልንና የሐዋርያት ሥራ የተባለውን መጽሐፍ ጻፈ ። በመጨረሻም በግሪክ አገር በመቄንዶያ ሲሰብክ እንደነበር በዚያው በሰማዕትነት ማረፉ ይነገራል ።

ኟ/ የወንጌሉ እውነተኛነት ፤ የ፫ኛው ወንጌል ጸሐፊ ቅ/ ሉቃስ እንሆነ የታመነ ነው ። ከመሠረቱም ጀምሮ ቅ/ ሉቃስ እንደጻፈው የቤተ ክርስቲያን አባቶች በአንድ ድምፅ መስክረዋል ።

፫/ የመጽሐፉ ዓላማ፤ቴዎፍሎስ ለተባለ በአንድ መኰንን ጠያቂነት ወንጌሉን እንደጻፈው ራሱ መስክሯል (፩፤ ፩—፬) ። እንዲሁም የሐዋርያትን ሥራ የጻፈው እርሱ ሲሆን በዚሁ መኰንን ጠያቂነት እንደጻፈው የታወቀ ነው ፤ (የሐ/ ሥራ ፩/ ፩/ ) ።

ከዚህም ጋር እርሱ አረማዊ ስለነበረ ለአረማውያን በሚገባ መልክ ወንጌሉን እንዳዘጋጀው ይታመናል ።



፬/ የተጻፈበት ዘመን ፤ የሉቃስ ወንጌል የተጻፈበት አገር ፥ የተጻፈበትም ዘመን ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው ። በእስክንድርያ ፥ በመቄዶንያም ፥ በሮም ተጻፈ የሚሉ የተለያዩ አስረጅዎች ይገኛሉ ።

የኛ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ግን ጌታ ባረገ ፳፫ኛው ተፈጽሞ ፥ ፳፬ኛው ሲጀመር ፥ ቀላውዲዎስ ቄሣር በነገሠ በ፲፬ኛው ዓመት እንደተጻፈ ይናገራል።

ምዕራፍ ፮ የቅ/ዮሐንስ ወንጌል ፤

፩/ ጸሐፊው፤ የ፬ኛው ወንጌል ጸሐፊ የያዕቆብ ወንድም ፥ የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ ነው ። ይኸም ወንጌላዊ የጌታ የመጀመሪያ ደቀ መዝሙር ነው ። ከእንድርያስ ጋር ለመጀመሪያ ጌታን የተገናኘ እርሱ ነው (ዮሐ. ፩. ፴፭—፵) ።

የዚህም ወንጌላዊ እናት ሰሎሜ ትባላለች ፤ ይኸችም ከ፴፮ ቅ.አንስት ውስጥየሆነች፥ወንጌላውያን ሁሉ በየቦታው ስሟን ያነሷት ናት (ማር.፲፮.፩፤ማቴ. ፳፯ ፶፮፤ ዮሐ.፲፱ ፳፭)። በኛ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ግን ማርያም ባዑፍልያ እንደምትባል ይነገራል ።

ይኸም ወንጌላዊ በሥጋ የጌታ ዘመድ ነው ፤ እናቱ የቅ/ማርያም ዘመድ ናትና ። ጌታ የሚወደው፥ የጌታ ወዳጅ እየተባለ ይጠራል (ዮሐ. ፲፫/፳፫፤ ፳፩/፳) ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር ባኔርጌስ ደቂቀ ነጎድጓድ እየተባሉ ይጠራሉ (ማር.፫. ፲፯) ።



www.ethiopianorthodox.org

ጌታ ምሥጢረ መለኮቱን ፥ ምሥጢረ ምጽአቱንም ሲገልጥ ይኸ ደቀመዝሙር አልተለየውም ነበር ፤ እንዲሁም ሁሉም ይሞታሉ ሲባል እርሱ እንደማይሞት ተነግሮለታል(ዮሐ. ፳፩. ፳—፳፫)። ከእናንተ መካከል አንዱ ያስይዘኛል ብሎ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ በተናገረ ጊዜ ሁሉም እኔ እሆን እኔ እሆን እያለ ሲሸበር ጌታን ቀርቦ ይጠይቅ ዘንድ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ የጠየቁት ዮሐንስን ነው(ዮሐ.፲፫.፳፩—፳፮)። ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጥለውት ሲበተኑ በእንጸረ መስቀሉ ቁሞ ከእመቤታችን ጋር የተገኘ ይኸው ዮሐንስ ነው ፤ ስለዚህም ጌታ «ነያ እምከ ብሎ እመቤታችን አደራ ሰጥቶታል (ዮሐ. ፲፱. ፳፮—፳፯)።

ይኸ ሐዋርያ ከጰንጠቆስጤ በዓል በኋላ በብዙ ቦታ ሲዘዋወር ታይቷል(የሐ. ሥራ ፫፥ ፩—፱)።

ዮሐንስ በንጉሡ ድሚትያኖስ ትእዛዝ ፍጥሞ ደሴት ተግዞ ፳፩ ዓመት ይኖር ነበር ፤ በስሙ የሚጠራውን ራእይ ያየና የጻፈ በዚያ ነው (ራእ. ፩.፱)።

ዮሐንስ በኤፌሶን ብዙ ጊዜ ይኖር ነበር ፤ ሙቶ እንደተቀበረ የሚነገርለትም በዚህችው ከተማ ነው፤ ነገር ግን «ከዚህ ከቆሙት መካከል እኔ እስከመጣ ሞትን የማይቀምሱ አሉ ሲል ጌታ ከተናገረላቸው ውስጥ ፩ኛው ዮሐንስ ነውና አልሞተም የሚሉ አሉ፤ (ማቴ. ፲፮፥፳፰)። እንዲሁም ጴጥሮስን ተከተለኝ ሲል ስለዮሐንስ ግን እኔ እስከመጣ ቢቆይ ምን አግዶህ ያለውን ይዘው ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ አይሞትም ስላሉ



ዮሐንስ እንዳልሞተ እንደአልተቀበረም ይነገራል (ዮሐ.፳፩፥ ፳—፳፱)።

እንግዲህ ከማንኛውም ከጌታ ደቀመዝሙር ውስጥ ብዙ ዘመን የቆየና ዕድሜ የጠገበ ዮሐንስ ወንጌላዊ ብቻ ነው ፤ እስከ ፻፲ ዓመት እንደኖረ ይነገርለታል።

፱/ የወንጌሉ እውነተኛነት ፤ ፬ኛው ወንጌል በዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ እንደተጻፈ የውስጥም የውጭም ምስክር አለ። የውስጥ ምስክር ወንጌሉን የጻፈ የጌታ ወዳጅ የሆነ እንደሆነ መላልሶ በገለጠው እንረዳለን። የውጭ ምስክር ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሁሉ በአንድ ድምፅ የ፬ኛው ወንጌል ጸሐፊ ዮሐንስ እንደሆነ መስክረው ጽፈዋል።

፲/ የመጽሐፉ ዓላማ ፥ የዮሐንስ ወንጌል ዓላማ

የክርስቶስን መለኮታዊ ባሕርዩን ለማጉላት ነው ፤ ምክንያቱም ሌሎች የስውነቱን፥የልደቱን፥የሕማሙን፥የሞቱን ነገር ሲናገሩ እርሱ ደግሞ ፍጹም አምላክነቱን ለመግለጥ ነው ፤ ስለዚህ ደረቅ ቃልን ቀዳሚሁ ብሎ ጀመረ። እርሱ ራሱ እንደገለጠው ግን ይኸ የተጻፈው ኢየሱስ የተባለው ክርስቶስ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ በስሙም አምናችሁ የዘለዓለም ሕይወትን ታገኙ ዘንድ ተጻፈ ሲል ዓላማውን ገልጦ ይናገራል (ዮሐ.፳ ፥ ፴፩)።



www.ethiopianorthodox.org

፬ኛ/ የተጻፈበት ዘመን ፤ የዮሐንስ ወንጌል በጣም ዘግይቶ ብዙም ቆይቶ እንደተጻፈ የቤተ ክር ስቲያን አባቶች ሁሉ በአንድ ድምፅ ይመሰክራሉ ።

እንደኛ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ግን ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ጌታ በዐረገ በ፴ ወይም በ፴፩ ዓመት ነው። ኔሮን ቄሣር በነገሠ ደግሞ ፯ኛው ዓመት ተፈጽሞ፣ ፰ኛው ሲጀመር ነው (መቅድመ ወንጌል)።

## ምዕራፍ ፯ የሐዋርያት ሥራ ፤

፩/ ጸሐፊው ፤ ይኸን ፪ኛ የታሪክ ክፍል የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ የጻፈ፡፫ኛውን ወንጌል የጻፈ ቅ/ሉቃስ ነው ። በሁለቱም መጽሐፍ መቅድም ላይ አንድ ዓይ ነት ቃል ይጠቀሳል አንድ ዓይነት ሐሳብም ያቀርብ ልናል ።

ራሱ ጸሐፊው በሐዋ/ሥራ መቅድም ላይ አስቀ ድሞ ወንጌሉን እንዳጻፈ ይኸንንም በዚያ መሠረት ለመጻፍ እንደጀመረ ኀልጦ ጽፏል (የሐ.ሥራ ፩፣ ፩—፪) ።

የሉቃስ ወንጌል ቃል አገባብ፣የዓረፍተ ነገር አሰካክ ከሐዋርያት ሥራ አጻጻፍ ስልት ጋር ተመሳሳይነው፤ ስለዚህ ወንጌሉንም፣የሐ. ሥራንም የጻፈ ሉቃስ እንደ ሆነ የታመነ ነው ።

፪/ የመጽሐፉ እውነተኛነት ፤ ይኸን መጽሐፍ የጻፈ ቅ/ሉቃስ እንደሆነ ከላይ ክሰጠ፟ው ማስረጃ ሌላ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሁሉ በአንድ ድምፅ መስክረዋል ።



የጻፈበትም ዓላማ ልክ እንደ ወንጌሉ ነው ፤ ቴዎፍሎስ የተባለ መኰንን ለምናት እርሱን ለማስረ ዳት ከመነሻው ጀምሮ ተርኮ ለማስረዳት ነው ። በእ ውነትም ስለ ክርስቲያን ሕይወት፣ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከመሠረቱ ጀምሮ የሚያስረዳው ይኸ መጽ ሐፍ ብቻ ነው ።

፫/ የተጻፈበት ዘመን፤ የሐ/ ሥራ መቼ ፣ ወዴት እንደተጻፈ ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው ። የሆነ ሁኖ ከ፷—፷፪ ዓመት ከክርስቶስ በኋላ እንደሆነ ይነ ገራል ። አንዳንዶችም ከ፹፫ ዓ/ም በኋላ እንደሆነ የሚናገሩ አሉ ።

## ምዕራፍ ፰ መልእክታት ፡

### ሐ/ የትምህርት ክፍል ፤

የትምህርት ክፍል የሚባሉት በመልእክት መልክ የተጻፉ ቅዱሳን ሐዋርያት ትምህርት ያስተላልፉባቸው ናቸው ። እነዚህም መልእክታት ለቤተ ክርስቲያን፡ ለሀገር ፣ ለግል ሰዎች የተጻፉ ናቸው ። እንዲሁም ጥቂቶች መልእክታት ለጠቅላላው ክርስቲያን ሕዝብ (ቤተ ክርስቲያን) የተላኩ ናቸው ። እነዚህ በመጨ ረሻ የተጠቀሱት መልእክታት ግን የተለየ ክፍል የሌ ላቸው ሁሉንም በአጠቃላይ ስለሚመለከቱ፡ አጠቃ ላይ መልእክታት ተብለው ይጠራሉ ።

በነዚህም የትምህርት ክፍል በተባሉት መልእ ክታት ሐዋርያት በጠቅላላው ስለ ሃይማኖት ጊዜውን የተከተለ ምክር ፣ ስለ ሥነ ምግባር፣ ስለ ማኅበራዊ



www.ethiopianorthodox.org

ኑሮ፣በተለይም ከዕለት ወደዕለት እያደገ የሚሔደው ክርስቲያናዊ ማኅበር የራሱ የሆነውን መልክ ይዞ እን ዲገኝ ከፍ ያለ ማስጨንቀቂያን የሚሰጥ ነው ።

እነዚህ ለትምህርት የተመደቡት መልእክታት የሚከተሉት ናቸው ፤

ሀ/ አሥራ አራት የጳውሎስ መልእክታት ናቸው እነርሱም ፤

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩/ | ወደሮሜ ሰዎች የተላከው | | | | ፲፮ | ምዕራፍ | ያለው |
| ፪/ | » ቆሮንቶስ | » | » | ፩ኛ | ፲፮ | » | » |
| ፫/ | » ቆሮንቶስ | » | » | ፪ኛ | ፲፫ | » | » |
| ፬/ | » ገላትያ | » | » | — | ፮ | » | » |
| ፭/ | » ኤፌሶን | » | » | — | ፮ | » | » |
| ፮/ | » ፊልጵስዮስ | » | » | — | ፬ | » | » |
| ፯/ | » ቆላስይስ | » | » | — | ፬ | » | » |
| ፰/ | » ተሰሎንቄ | » | » | ፩ኛ | ፭ | » | » |
| ፱/ | » ተሰሎንቄ | » | » | ፪ኛ | ፫ | » | » |
| ፲/ | » ጢሞቴዎስ | | » | ፩ኛ | ፮ | » | » |
| ፲፩/ | » ጢሞቴዎስ | | » | ፪ኛ | ፬ | » | » |
| ፲፪/ | » ቲቶ | | » | — | ፫ | » | » |
| ፲፫/ | » ፊልሞና | | » | — | ፩ | » | » |
| ፲፬/ | » ዕብራውያን ሰዎች | | » | — | ፲፫ | » | » |

ለ/ አጠቃላይ መልእክታት የሚባሉት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩/ | የያዕቆብ | መልእክት | | ፭ | ምዕራፍ | ያለው |
| ፪/ | የጴጥሮስ | » | ፩ኛ | ፭ | ምዕራፍ | ያለው |
| ፫/ | የጴጥሮስ | » | ፪ኛ | ፫ | » | » |
| ፬/ | የዮሐንስ | መልእክት | ፩ኛ | ፭ | ምዕራፍ | ያለው |
| ፭/ | » | » | ፪ኛ | ፩ | » | » |
| ፮/ | » | » | ፫ኛ | ፩ | » | » |
| ፯/ | የይሁዳ | » | | ፩ | » | » |



## ምዕራፍ ፱ ራእየ ዮሐንስ

### መ/ የትንቢት ክፍል

ወንጌላዊ ዮሐንስ የጻፈው ራእይ ትንቢት ተብሎ ይጠራል ።

ዮሐንስ ፩ ወንጌል ፣ ፫ መልእክታት ፣ ፩ ራእይ በጠቅላላው አምስት መጻሕፍትን ጽፎ አቅርቦልናል ። በዚህ ራእዩ የቤተ ክርስቲያንን አቸናፊነት በልዩ ልዩ መልክ ጽፎልን እናገኛለን ። እንዲሁም ዋናው ዓላማው ስለ ክርስቶስ ፪ኛ መምጣት ስለሆነ የአመጣጡን መልክ አስቀድሞ የሚሆኑትን ነገሮች ሁሉ ተራ በተራ ይገልጥልናል። ይኸንንም ራእይ ያየውና የጻፈው በፍጥሞ ደሴት ተግዞ ፺፭ ዓመት በተቀመጠ ጊዜ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ ከምዕራፍ ሌላ ንኡስ ምዕራፍ፣ቍጥር አለው፤ ይኸም በጣም ቆይቶ የተወሰነ ነው ። እንዲሁም እያንዳንዱን ቃል ወይም ዐረፍተ ነገር ቈጥረው የሚያስቀምጡ አሉ ። ዋናው ዓላማቸው ግን በቅዱስ መጽሐፍ ላይ ሌላ ባዕድ ቃል ፣ ዐረፍተ ነገር እንዳይጨመርበት ለመጠበቅ፣ ወይም ለመከላከል ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍናቍጥሩ ግን ጥልቅ ጥናት ለማጥናት የሚረዱ ናቸው ። እንዲሁም እያንዳንዱን ኃይለ ቃል በቍጥር ለይቶ የተመለከቱት እንደሆነ ለጥናቱ ውጤት ይኖረዋል ፤ ስለዚህ ቅ/መጽሐፍን የሚያጠኑ ሁሉ ምዕራፉን ፣ ቍጥሩን ፣ ኃይለ ቃሉን ለይቶ በማወቅ መሆን አለበት ።



## ዐቢይ ክፍል ፩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

### መ ቅ ድ ም

ቤተ ክርስቲያን ስንል በጌታ በኢየሱስ የሚያምነውን ሕዝብ ሁሉ በአጠቃላይ በመጥራት ነው ፣ ይኸም ማለት ጌታ ኢየሱስን የቤተ ክርስቲያኗ መሥራች መሪዋም ፣ አስተማሪና የዓለሙ መድኅን እርሱ እንደሆነ አምኖ የተቀበለው ሁሉ ነው ማለት ነው ። እነዚህም ክርስቲያኖች አንድ ዓይነት እምነትና ትምህርት ያላቸው ፣ የአንድ ምሥጢር ተሳታፊነት ያላቸው፣ በአንድ ቤተ ክርስቲያን መሪ የሚተዳደሩ መሆን አለባቸው ። ይህም የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ውርስ መሠረት ፀአንብሮተ እድ የተሾመ መሆን አለበት ።

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ እንደ መመሥረቷ አምላካዊት ወይም መንፈሳዊት ድርጅት ናት፣ ስለዚህ አማንያኑን ሁሉ በሕፅኗ የምትይዝ ፣ ምሥጢራትን ሁሉ የምትጠብቅ የጸጋ መዝገብ ናት ።

ቤተ ክርስቲያን ይኸን የመሰለች መንፈሳዊት ድርጅት ስትሆን ስለ አመሠራረትዋና ጠቅላላ ሕይወትዋ፣እንዴትም ተግባሯን እንደምትፈጽም ፣ ከተመሠረተችበት ጊዜ አንሥቶ ያደረገችውን ጉዞ ፣ የገጠማትንም ችግር ሁሉ የሚገልጥ ታሪክ አላት ። ቤተ ክርስቲያን በተቋቋመችበት ዓላማ መሠረቷን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ያሳየችውን ውጤት



www.ethiopianorthodox.org

በመካከልም በነበረው ዐረፍተ ዘመን የተገኘው መሻሻል ጉዳት ወይም ጥቅም መታወቅ አለበት ፣

ይኸ ሁሉ በታሪክ መልክ መገለጥ አለበት ፣ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስንል ይኸን ሁሉ አጠቃሎ እንደጊዜው እንደየሁኔታውም ገልጦ የሚያስረዳ ነው

አሁንም የቤተ ክርስቲያንን ጠቅላላ ሁኔታ በአጭሩ የሚያሳይ ይኸን አጭር ጽሑፍ እንደሚከተለው አበረክታለሁ ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ



## ክፍል ፩ ጠቅላላ ታሪካዊ መግለጫ

### ምዕራፍ ፩ የፍልስጥኤም ጂኦግራፊ በአጭሩ፣

፩/ ሀገር ፣ እሥራኤላውያን የኖሩበት፣የሠሩበት፣ ታሪክን ያተረፉበት አገር ምድረ ፍልስጥኤም ይባላል ፤ እንዲሁም ምድረ ከነዓን ይባል ነበር። ራሳቸው እሥራኤል ግን ቅድስት ሀገር ወይም የተስፋ ሀገር ይሏታል ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአባቶችና ለሙሴ ይኸችን ሀገር እሥራኤል እንደሚወርሷት አስቀድሞ ተስፋ ሰጥቷቸው ነበርና ።

ይኸችም ፍልስጥኤም የተባለችው ሀገር በጣም ትንሽ የሆነች ሀገር ናት ፣ እርሷም በታናሽ እስያ ደቡብ የምትገኝ ናት ፣ በምሥራቅ የዮርዳኖስ ወንዝና በምዕራብ በኩል ደግሞ የሚድትራንያን ባሕር ያዋስኗታል ፤ ብዙ ታላላቅ ታናናሽም ተራራዎች፣ ኮረብታማ ቦታዎች ይገኙባታል ። በዚህ አንፃር ደግሞ ዝቅተኛ ጉድጓዳም ቦታዎች ይገኙባታል ።

፪/ ተራራዎች ፣ ታላላቆቹ ተራራዎች በሶርያ በኩል በሚገኘውጠረፍ ጐላን ተራራ ይገኛል፣ ወደ ቤይሩት ጠረፍ ደግሞ የሊባኖስ ተራራ ፣ይገኛል ። ይኸም ተራራ አስደናቂና ታላላቅ በሆነ ዝግባ (ዓርዘ ሊባኖስ፣ ዕፀ ቄድሮስ) በተባለ ዛፍ ቀሸፍኖ



www.ethiopianorthodox.org

ይገኝ ነበር ። ከዚህ ከሊባኖስ ተራራ ጋር እንደ ሠንሠለት ተያይዞ ወደ ሰሜን በኩል ሲል የአርሞንኤም ተራራ ይገኛል ፣ ከዚህም ወደ ሰሜን በኩል ደግሞ የታቦር ተራራ ይገኛል ።

በሊባኖስ ደቡብ የቀርሜሎስ ተራራ ይገኛል፤ ይኸም ተራራ ከሌሎች ተራራዎች ይልቅ ብዙ ምንጮች ምንጮች ይገኙበታል ፤ ወደ መካከሉ ገባ ሲሉ ደግሞ የገሪዛን ተራራ ይገኛል ። ራሷ ከተማዋ ኢየሩሳሌም የምትገኝበት ቦታ ከፍታ ያለው ስለሆነ እንደ ተራራ ይቈጠራል ። በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ወይም አካባቢ ደብረ ዘይት ፣ ደብረ ጽዮን ፣ (ኢየሩሳሌም) ሞሪያ ፣ ጎልጎታ የሚባሉ ኮረብታዎች ይገኛሉ ።

ተራሮችና ኮረብቶች በዚህ መልክ ታናናሾችም ሌሎች ሲኖሩ ለእርሻ ፣ ለከብት ርባታ የሚሆኑ ሜዳ ዎች በመጠኑ ይገኛሉ ።

፫/ የፍልስጥኤም ባሕሮችና ወንዞች ፤ የፍ ልስጥኤም ታላቁ ባሕር የሎጥ ባሕር ፣ ምዉት ባሕር ፣ የጨው ባሕር እየተባለ የሚጠራው ነው ። በዚህ ባሕር ውስጥና በዙሪያው ሕይወት ያለው ነገር ከቶ አይኖርም ። ዙሪያው በድኝና በቅጥራን (ዝፍት) የተሞላ ስለሆነ ምንም ነገር አይኖርበትም ።



በዚህ ቦታ ቀደም ብሎ ሰዶምና ገሞራ የተባሉ ታላላቅ ከተሞች እንደነበሩበት ይታወቃል ። እንዲሁም ተወዳዳሪነት የሌለው ለምለም ቦታ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል (ዘፍ.፲፫.፲) ። ሌላ የገሊላ ባሕር የሚባለው በ፪ኛ ደረጃ ይገኛል ፤ ይኸም ባሕር አንዳንድ ጊዜ ጌንሳሬጥ ይባላል ፤ እንዲሁም ባሕረ ጥብርያዶስ ይባላል ። እነዚህ ሁለቱ ባሕሮች በዮርዳኖስ ወንዝ አማካይነት ይገኛሉ ።

፬/ የፍልስጥኤም ወንዞች ፤ በፍልስጥኤም ውስጥ ከሚገኙ ታላላቅ ወንዞች ዮርዳኖስ ፣ ይኸም ወንዝ ከአርሞንኤም ተራራ ይነሣና ወደ ጌንሣሬጥ ባሕር ይፈሳል ፤ መጨረሻ መድረሻው ደግሞ የሎጥ ባሕር ይሆናል ። ይኸ ወንዝ ታሪካዊ ወንዝ ነው ። ብዙ ጥቅምንም የሰጠና የሚሰጥ እንደ ቅዱስም ወንዝ የሚታይ ነው ። በተለይም መድኃኒታችን ኢየሱስ ከተጠመቀበት በኋላ ቅድስና ያለው ወንዝ ሆኖ ይገኛል ።

ሌሎች ወንዞች ቂሶን የተባለ ከታቦር ተራራ የሚመነጭ ይገኛል ። እንዲሁም ቃና የተባለው ወንዝ ከገሪዛን ተራራ የሚመነጭ አለ ። ሶሬክ የተባለው ወንዝ ደግሞ ከኬብሮን ኮረብታ የሚመነጭ አለ ። እነዚህ ሁሉ ወደ ሜዲትራኒያን ባሕር የሚፈሱ ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

ከኢየሩሳሌም የሚነሣው ቄድሮስ የተባለው ወንዝ ብቻ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ይገባል ።

ፎ/ <u>የዓየሩ ሁኔታ</u> ፤ የፍልስጥኤም ዓየር ዝቅተኛው ቦታ ሁሉ ፀጣም ሞቃት ነው ፤ ያቃጥላል ፤ በየተራሮች ላይ ግን ለስላሳና ተስማሚ ዓየር ይገኛል።

በዚህ ፀዝቅተኛ ቦታ ሁሉ አትክልትይተከላል፤ እርሻ ይታረሳል ፤ ከብት ይረባል ፤ መልካም ውጤትንም ይሰጣል ። በተለይ ወይን ፥ በለስ በጠቅላላው ፍራፍሬን በተሻለ መልክ ይሰጣል፤በበለጠ ግን ወይራ (ዘይት) ይሆናል ። በኮረብቶችም ልዩ ልዩ የሀገሩ ፍራፍሬዎች ይገኙበታል፤የተባረከ ሀገር ሁኖ ሁሉ ይገኝበታል ። በመጀመሪያም እግዚአብሔር ለአብርሃም ወተትና ማር ወደሚፈስበት የተስፋ ምድር አገባሃለሁ ብሎት ነበር ። ዕብራውያንም ይኸን ይዘው አገራችን መዓርና ወተት የምታፈስ ናት ይሏታል ።

## <u>ምዕራፍ ፪ በፍልስጥኤም ምድር ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦችና አስተዳደራቸው ፤</u>

በዚሀች ፍልስጥኤም ወይም ከነአን እየተባለች በምትጠራው አገር በቊጥር የበዙ በጎሣ የተለያዩ ፥ ፀልማድና በባሕርይ የተለያዩ ሕዝቦች ይኖሩ ነበር ፤ ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶችን እናነሣለን፤ ከነናውያን፥አማሌቃውያን ፤አሞራውያን፥ሞአባውያን፥ኢያቡሳውያን



የሚሉና ሌሎችም ሕዝቦች እንዲሁም ነበሩ ፤ሁኖም ፀአንድ ላይ ከነናውያን ተብለው ይጠሩ ነበር ።

እነዚህም ሕዝቦች አንዱ ሌላውን እንደጠላት ይመለከተው ነበር ፤ ይሁን እንጂ በዚህ መልክ ተለያይተው በሚኖሩበት ጊዜ አብርሃም ከዘመዶችህ ተለይ፤ከአገርህ ውጣ፤እኔ ወደ ማወርስህ ምድር ናና ተቀመጥ ተብሎ ተጠርቶ ወደ ከነአን መጣ(ዘፍ.፲፪.፩) ። ሁኖም መጻተኛ፥ስደተኛም ሁኖ ኖረ እንጂ በተነገረለት ተስፋ መሠረት ያገኘው ነገር አልነበረም ። ልጁ ይስሐቅ ፥ ያዕቆብም እንዲሁ ከሀገሩ ሕዝብ ጋር በመግባባት ብቻ ኖሩ እንጂ አሁንም መብት ያልነበራቸው ስደተኞች ነበሩ ።

ፀያዕቆብ ጊዜ ግን የባሰውን ከከነአን ተሰደው ወደ ግብጽ ሄዱ በዚያም ፬፻፴ ዘመን በግብጽ አገር ባሪያዎች ሁነው ኖሩ ። ይሁን እንጂ ጊዜው ሲደርስ ከግብጽ ባርነት ነጻ ወጡና ለአባቶቻቸው የተነገረው ተስፋ በእነርሱ ተፈጽሞ የአገሯ ባለቤት፥ የርስቱ ወራሽ ዕብራውያን የአብርሃም ዘሮች ሆኑ ።

ይኸችን ሀገር ዕብራውያን እንደወረሷት ወዲያውኑ በ፲፪ ዕጣ ተካፈሏት ፤ በ፲፪ቱ ነገደ ሥራኤል ልክ፤እነርሱም ርእስ ከተማቸውን ኬብሮን አድርገው ለብዙ ዘመን ኖሩ ። በዳዊት ጊዜ ግን ኢየሩሳሌም ተመሠረተችና የእሥራኤል ዋና ከተማ ሆነች ።

ምንም ርስቱ በ፲፪ቱ ነገደ እሥራኤል ልክ ተከፍሎ ቢቆይም በአስተዳደር በኩል ፍልስጥኤም በአራት ክፍል ተከፍላ ኑራለች ፤ እነዚህም ፥ ይሁዳ ፥ ሰማርያ ፥ ገሊላ ፥ ፔሪያ የተባሉ ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

በጌታችን በኢየሱስ ጊዜ ግን ፩ኛ ክፍል ኤዶሚያስ የተባለው ተጨምሮ ነበር ።

ኢየሩሳሌም የተባለችውን ከተማ ንጉሡ ዳዊት ከኢሎፍላውያን ነጥቆ ያዘና ከተማ እንድትሆን አደረጋት ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስራኤል ዋና ከተማ ሁና ትኖራለች ። ይኸችም ከተማ ከኮረብታ ላይ የተሠራችና ምሽግም የተሠራላት ስለነበረች ጽዮን ብሎ ሰይሟታል ፤ ከዚያን ጀምሮ ደብረ ጽዮን እየተባለች ትጠራለች ፤ ሕዝቦቹም ጽዮናውያን እየተባሉ ይጠራሉ ።

ኢየሩሳሌም ማለት የሰላም ከተማ ማለት ነው፤ በመጨረሻ ጊዜ ግን የዓለሙ መድኃኒት ኢየሱስ ተሰቅሎ ሰላምን መሥርቶባታል ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የክርስቲያኑ ሕዝብ ቅድስት ከተማ ናት ።

## ምዕራፍ ፫ የዓለም ሃይማኖትና ሥነ ምግባር ፤

ጌታ ኢየሱስ በሚወለድበት ዘመን አቅራቢያ የኢየሩሳሌምንና አካባቢዋን አገር ሁሉ ይገዙ ያስተዳድሩም የነበሩት ሮማውያን ነበሩ። በዚያን ጊዜም በአካባቢው የነበር ሕዝብ ሁሉ ከዕብራውያን በቀር ሁሉም የተለያየ ፣ በቍጥርም የበዛ ጣዖት ያመልክ ነበር ።

ሁሉም እንደመሰለው፥ እንጨት ጠርቦ፣ ድንጋይ አለዝቦ ፣ ሸክላ ሠርቶ ያመልክ ነበር ፤ ሌላው ደግሞ ነፋሱን፥ ባሕሩን ፣ እሳቱን፣ ፀሐዩን ፣ ጨረቃውን እንዲሁም ዛፉን፥ እንስሳውን፥ የመሳሰለውን ሁሉ ያመልክ ነበር ። ለእነዚህም አማልክት የሰው መሥዋዕት፡ የሰውም ቅርጽ በመስጠት ያመልኳቸው፥አገልግሎትም ያቀርቡላቸው ነበር ። ሰዎችም እንደመሰላቸው ለአማልክት የሰው ጠባይ እየሰጡ እንደሚያገቡ ፣እንደሚራቡ ፣ እንደሚቆጡ፥ እርስ በርሳቸውም ጦርነት እንደሚገጥሙ ይናገሩ ነበር ።

የሰውም ዕድል ከአማልክት ምሕረትና ቁጣ የተነሣ እንደሚሆን ያምኑ ነበር፤ ስለዚህ አንድ ሰው ክፉ ነገር ቢገጥመው አማልክት እንደተቆጡት ፣ መልካም ነገር ሲገጥመው ደግሞ አማልክት ዕድሉን እንዳቃኑለት ይናገሩ ነበር ።

ለጣዖት መሥዋዕት ይሠዉ ፣ ወርቅና ብር ስጦታ ይሰጡ ነበር ፤ ከዚያውም ዘንድ የከበረውን ፣ ያማረውን እየመረጡ ይሰጡ ነበር ።

ሀ/ የሕዝቡ ሥነ ምግባር ፣ አምልኮቱ የጣዖት እንደመሆኑ በሐሰት ጣዖታትን እንደሚያመልኩ ምግባሩም ሐሰት ፣ ክፋት ፣ ራስን መውደድ ተግባር አድርጎ ይዞ ነበር ፤ በዚህ ጊዜ እውነት የተባለው ተረስቶ ነበር ፤ እንዲያውም ለእውነት ቦታ ከቶ አልነበረውም ። የባርነት፥ ያጭቆና አገዛዝ በዓለም ላይ ጐልቶ ይታይ ነበር ፤ ባሮችን እንደ ዕቃ ወይም እንደ ከብት ይገዟቸው ይሸጧቸውም ነበር፤ ለጤናቸው፥ለኑሯቸው ምንም ጥንቃቄ አይደረግላቸውም ነበር ፤ እንዲያውም ሰው አይመስሏቸውም፤የሰውም ግምት



www.ethiopianorthodox.org

አይሰጣቸውም ነበር ። እንግዲህ አንዱ ቀለል አንዱም ክበድ አድርጎ በመያዝ ይለያዩ እንጂ፣ በሮማውያን ይዛዛ የነበረው ሕዝብ ሁሉ በሃይማኖትም በምግባርም ይኸን የመሰለ የኑሮና የሃይማኖት መዛባት ይታይ ነበር ።

## ምዕራፍ ፩ የእሥራኤል እምነትና ማኅበራዊኑሮ

ከክርስቶስ መምጣት በፊት እውነተኛውን አምላክ ያመልክ የነበረው የእሥራኤል ሕዝብ ብቻ ነበር፤ እስራኤላውያን አንዱን አምላክ ብቻ ሲያመልኩ ኤምልኮቱን ለጣዖት አይሰጡም፤ እውነቱንም በሐሰት አይለውጡም ነበር ።

እሥራኤላያውን ለፈጣሪያቸው ይታዘዙ፣ ሕጉንም ይጠብቁ ነበር ፤ እግዚአብሔርም በሙሴና በሌሎችም ነቢያት አማካይነት ያነጋግራቸው መመሪያም ይሰጣቸው ነበር ።

እግዚአብሔርና የእሥራኤል ሕዝብ ስምምነት፣ ቃል ኪዳንም ነበራቸው ፤ ይኸም እነርሱ ሕጉን ቢጠብቁ እርሱም እንደሚጠብቃቸው ነው ።

እሥራኤላውያን ብሮማውያን አገዛዝ ሥር ይተዳደሩ እንጂ የውስጥ ነጻነታቸው የተጠበቀ ነበር ፤ ይኸም ማለት በራሳቸው መሳፍንት ፣ ነገሥታት ይተዳደሩ ነበር ። በሃይማኖት በኩል ደግሞ ፸፩ ዓባል የአሉበት ጉባኤ (ሴኔድር) እየተባለ በሚመራ ሕግ ይተዳደሩ ነበር ፤ የዚህም ሴኔድር ሊቀ መንበር ይሆን የነበረው የየጊዜው ሊቀ ካህናት ነበር ።



ዕብራውያን ይኸን የመሰለ የራስ በራስ አስተዳደር ይኑራቸው እንጂ የላይ አስተዳደሩ ኀላፊ የሮማ መንግሥት ስለሆነ በሮማውያን ሥልጣኔና ወደ ሮማውያን ሥርዓተ ማኅበር እየተሳቡ ቀስ በቀስ ከሥነ ምግባር መውጣታቸው ከሃይማኖትም መና ወጣቸው አልቀረም ፤ በዚህም አምላካቸውን አሳዘኑ ። እሥራኤላውያንበራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ አንዱ ከሌላው የተለያየ የሃይማኖት ድርጅት እያቋቋመ እንደፍላጎቱ መንፈሳዊ አምልኮቱን ይፈጽም ነበር ።

በዚህ መልክ የተለያዩ ሃይማኖታውያን ድርጅቶች ያሏቸው ክፍሎች ነበሩ፤እነርሱም ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን፣ኤሴይ፣ ኤፂአኒቴ የተባሉና ሌሎችምነበሩ።

ሀ/ ፈሪሳውያን፤ እነዚህ ወገኖች አፍአዊውን ትእዛዝ ብቻ በመጠበቅ የሕግ ፈጻሚዎች መስለው የሚታዩ ፣ እንደነርሱ እርምጃ የማይሄደውን የሚወቅሱ የሚከሱ ነበሩ ። በነርሱ ፊት ሌላው የረከሰ፣እነርሱ ብቻ የተቀደሱ ሁነው የሚታዩ ነበሩ ፤ ለዕብራውያንም ሃይማኖት ተጠያቂና ኃላፊ እነርሱ ብቻ እንደሆኑ የሚያምኑ ናቸው ።

በእውነተኛው መንገድ የሄድን እንደሆነ ግን ግብዞችና አስመሳዮች ነበሩ ፤ ጥፋታቸውን በውስጥ ሸፍነው በውጭ ግን ጻድቅ መስለው የሚታዩ ነበሩ ። እነርሱን የሚመስሉ ወይም እነርሱን የሚከተሉ ጸሓፍት ሕዝብ የተባሉና የሕግ ሰዎች የቀበሉ ነበሩ ። እነዚህም በበኩላቸው ፈሪሳውያን



www.ethiopianorthodox.org

የሚፈልጉትን እንደነርሱ ጠባይ ሕግን ይተረጉሙ፡ ከነርሱም ጋር ይተባበሩ ነበሩ ።

፪/ <u>ሰዱቃውያን</u ፤ እነዚህ ወገኖች ደግሞ በጣም ከዕብራውያን ውስጥ ከፍ ያለ ሀብት የነበራቸው ፤ ከፈሪሳውያን በንድ ተቃራኒ ሆነው የቀረቡ ነበሩ ። እነዚህ ሰዱቃውያን የሙሴን ሕግ በራሳቸው አስተ ያየት ይተረጉሙ የነበሩ ናቸው ። ለምሳሌ ትንሣኤ ሙታንን ፣ የነፍስንም ሕያውነት ይክዱ ነበር ፤ የመ ላእክትን ህልውና የመንፈሳውያንንም ሁሉ ህልውና ይክዱ ነበር፤ እነዚህም የዘመኑ ቂሳውያን ነበሩ(ማቴ፥ ፳፪፥ ፳፫) ።

፫・<u>ኤሴያውያን</u>፤ እነዚህ ወገኖች ደግሞ የመናንያን ማኅበር ነበሩ ፤ እነዚህ ያላቸውን ሁሉ ሀብትእየተዉ፣ ወደ በረሃ የሚገቡ ፣ በዚያም በጾምና በጸሎት በትህር ምት የሚኖሩ፣ ሹመት ሽልማት የማይፈቅዱ፣ ሀብት ንብረት የማይወዱ ነበሩ ። ዮሐንስ መጥምቅ የዚህ ዓይነቱ ማኅበር ወገን እንደነበር ይነገራል ።

፬/ ኤቢአኒቲ፤ ኤቢአኒቲ ማለትም ደሀ ፤ ድህ ነት ማለት ነው ፤ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች እንደ ፫ኛው ክፍል <u>ድህነትን</u> ገንዘብ የሚያደርጉ መናንያን ደናግሎችም ነበሩ። እነዚህም ወገኖች በማኅበር ይኖሩ ነበር ፤ የነዚህ ወገኖች ማኅበር ይሠራበት የነበረው አሁን በምርመራ በሙት ባሕር አጠገብ የተገኘው ኩምራን የተባለው ፍራሽ ነው ። ከነዚህም ሌላ የመ ናንያን ማኅበር እንደ ናዝራውያን ያሉ ነበሩ ።



## ምዕራፍ ፩ የመሢሕ መምጣት ተስፋ ፡

ዓለም በዚህ በተመሰቃቀለ ማኅበራዊ ኑሮ ሲኖር ከቶ ደስ ብሎት በኑሮው አምኖበት የሚኖር አልነበረም ። ብዙ ነቢያት ስለ መሢሕ መምጣት አስፋፍተው ተናግረው ነበር ፤ ይህ ትንቢት የተጠ በቀው በእሥራኤል ብቻ በመሆኑ የእሥራኤል ተስፋ አሁንም መሢሑ መጥቶ ከአለባቸው ችግር እንዲ ያድናቸው፣ ከሮማውያን የባርነት ግዛት ነጻ እንዲያ ወጣቸው ይጠብቁ ነበር ።

አረማውያን ደግሞ የሰውን ጨለማነት ፡ የኃጢ ኣቱን ብዛት ከቀን ወደቀን እየባሰ መሄዱን እያዩ ከአምላክ አንድ ምሕረት ከአልተላከ በቀር በሰው ኃይል ድኅነት ሊደረግ የማይቻል እንደሆነ ያውቁ ነበር ።

የእስራኤል ተስፋ ሙሉ ቢሆንም መሢሕም እንደሚመጣ ተስፋ ቢያደርጉም የመሢሕን መም ጣት ይጠባበቁት የነበር አንድ መሢሕ ተነሥቶ አገሯን ከባዕድ አገዛዝ ነጻ አውጥቶ የዳዊትን፡የሰሎ ሞንን መንግሥት መልሶ በሰላም የሚያስተዳድር አድርገው ይጠብቁት ነበር እንጂ አምላክ ወልደ አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ዓለምን እንደሚያ ድን አያምኑም ነበር ።

የሰው ወገን የሆነው ሁሉ ደክሞት መኖርን ስል ችቶ ሁሉም በየበኩሉ ይቆዝም ነበር ። ዓለም በዚህ መልክ በሚገኝበት በጭንቁ ጊዜ የዓለሙ መድኃኒት የሆነው ኢየሱስ በሥጋ ተገለጠ ማለት ሰው ሁኖ ሥጋንም ለብሶ ተወለደ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፩ የዓለም ድኅነት ፤

### ምዕራፍ ፩ የጌታችን የኢየሱስ ልደት ፤

ይኽ ዓለም በጭንቅ በችግርም ሳለ የደከመው አጋዥ፣የታመመው ፈዋሽ፣በሚፈልግበት ጊዜ ሁሉን የቀን ጨለማ ይዞት በጨለማና በሞት ጥላ ሥር ሲመላለስ ሳለ በድንገት አንድ ታላቅ ብርሃን ወጣ ብርሃኑም ለሁሉ ሆነ (ኢሳ፣ ፱፥፪ )። ይኸውም የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ መወለድ ነው ።

እግዚአብሔር መንፈሱን የሚያሳርፍበት የበቃ ሰው ባልነበረበት ጊዜ በነፍስና በሥጋ ንጽሕት የሆነች፣ የእግዚአብሔር ቃልን በማሕፀኗ ለመሸከም የበቃች፣በናዝሬት ከተማ የምትኖር አንዲት ድንግል ነበረች፤ የዚህችም ድንግል ስሟ ማርያም ነበር(ሉቃ፥ ፩፥፳፯) ።

እግዚአብሔር የዓለሙ ድኅነት ፈቃዱ ስለሆነ ለዚህ ዓለም ድኅነት ምክንያት ይኸችን ድንግል መረጠ ፤ ማለት መሰላል መውጫና መውረጃ ወይም ድልድይ መሸጋገሪያ አደረጋት ። ስለዚህም በፊቱ የሚቆመውን ባለሟሉን መልአክ ገብርኤልን የምሥራች ይናገር ዘንድ ወደ እርሷ ላከ ። መልአኩም ወደዚች ድንግል በደረሰ ጊዜ «ጸጋን ያገኘሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ። አንች ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ» አላት(ሉቃ ፩፥ ፳፰) ። ቅ/ማርያምም በነገሩ ተገረመች ወንድ ሳይኖራት በድንገት ይኸን የመሰለ የምሥራች ስለነገራት ።



ቅ/ማርያም እውነተኛ ስለነበረች በውዳሴ ከንቱ አልተቀበለች አልተጠለፈችም ፤ ስለዚህ ወዲያውኑ አልተቀበለችውም ነበርና ወንድ የማላውቅ ስሆን ይኽ እንደምን ይሆናል ? ብላ ጠየቀችው ፤ መልአኩም የተላከበት ነገር ነውና በብዙ አስረጅ አስረዳትና ማሠሪያውን «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም» አላት ። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ቅ/ማርያምም በእርግጥ ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለምና እነሆ የእግዚአብሔር ገረዱ አለሁኝ፤እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለችው (ሉቃ፩፥ ፴፰) ። በዚህ ጊዜ አካላዊ ቃል በማሕፀኗ ተቀረጸ ።

<u>፪/ የኤልሳቤጥ ምስክርነት</u> ፤ ቅድስት ማርያም ይኸን የምሥራች ቃል እንደሰማች ወዲያውኑ እኅቷ ኤልሳቤጥ ወደምትገኝበት ወደ ይሁዳ ተጓዘች ። ከኤልሳቤጥም ዘንድ ደርሳ፣ ሰላምታ እንደተሰጣጡ፣ በኤልሳቤጥ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሞላባትና የመልአኩን ቃል በመድገም «አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ፤የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከነው»ብላ ብፅዕናዋን፣ቅድስናዋን፣የጌታምእናት መሆኗንተናገረች። ቅ/ ማርያም በሰውም በመልአኩም ከሁለት ወገን ምስክር ስላገኘች ለባለውለታው አምላክ ምስጋናን አቀረበች (ሉቃ፣ ፩፥ ፵፬—፶፭) ።

<u>፫/ የተስፋው ቃል መፈጸም</u> ፤ መሢሕ እንደሚመጣ የተነገረው ትንቢት የተቈጠረው ሱባኤ በተፈጸመ ጊዜ ማንም ባልጠረጠራት ዕለት ባልቈጠራት ሰዓት ድንገት ጌታ ተወለደ ።



www.ethiopianorthodox.org

በሮማ አውግስጦስ ቄሣር በነገሠ ፣ በሶርያም ቄሬኔዎስ ገዥ በነበረበት ጊዜ፣በኢየሩሳሌምና በአውራጃዎም ሄሮድስ በነገሠ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ እንዲቈጠር ቄሣር በሰጠው አዋጅ መሠረት የቅድስት ማርያምና የዮሴፍ አገር ይሁዳ (ቤተ ልሔም) ነበርና በአዋጁ መሠረት ሊቈጠሩ እንደወጡ ጌታብዚያ በቤተልሔም ተወለደ ። ለቈጠራ የመጣው ሕዝብ በዝቶ ቦታውን ሁሉ ይዞት ስለነበር፣እመቤታችንና ዮሴፍ ማረፊያ አጥተው በአንድ በረቱ እንደመፈሩ የጌታ ልደት በዚያው በበረት ሆነ ። ሁኖም አምላክ ነውና እንደእም ላክነቱ፣ ከእንስሳት ወገን ላምና አህያ እስትንፋሳቸውን ገበሩለት ።

የሰማይ ሠራዊት ደግሞ «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት፤ወሰላም በምድር ፤ ሥምረቱ ለሰብእ» እያሉ በምስጋና ተቀበሉት ። እረኞችም ከብርሃኑ ብዛት ፣ ከሰማይ ሠራዊት ምስጋና ድምፅ የተነሣ ይደነቁ ምስጋናም ያቀርቡ ነበር ።

እንዲሁም የጥበብ ሰዎች ከምሥራቅ ረጅም ጉዞ አድርገው መጥተው ሰገዱለት፤ወርቅ ዕጣን ከርቤም ገበሩለት ።

ቅ/ማርያም ግን የሆነውን ሁሉ ታስተውል በልቧም ትጠብቀው ነበር ፤ ታላላቅ ተአምራት ሊደረጉ አይታልቸና ፤ ይኸውም በኀቱም ድንግልና ፀንሳ በኀቱም ድንግልና መውለድ ፣ የሰማይ ሠራዊት መጥተው ምስጋና ማቅረብ ፣ እንስሳት እስትንፋሳቸውን መገበር ፣ እረኞች ምስጋና ማቅረብ ይኸ ሁሉ ተጠቃሎ ማየት ታላቅነቱን የሚገልጥ ነውና ።



## ፬/ የመቤታችንና የጌታ ስደት ወደግብጽ ፤

የምሥራቅ ሰዎች ሲመጡ የአይሁድ ንጉሥ የት ነው የተወለደው እያሉ የክርስቶስን ንጉሥነት እየመሰከሩ ስለመጡ ፣ ሄሮድስ ንጉሥ በሀገሩ ንጉሥ ሳይገድል አይነግሥ ፤ በኔ ላይ የሚሠለጥን እንዴት ያለ ንጉሥ ተወለደብኝ፣በማለት ጌታን ያጠፋ ዘንድ አሰበ ፤ ስለዚህም ወደ ግብጽ እንዲሰደዱ ምክሩን የሚለግስ መልአክ ከእግዚአብሔር ታዘዘ ። እርሱም በሌሊት በራእይ ለዮሴፍ አሳየው ተናገረም እንዲህ ሲል «ተነሣና እናቱንና ሕፃኑን ይዘህ በሌሊት ወደ ግብጽ ሽሽ ፤ ሄሮድስ ሕፃኑን ይገለው ዘንድ አለውና» አለው ።

የጥበብ ሰዎች ግብሩን ሰጥተው እንደተመለሱ ዮሴፍ ቅድስት ማርያምንና ሕፃኑን ይዞ በሌሊት ወደ ግብጽ ተሰደደ ። በዚያም ከቦታ ወደቦታ በመዘዋወር ፫ ዓመት ከመንፈቅ ቆየ ፤ ሄሮድስ እስከ ሞተበት ጊዜ ። ሄሮድስ እንደሞተ ያው መልአክ ለዮሴፍ ከግብጽ እንዲመለስ አመለከተውና ሲመለስ ወደ ይሁዳ በመሔድ ፈንታ በናዝሬት እንዲቆይ ሆነና ጌታ በዚያው አደገ ።

## ምዕራፍ ፬ የክርስቶስ የሕፃንነቱ ጊዜ ፤

ከግብጽ ስደቱ ከተመለሱ በኋላ ጌታም ቤተ ሰቦቹም መኖሪያቸው ናዝሬት ነበር ፤ ናዝሬትም የገሊላ አውራጃ ከተማ ነበረች ፤ ግን እንደሌሎቹ አውራጃ ከተሞች ዝነኛ አልነበረችም ፤ ዮሴፍም የእመቤ



www.ethiopianorthodox.org

ታችን እጮኛ የተባለው ፅብት ያለው ሰው አልነበ ረም ፤ ስለዚህ የፅለት ሲሳዩን ያገኝ የነበረው እን ጨት እየጠረበ ለቤት አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎ ችን እየሠራ በመሸጥ ነበር ። ጌታም ከዮሴፍ ጋር በመኖሩ ይኸን ሥራ ይሠራ እንደነበር ይገመታል ። ሁኖም በዚህ በናዝሬት እያደገ፣ ጥበብን እየተሞላ፣ በመንፈስ እየጠነከረ ይሄድ ነበር ፤ ምክንያቱም ጌታ ግዕዘ ሕፃናትን አላፋለሰም ፤ እንደማንኛውም ሕፃን ቀስ በቀስ እያለ ነውና ያደገው ።

በ፲፪ ዓመቱ ከዘመዶቹ ጋር ለበዓል ኢየሩሳሌም ሂዶ እንደነበር እናገኛለን (ሉቃ.፪.፵፩—፶፩) ፤ ምክ ንያቱም እመቤታችንም ዮሴፍም በየዓመቱ እንደ አይሁድ ልማድ ለበዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ነበርና ።

በዚያን በኢየሩሳሌም በሊቃውንቱ መካክል ሁኖ ሲጠይቃቸው ሲሰማቸውም ተገኝቷል ፤ ይኸም ማለት የዕብራውያንን ሥርዓት በመከተል የዕብራው ያንን ትምህርት እየተማረ እንዳደገ ያስረዳል ። አባ ሕርያቆስ እንደሚያስረዳን «ወተምሀረ ሕገ ዕብራው ያን» ይላል ፤ ስለዚህም፥ በዕብራውያን ሕግ የጸና ሆነ ።

ጌታም በዚህ በናዝሬት እየኖረ በጥበብም በቁ መትም አደገ ፤ በእግዚአብሔርና በሰው ፊትም ሞገ ስን አገኘ፤ ቤተ ዘመዶቹን ይታዘዝ ያገለግልም ነበር (ሉቃ. ፪. ፶፩—፶፪) ።

ከ፴ ዓመት ዕድሜው በኋላ በመምህርነት እስከ ተገለጠበት ድረስ ተራ ሰው መስሎ ማንኛውንም



ሥራ እየሠራ በዚያው በናዝሬት ኖረ ። በዚህም ዘመን ሁሉ ሰው የሚሠራውን ሁሉ ከኃጢአት በቀር ሠራ ፤ ኀዘንን ፥ ደስታን ፥ ችግርን አይቷል ፥ ተካፍሏልም ።

የጌታ ፴ ዓመት ዕድሜ በዚሁ የተሸፈነ ነው እንጂ ሌላ ይኸንና ይኸን ሠራ የሚባል የለም ፤ ወደ ሌላም አገር እንደ ሔደ የሚያመለክት ነገር የለም ።

## ምዕራፍ ፫ የክርስቶስ ጥምቀት ፤

ጌታ የሕፃንነቱን ዘመን ፈጽሞ ልክ ፴ ዓመት ሲመላው የይፋ ሥራውን ለመሥራት ከናዝሬት ወጣ፤ ወደ ይሁዳም መጣ ። የይፋ ሥራውንም በጥምቀት ጀመረ ፤ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ምድረ በዳ ንስሐ ግቡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና እያለ ፥ እያስተማረ፥ ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ የንስሐ ጥምቀት እያ ጠመቀ ፥ የክርስቶስን መንገድ እየጠረገ ፥ እያዘጋጀም መጣ ። ክርስቶስ ከዮሐንስ ጋር በተገናኘ ጊዜ እንዲ ያጠምቀው ጠየቀው ፤ ዮሐንስ ግን እኔ ከአንተ ልጠ መቅ እወዳለሁ እንጂ፥ አንተ ከኔ እንዴት ትጠመቃ ለህ ሲል አይሆንም አለው ። ጌታ ግን አንድ ጊዜ ተው ፤ የተነገረው ሁሉ እውነት ነው ፤ እርሱንም እንፈጽም ዘንድ ይገባናልና አለው ። በዚህን ጊዜ ተወውና አብረው ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሄዱና ዮሐንስ አጠመቀው ጌታም ተጠመቀ ። (ማቴ.፫.፲፫—፲፯) ።

ጌታ ተጠምቆ ከውሀው እንደወጣ ከሰማይ ቃል መጣ ፤ ይኸ ነው ልጄ የምወደው የሚል ፤ መንፈስ



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስም በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ሲያርፍበትታየ፤ በዚህን ጊዜ ፫ነት ተገለጠ ፤ ማለት ወልድ ሲጠመቅ፥ አብ በሰማይ ሁኖ ድምፅን ሲያሰማ ፥ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ ሲያርፍበት ።

ዛሬም የክርስትናው ምልክት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም አምና መጠመቅ ፥ የወልድንም አዳኝነት አምና መቀበል ነው ።

ለጥምቀት የሚያስፈልጉ ነገሮች ፫ ናቸው ፤ ፩ እምነት በሥላሴ ፤ ፪ በሥላሴ ስም መጠመቅ ፤ ፫ ፀውሀ መጠመቅ ናቸው ። በነዚህም መልክ የተጠመቁት ጥምቀት በምንም መልክ አይመለስም አይከለስም ።

፪/ የክርስቶስ ጾም ፤ ክርስቶስ እንደተጠመቀ ወዲያውኑ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ሄደ ፤ በዚያም ፵ መዓልት ፵ ሌሊት ጾመ ። ከዚህ በኋላ ተራበ ፤ ፈታኙ ሰይጣንም እንደተራበ በአየ ጊዜ አዳምን በመብል እንዳሳትኩት ክርስቶስንም በምግብ አስታለሁ ብሎ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እነዚህን ድንጋዮች እዘዝ ኅብስት እንዲሆኑ አለው ፤ ክርስቶስ ግን ለፈታኙ አልታዘዘለትም ፤ እንዲያውም ቀዋሚውን መልስ «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ከእግዚአብሔር በሚወጣው ቃልም ነው እንጂ» ሲል መለሰለት (ማቴ ፬፥፬ ፤ ዘዳግ፥ ፰፥ ፫) ።

፪ኛም ወደ ቤተ መቅደስ አውጥቶ ክተዛነቡ ላይ አውጥቶ ከዚህ ዘለህ ውረድ ስለ አንተ መላእክትን ያዛቸዋል ፤ በጎዳናህ ሁሉ እንዲጠብቁህ ፥ እግርህም በእቅንፋት እንዳትሰናከል የሚል ጽሑፍ አለና አለው ። ጌታም መልሶ ፈጣሪህን እግዚአብሔርን አትፈታተን የሚለውን መለሰለት።ማንኛውንም የማይገባውን እየሠሩ እግዚአብሔር ይኽን ያድርግልኝ የሚለው ሁሉ የማይገባ መሆኑን ጠቅሶ አስረዳው ።

፫/ እንደገና ከረጅም ተራራ አወጣውና የዓለም መንግሥታት ክብራቸውን አሳይቶ ለኔ ብትታዘዝ ብትሰግድልኝ ፥ ብታመልከኝም ይኽን ሁሉ ለአንተ እሰጥሃለሁ ብሎ በሚያስጐመጅ አገላለጥ ነለጠለት ፤ ጌታ ግን ከክብር ዙፋኑ የወረደው ወደ ዚህም ዓለም የመጣው ለሰው ድኅነት እንጅ ለራሱ ክብር አይደለምና ሰይጣን ባላጋራዬ ወግድ ከኋላዬ ሲል ለአምላክ ብቻ መስገድ ፥ አምላክን ብቻ ማምለክ እንደሚገባ አስረድቶ ድል ነሥቶታል ። በዚሀ ጊዜ ግን እንደ ድል አድራጊነቱ ምስጋና ለማቅረብና ለማገልገል መላእክቱ መጡለት ።

ዛሬም ክርስቶስ ድል ከነሣው በኋላ የሰይጣን ኃይል የለውም፤ ሁሉም ድል ሊነሳው ይችላል፤ (ሉቃ ፲፥ ፰)። ጌታ የጾመበት የ፵ ቀን ተራራ ተብሎ ተሰይሟል፥በዚህ ሰይጣንን ድል ነሥቶ በመላእክት ሲገለገል ከቆየ በኋላ ወደ ማስተማር ሥራው ተመለሰ ።

## ምዕራፍ ፬ የክርስቶስ የይፋ ሥራ ፤

ክርስቶስ ጾሙን ከፈጸመ በኋላ ደቀ መዛሙርትን መሰብሰብ ጀመረ ፤ ገሚሱ በዐሣ አጥማጅነት ሲሠሩ፥




www.ethiopianorthodox.org

ሌላውም እንዲሁ በመንገድ እንዳለ የክርስቶስ ጥሪ ደረሰውና እርሱን ለመከተል ፈቃደኛ ሁኖ እየተለና በተ ሄደ ። ይኸም ሁሉ የተፈጸመው ከጾሙ በኋላ ለ፫ ቀናት በአደረገው ትምህርት ነው ። በ፫ኛው ቀን ግን በገሊላ ቃና ሠርግ ተደረገና ጌታ በዚያ ተገኝቶ የመጀመሪያውን ተአምራት አደረገ ። በዚህም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ አመኑበት ስለዚሁም በ፩ ልብ ሁነው ተከተሉት ። ከዚህ በኋላ በገጠር፣በመንደር ፣ በከተማ እየተዘዋወረ በግልጥ ማስተማር ጀመረ ። ትምህርቱ የተለያዩ እርእስቶች በመሆናቸው ከቃሉ ልዝብነት ከትምህርቱ ጣፋጭነት የተነሣ ሕዝቡ በማድመጥ ልቡን ይሰቅል ነበር (ሉቃ ፲፥ ፴፪) ።

፩/ አንቀጸ ብፁዓን ፤ የተራራው ትምህርት በመባል የሚታወቀውን፣ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ስያሜ ግን አንቀጸ ብፁዓን እየተባለ የሚጠራውን እንደ መጀመሪያው አዋጅ አድርጎ«ብፁዓን ብፁዓን» እያለ እውነተኛውን የክርስቲያን ትምህርት በዚህ መልክ አስተማረ ።

ይኸ ትምህርት ፍጹም ልዩ የሆነ የፍጹምነት ትምህርት ነው ፤ የክርስትናውም እምነት ፍጹም ነውና አንድ የመንግሥት መሪ መንግሥትን እንደያዘ የሚያውጀው የመንግሥቱን ዓላማ ነው ፤ ክርስቶስም በመጀመሪያ የክርስትናውን ዓላማ ይኸንና ይኸን ሠርቶ የፈጸመ ብፁዕ ነው በማለት እውነተኛውን ክርስቲያናዊ ትምህርት አስተማረ ።



ምንም በተለያዩ ቦታዎች ሌሎች ብፁዓን ቢጠሩም በዚህ በተራራው ትምህርት ጊዜ የተገለጡት እንደ ማቴዎስ አገላለጥ ፱ ናቸው ።

፪/ ትምህርት በምሳሌ ፤ ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር እንዲሁ ቢገባው ይግባው ካልገባውም ይቅር በማለት አልነበረም ፤ ነገር ግን ሁሉንም በሚገባው በምሳሌ ያስተምር ነበር ፤ ለምሳሌ ለገበሬዎች በእርሻና በዘር እየመሰለ አስተምሯል (ማቴ. ፲፫.፫—፱ ፤ ማር. ፩.፲፫—፳፤ ሉቃ.፰፣፬—፲፭) ። ለሴቶች በዱቄትና በእርሾ እየመሰለ አስተምሯል (ማቴ.፲፫ ፴፫) ። ለነጋዴዎች በመክሊትና በልዩ ልዩ ሚዛን እየመሰለ አስተምሯል (ማቴ. ፳፭ ፲፬—፴) ። ለመምህራን ፣ ለካህናት በልዩ ልዩ ምሳሌ እየመሰለአስተምሯል። መንግሥተ ሰማያትን በልዩ ልዩ ምሳሌዎች እየመሰለ አስተምሯል ። እንዲያውም ያለምሳሌ አልተናገረም አላስተማረም (ማቴ. ፲፫.፴፭) ። እንግዲህ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዓላማ ለማስተማር ስለሆነ ሁሉንም በሚገባው መልክ አስተምሯል ።

፫/ ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ፤ የብሉይ ሕግ ፲ሩን ቃላት በማጽናት ፣ ያውም ነገሩን አርቆ በማጠር በ፮ አንቀጽ አጠቃልሎ አዲሱን ሕግ አስተማረ ፤ ይኸውም ፣

ሀ/ የቀድሞው ሕግ አትግደል ይል ነበር አዲሱ ሕግ ግን ወንድምህን አትስደብ በማለት ፤

ለ/ የቀደመው ሕግ አታመንዝር የሚል ነበር ፤ አዲሱ ግን ሴትን አይተህ አትመኝ በማለት ፤



www.ethiopianorthodox.org

ሐ/ የቀደመው ሕግ ሚስቱን የሚፈታ የፍችዋን መጽሐፍ ይስጣት የሚል ነበር፤አዲሱ ሕግ ግን ሚስቱን ያለ ዝሙት ምክንያት የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል ፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል ይላል ።

መ/ የቀደመው ሕግ በሐሰት አትማል ይል ነበር ፤ አዲሱ ሕግ ግን ፈጽመህ አትማል ይላል ፤

ሠ/ የቀደመው ሕግ ስለ ዓይን ፈንታ ዓይን ፣ ስለ ጥርስ ፈንታ ጥርስ የሚል ነበር ፤ አዲሱ ሕግ ግን ማንኛውንም ክፉውን ነገር በክፉ አትቃወም ይላል ።

ረ/ የቀደመው ሕግ ወዳጅህን ውደድ ጠላትህን ጥላ ይል ነበር ፤ አዲሱ ሕግ ግን ጠላትህን ውደድ የሚረግሙህንም ባርክ ፤ ለሚጠሉህም መልካም አድርግ ይላል ።

በጠቅላላውም የፍጹሙ የሰማያዊ አባት ልጆች እንመሆናችሁ እናንተም ሁሉን በመውደድ ፍጹማን ሁኑ ይላል ።

<u>፬/ የምጽዋትን ፣ የጾምን ፣ የጸሎትን ስልት በመ</u>ግለጥ ፣ ይኽን ዓለም በመረዳዳት የምናሳልፈው መሆኑን ለመግለጥ ደሀው በጉልበት፣ባለጸጋው በሀብት መረዳዳት ምጽዋት ሞስጠት ለያንዳንዱ ሰው ግዴታ ተግባሩ ሰብአዊ ክርስቲያናዊም ግዴታ መሆኑን ገልጦ አስተምሯል ። ምጽዋትም በእንዴት ያለመልክ መሰጠት እንዳለበት ስልቱን ሁሉ አስተምሯል ።



ጸሎትም «አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር» የሚለውን ፍጹም ጸሎት አስተምሯል ። ማንኛውም ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ አባቱን ማመስገን ፣ ችግሩን ገልጦ መለመን እንዳለበት የጸሎትን ስልት ገልጦ አስተምሯል ፤ ግዴታውንም ገልጧል። ጾም አስፈላጊ መሆኑንና በየጊዜው መጾም እንዳለብን ሲገልጥ በጾምኽ ጊዜ እንዲህ ሁን እንዲህም በል እያለ ዘዴውንም ፣ ተገቢነቱንም ግዴታ መሆኑንም አስተምሯል ።

ጌታ ኢየሱስ የተራራውን ትምህርት ፈጽሞ ሲወርድ በተለያዩ አገሮች እየዞረ ልዩ ልዩ ተአምራትን አድርጓል ።

<u>፭/ የክርስቶስ ተአምራት</u> ፤ ክርስቶስ የተራቡትን ኅብስት አበርክቶ ለብዙ ሕዝብ አብልቷል ፤ ድውይ ፈውሷል፤ማለትየ፴፰ዓመትመፃጉዕን ፈውሷል (ዮሐ.፭፡፩—፲) ፤ ለምጽ አንጽቷል፤ ዕውር አብርቷል፤ ማለት ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር የነበረውን ፈውሷል፣(ዮሐ.፲፩፣፩—፵፩)በጠቅላላም ብዙ ገቢረ ተአምራት ወመንክራትን ፈጽሟል (ዮሐ.፳፣ ፴) ።

ድውይ በመፈወሱ፣ተአምራትን ሁሉ በማድረጉ ሰንበትን ሻረ ተብሎ ተከሷል ፤ ሰይጣንን በሰይጣን አለቃ ያስወጣል ተብሎም ተወቅሷል ።

ነቢዩ ኢሳይያስ «በእውነት እርሱ ደዌያችንን ወሰደ ሕመማችንም ተሸከመ»፤ብሎ የተናገረው ይፈጽም ዘንድ ከሰዎች ሁሉ ደዌ ሥጋንም ደዌ ነፍስንም



www.ethiopianorthodox.org

አጠፋ (ኢሳ. ፶፫. ፩) ። ለሐዋርያት ቅሉ የሰጣቸው ሥልጣን በርኩሳን አጋንንት ላይ እንዲሠለጥኑ ነው ፤ ይኸውም እነርሱ አጋንንትን እንዲያስወጡ ፣ ድውያንን እንዲፈውሱ ፣ ሕማምንም እንዲያርቁ ነው (ማቴ. ፲. ፩) ።

፮/ በማኅበራዊ ኑሮ ፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ሰው የሆነው ሰውን መስሎ ሰው በሄደበት ሂዶ ለማስተማር ነው በሰዎች ማኅበራዊ ኑሮም እየገባ የደስታቸውም የኀዘናቸውም ተካፋይ ሁኖአል ። ለመጀመሪያ ጊዜ በገሊላ ቃና ታምራቱን ያደረገ በሠርግ ቤት በመገኘቱ የሰዎችም ደስታ ተካፋይ ከመሆኑ የተነሣ ነው (ዮሐ. ፪. ፩—፲፪) ።

ከማቴዎስ ቤት ጀምሮ በነአልአዛር ፣ በእነስምዖን ዘለምጽ ቤት ግብዣ እየተጋበዘ ገብቷል፤በእነዚህም ቤቶች ቀዋሚ የሆኑ ትምህርቶችን ሰጥቷል ። (ማቴ. ፱. ፲፩ ፣ ም ፮. ፲፩ ፣ ሉቃ. ፲. ፴፰—፵፪) ።

በቤተ መቅደስ ተገኝቶ የጸሎቱ ፣ የሥነ ሥርዓቱ ተካፋይ ለመሆን ከ፲፪ ዓመት ዕድሜው ጀምሮ ፈጽሟል (ሉቃ. ፪. ፵፪—፶ )። እኔ አምላክ ነኝና እኔ ያለሁበት ነው ቤተ መቅደስ አላለም። ይኸም ሰው ሁሉ እምነቱን፣ ሥርዓቱን አክብሮ በማኅበር፣ ጸሎት በተወሰነው ቦታ መገኘት ግዴታ መሆኑን ያስረዳል።

በኀዘን ቤት ተገኝቶ ተንሰቅስቆ አልቅሷል ፤ ይኸውም በአልዓዛር ሞት ጊዜ ነው ፤ በዚያም ከመገኘቱ የተነሣ አልዓዛርን ከሞት አስነሥቶታል (ዮሐ. ፲፩. ፲፩—፵፬) ።



በዚህም መልክ እንደማንኛውም ሰው ሁኖ ከኃጢአት በቀር የሰውን ችግር እየተካፈለ እግረ መንገዱን ግን እያስተማረና፤ተልእኮውንም ፈጸመ።

ይኸም ሁሉ ሲሆን እህል ለመብላት ውሀን ለመጠጣት ከቶ ጊዜ አልነበረውም ፤ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸምና የመጣበትን ተልእኮ ለመፈጸም እየተራበ እየተጠማ ያስተምር ነበር (ዮሐ. ፬. ፴፩—፴፬) ።

ሲያስተምር ውሎ የሚያድርበት ቤት፣ የሚያርፍበት ክፍል ከቶ አልነበረውም ፤ ቀን በምኩራብ በአዳራሹ ሁሉ ሲያስተምር ይውላል ፤ ሌሊት ግን ወደ ደብረዘይት እየወጣ ያድር ነበር(ሉቃ. ፳፩. ፴፯)። ምግብ የሚያዘጋጅለት አበዛ ፣ ደከመህ ዕረፍ የሚለው ዘመድ አልነበረውም ፤ ሲያስተምር ውሎ ልጆቼ የሚበላ አለን ?እያለ ይጠይቅ ነበር(ማቴ. ፲፭፣ ፴፪—፴፰)።

ቀማጭ ሀብት፣የክት ልብስ ከቶ አልነበረውም፤ እንዲሁም ፍጹሙን ሕይወት ስለሚኖር ይኸ ሁሉ ዝግጅት አላስፈለገውም ። እንግዲህ ይኸ ሁሉ ማንኛውም ክርስቲያን ለሚያልፈው ለዚህ ከንቱ ዓለም ሳይሆን ለወዲያኛው ተስፋ እንዲያደርግ፣ ስለርሱም እንዲሠራ ያጠይቃል ።

፯/ የክርስቶስ ጠባይ ፤ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ማኅበራዊ ኑሮ ሲኖር ከሰው ጋር አልተጣላም፤ይኸን ጥፋት አጠፋ አልተባለም ፤ ይኸን ጠብ አነሣ አይባልም ነበር ። የሰላም ባለቤት ፣ የሰላም መሪና አስተማሪ እንደመሆኑ ሰላምን ይሰብክ ፣ ሰላምንም ያስተምር፣ በሰላምም ይኖር ነበር። ክርስቶስ ሲሰድቡት አል



www.ethiopianorthodox.org

ተሳደበም ፡ አልተቀየመም፣ አፉን ለክፉ ነገር አልከፈተም ፤ በአፉም ሐሰት አልተገኘበትም ። ምንም እንዲህ ያለ የሰላም መምህር ሁኖ የሰላምም ምሳሌ ሆኖ ቢኖርፈሪሳውያንና ጸሐፍት ለጥቅማቸው ሲሉ በጠላትነት ተነሡበት ፤ ሕዝቡንም በእርሱ ላይ በዐመፅ አነሣሡበት ። መጨረሻውንም ይኸን በደለ ተብሎ ሳይነገርበት ፡ ዐመፅ ሳይገኝበት በመስቀል ተሰቅሎ እንዲሞት ተፈረደበት ።

**ምዕራፍ ፳ የክርስቶስ ንጉሥነት በመስቀል ፤**

ጌታችን ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፍሥሕን በዓል በማክበር ራት ሲበላ ፤ ኅብስቱን አንሥቶ ባረከ ፈትቶና ለደቀ መዛሙርቱም እንኩ፤ ብሉ፤ ይኸ ሥጋዬ ነው ነገ በመልዕልተ መስቀል የሚቆረሰው ብሎ ሰጣቸው ፤ ጽዋውንም አንሥቶ እንዲሁ ባረከ፤ እንኩ ሁላችሁ ጠጡ፤ ይኸ ነው የሐዲስ ኪዳን ደሜ ለዓለም ኃጢአት ማስተሥርያ ሁኖ ነገ የሚፈሰው ሲል ሰጣቸው (ማቴ. ፳፮.፳፮) ።

በዚህ ጊዜ ሥርዓተ ቍርባንን አሳያቸው ፤ ምሥጢረ ቍርባንን መሠረተላቸው ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ከእርሱ ጋር ግንኙነት ሳያቋርጥ ይኖር ዘንድ ሥጋውንመብላት፣ደሙን መጠጣት አስፈላጊ መሆኑን አስረዳ ፤ ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ ለጸሎት ወደ ጌቴሴማኒ ሄደ ።

**፩/ የጌታ መያዝ** ፤ ጌታ በጌቴሴማኒ ሁኖ ሲጸልይ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ የነበር ይሁዳ ወደካህናቱ አለቃ ሂዶ ነገር ሠራ ፤ ያስይዘውም ዘንድ ፴ ብር ተቀብሎ የጭፍሮች መሪ ሁኖ ድንገት ደረሰ ። ጭፍሮቹ ክርስቶስን ለይተው አያውቁትም ፤ ጊዜውም ጨለማ ነበርና እኔ ሂጄ የምስመው እርሱ ክርስቶስ ነውና ተረባርባችሁ ያዙት ብሎ ምልክት ሰጥቷቸው ነበርና ፤ ይሁዳ ሒዶ«በሐከ ረቢ»ሲል እጅ ነሣው ፤ በዚህን ጊዜ ጭፍሮች ተረባርበው ያዙት ።

ክርስቶስ ግን ይሁዳ! በመሳም ልታስይዘኝ መጣህን? ሲል የሰላም ቃል ተናግሮ እጁን ሰጠ እንጂ አልያዝም ብሎ አልታገለም ። ወዲያውም ጭፍሮቹ እያዳፉ እያጋፉም ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደቀያፋ ወሰዱት።

ደቀመዛሙርቱ ግን ለራሳቸው ፈርተው ተበተኑ ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ ብቻ የሚሆነውን ሁኔታ ሁሉ ለማየት በኋላ በኋላ እየተከተሉ እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ አብረው ሄዱ ። ዮሐንስ ግን እስከ መጨረሻውም ቢሆን አልተለየውም፤ ስለዚህ በመስቀሉም ጊዜ በአንጻሩ ሁኖ ሲያለቅስ ውሏል ።

ሊቀ ካህናቱም አጣድፎ የበኩሉን ምርምራ ፈጸመና በክርስቶስ ላይ ለሞት የሚያበቃ ውሳኔ በበኩሉ አስወሰነና ወደ ጲላጦስ ወሰደው ። ጲላጦስ ግን ነገሩን መላልሶ በማጥናት ምንም በደል ያልተገኘበት መሆኑን ተረድቶ ሊለቀው ፈልጎ ነበር ፤ ነገር ግን የካህናቱ አለቃ ፡ ጸሐፍቱም የሕዝቡ ሽማግሌዎችም በአንድ ድምፅ ሁነው«ስቀለው፣ አስወግደው» እያሉ ጮኹ፤በመቀጠልም ይኸን ሰው ከአዳንከው ግን የቄሣር ታማኙ አይደለህም ፤ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነውና ፤ ይኸ ሰው የቄሣር ጠላት ነው ፤ ለቄሣርም ሰዎች ግብር እንዳይከፍሉ ከልክሏል ሲሉ ከቄሣር





www.ethiopianorthodox.org

ጋር እንደሚያጣሉት አስፈራሩት ። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ሕጋችን ሞት ይገባዋል ብለው የነርሱን ሕግ ስለጠቀሱለት እንደ ሕጋችሁ ወስዳችሁ ስቀሉት ብሎ ክርስቶስን አሳልፎ ሰጣቸው ። ጲላጦስ ግን ከነ ገሩ ንጹሕ እንደሆነ ለማጠየቅ ደሙ በነርሱ ላይ ይሁን ሲል እጁን በአደባባይ ታጠበ ። ይኽም የክርስ ቶስ እውነተኛነት በእጁም በቃሉም ያልበደለ በሰ ላም የኖረ ሰው መሆኑን ያመለክታል ።

፱/ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ፤ ኢየሱስ እንደ ክፉ አድራጊ በመስቀል ተሰቀለ ፤ በመስቀል ተሰቅሎ የሚሞት ሁሉ ርጉም ይባል ነበርና ርግማንን ውርደ ትን ከሰው ለማራቅ ሲል በዕንጨት ተሰቀለ ። ወን ጀሉንም ከፍተኛ ለማድረግ በነፍስ ግዳይና በልዩ ልዩ ወንጀል ከተፈረደባቸው ሁለት ወንበዴዎች ጋር ተሰቀለ ።

ክርስቶስ በሰው ዘንድ እንደ ክፉ አድራጊ ቢቈ ጠርም ሌላው ግዑዝ ፍጥረት ሁሉ ለአምላክ ለመ መስከር ወደኋላ አላለም፤ ስለዚህም ፀሐይ ጨለመ ፤ ጨረቃ ደም ሆነች ከዋክብት ረገፉ፤አዕባን ተፈተቱ፤ መቃብራት ተከፈቱ ፤ ሙታን ትንሡ ፤ የቤተ መቅደስ መጋረጃም ከላይ እስከታች ተቀደደ (ማቴ.፳፯.፶፩) ።

ካህናቱም ፍላጎታቸው የክርስቶስን ሕይወት ለማጥፋት ነበር፤ ይኸው ፈቃዳቸው ተፈጸመ ፤ የክር ስቶስ ፈቃድ ደግሞ ስለ ሰው ሕይወት ተላልፎ መሞት ነበር፤እርሱም ተፈጸመ። እንዲሁም በሰው በኩል የሚቻ ለው የክፋት ሥራ ሁሉ እስከ ሞት ድረስ ነበር፤እርሱም



ሁሉ ተፈጸመ ። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ «ሁሉ ተፈጸመ»ሲል የመጨረሻውን ቃል ተናግሮ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በሥልጣኑ ለየ ።

የአንድ ሰው ሞት ለወገኑ ኀዘን ቢሆንም ለሌ ላው ደስታ ነው ፤ የክርስቶስ ሞት በእናቱ በእመቤታ ችንና በደቀ መዛሙርቱ በኩል መራራ ኀዘን ሲሆን በጸ ሐፍቱና፤በሊቀ ካህናቱ በኩል ደግሞ ታላቅ ደስታ ሆነ

፲/ የኢየሱስ መቃብር ፤ ንጉሥ የሰቀለው ፤ አንበሳ የሰበረው ፤ ይፈራልና በመስቀል ተሰቅሎ የሞተውን ኢየሱስን ለመቅበር የትሩፋት አበጋዞች ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የተባሉ ሺማግሌዎች ጥያቄ አቀረቡ። ጲላጦስም እንደሞተ በሰማ ጊዜ ተደነቀ፤ በመስቀል ሳለ የተደረገውን ተአምራት ሰምቶ ስለነበር በእውነት ይኸ ሰው ታላቅ ነው ብሎ፤በመሰቀሉ ተጸጽቶ ነበርና ዮሴፍና ኒቆዲሞስም በጠየቁት መሠረት እንዲቀብሩ ተፈቀደላቸውና በአዲስ በፍታ ገንዘው ማንም ወደ አልተቀበረበት ቦታ ወስደው ዮሴፍ ለራሱ በአዘጋ ጀው መቃብር ውስጥ ቀበሩት ።

በዚህም ጊዜ መለኮት በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ሂዶ ለነፍሳት ነፃነትን ሰበከ (፩ኛ ጴጥ.፫. ፲፰) ።

ከቅዱስ ሥጋው ጋርም ወደ መቃብር ወረደ፤እን ዲሁም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስም ጋር በዕሪና አልተ ለየምና ዓለምን ይገዛ ያስተዳድር ነበር ።

መቃብር ጠባቂዎችም ተመደቡ ፤ ለመቃብሩም ቊልፍ ተደረገለት፤በማኅተምም ታተመ፤ ግን ክርስቶስ



www.ethiopianorthodox.org

መቃብሩንከፈቱልኝ፤ መግነዙን ፍቱልኝሳይልበ፫ኛው ቀን በሥልጣኑ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ።

## ምዕራፍ ፮ የክርስቶስ ትንሣኤ ።

ክርስቶስ በተቀበረ በ፫ኛው ዕለት በመንፈቀ ሌሊት ሲነሣ የመቃብር ጠባቂዎች ደነገጡ ፤ እንደ በድንም ሆኑ፤ ክርስቶስን ከልደቱ እስከ መስቀለ ሞቱ ድረስ በደካማነት መልክ እንደሰውነቱ ብቻ ይመለከቱት፣ ነበር፤ ነገር ግን ትንሣኤው ፍጹም አምላክነቱን አቸናፊነቱን አሳመነ ። ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውምና ይዞም ሊያስቀረው አልቻለምና ።

በክርስቶስ ሞት ያዘኑት ሐዋርያት፣ቅዱሳት አንስትም ጽዋታ ሳያገኙ ሰንብተው ነበር፤በዚህ ቀን ግን በየበኩላቸው ወደ መቃብሩ እየሄዱ ከመቃብር አካሉን ስላሐሉ በበለጠ አዘኑ ። ሴቶች ደግሞ ከመመላለሳቸው የተነሣ መልአኩ እንዴት ሕያዉን ከሙታን ጋር ትፈልጉታላችሁ፤እርሱ ተነሥቷል፤ከዚህም የለም የሚል የሚያስደስትም የሚያሳዝንም ቃል ሰምተው ተመለሱ ፤ እያዘኑም ሲሄዱ ፣ ክርስቶስን በመንገድ አገኙት፤ እጅም ነሡት። እርሱ ግን ሂዱና ለደቀመዛሙርቶቼ እንደተነሣሁ ንገሯቸው አላቸው ። እነርሱም ሊነግሩ ሲሄዱ፣ሐዋርያት ከመንገድ ከክርስቶስ ጋር ተገናኙ፤ በክርስቶስ መነሣት በደቀ መዛሙርቱ በኩል ፍጹም ደስታ ሲሆን በሊቃነ ካህናቱና በጸሐፍት በኩል ደግሞ ኀዘን ፍርሃት ሆነ ። ስለዚህም ትንሣኤው ለሕዝብ እንዳይነገር እኛ ተኝተን ሳለ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ወሰዱት ተብሎ እንዲነገር አስደረጉ ።



ክርስቶስ ግን ለደቀ መዛሙርቱ «ሰላም" ለሁላችሁ ይሁን፣ሞት ጠፋላችሁ» ብሎ በኀዘን ተወግቶ የነበረውን ልባቸውን አጽናናላቸው ።

እንዲሁም ከነርሱ ጋር እየወጣና እየወረደ እንደቀድሞው እየበላና እየጠጣ ፵ ዕለት አብሯቸው ቆየ(የሐ. ሥራ ፩.፩—፱) ።

የክርስቶስ መነሣት ለአንዳንዶች መንፈስ መስሏቸው እንዳይጠራጠሩም ለመንፈስ አጥንት፣ ሥጋ፣ ጅማት እንደሌለው እኔ ግን እንደምታዩኝ አለኝ በማለት ፍጹም መለኮቱ ፍጹም ሰውነቱ በተዋሕዶ እንዳለ፣እንደሞተ፣እንደተነሣ፣ምንም ለውጥ እንደሌለበት አስረዳ ።

<u>፩/ ዕርገቱ</u> ፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ተልእኮ ደከመኝ ልረፍ ሳይል በመውጣት በመውረድ ፈጸመ ፤ ማጠቃለያውንም ሞቱን አደረገ። በመልዕልተ መስቀልተሰቅሎ፣ ደሙን አፍስሶ፣ሥጋውን ቆርሶ፣ለሰው ልጅ ክሶ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፣ በዚህ የሚፈጽመው ሌላ ተልእኮ ስለሌለው የቀየው ፵ ቀን ብቻ ነው ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ላከው ወደ አብ ዐረገ ። ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው ባሉበት የማጽናኛ ቃል«እንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከትለብሱ ኃይለ እምአርያም» ብሎ ነግሮ ዐረገ (ሉቃ. ፳፬.፵፰) ።

ደቀ መዛሙርቱም እጅ ነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ መቶ ሐያ ቤተሰቦች የሚያህሉ ሳይለያዩ የተስፋውን ቃል ይጠብቁ ነበር ። ፩፻፳ ቤተሰብ



www.ethiopianorthodox.org

የሚባሉትም ፲፪ ሐዋርያት ፤ ፸፪ አርድእት ፤ ፴፮ ቅዱሳት አንስት ነበሩ ፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም ከነ ዚህ ሁሉ አልተለየችም ነበር ።

## ክፍል ፪ የቤተ ክርስቲያን መሠረት ፤ ምዕራፍ ፩ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ፤

ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከዐረገ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ በመላ ፥ ወይም መቶ ሃያ ቤተ ሰብ የሚባሉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው ይጸልዩና ጌታ ኢየሱስም የሰጣቸውን ተስፋ ይጠባበቁ ነበር ። እንዲሁም ከ፲፪ ደቀ መዛሙርት ውስጥ ይሁዳ በመውጣቱ ቍጥሩ ጐድሎ ነበርና በእርሱ እግር ለሐዋርያነት ምርጫ አድርገው ማትያስ የተባለውን ዮስጦስን መርጠው ሹመው ሳለ ፥ ጌታ በዐረገ በ፲ኛው ቀን ፥ በተነሣ ደግሞ በ፶ኛው (በጰንጠቆስጤ) ቀን ከንጋቱ በ፫ ሰዓት ገደማ በድንገት መንፈስ ቅዱስ ወረደ ፤ በደቀ መዛሙርቱም ሁሉ ላይ አደረባቸው ። ሐዋርያት ወዲያው መንፈስ ቅዱስን ተመልተው ባልዩ ልዩ ቋንቋ ይናገሩ ፥ የእግዚአብሔርንም ቸርነት ይመሰክሩ ጀመር ። ሌሎች አይሁዳውያን ግን ወይን ጠጥተው ፥ የሆነውንና ያልሆነውን እንደሚናገሩ አድርገው ገመቷቸው ። ሐዋርያት ይናገሩበት የነበረው ቋንቋ የተለያየ ነበር ፤ በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ፸፪ ቋንቋ እንደነበር ይነገራል ። ቋንቋውንም ሆነ ቴዎሎጂውን ብዙውን የማያውቁት ሲሆኑ ፥ በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ተናገሩ ። መንፈስ ቅዱስን ከመመላታቸው የተነሣ ፥ ፈሪዎች የነበሩ ደፋሮች ፥ ምንም የማያውቁ የነበሩ ምሥጢርን ሁሉ የሚተረጕሙ ሆኑ ።

የመንፈስ ቅዱስ የመሆኑ ምልክት ፩ኛ የሚናገሩበትን አዲስ ቋንቋ ሌላው ይሰማው ነበር ፤ ከሕዝቡም ውስጥ ከልዩ ልዩ አገር እንደመሰብሰቡ ያየሀገሩን ቋንቋ ሲናገሩ በመስማቱ ይደነቅ ነበር (የሐ·ሥራ ፪·፭·፲፩)።

በዚያ ይገኝ የነበረው ሕዝብ ይሁዲ ይሁን እንጂ ከተለያዩ አህጉር ከአፍሪካ ፥ ከአውሮፓ ፥ ከእስያ በዓለ መጸለትን ለማክበር ተሰብስቦ የነበረ ነው ። ግማሹ ሲያደንቅ ፥ ግማሹ ደግሞ ሲያሽሟጥጥ በመስማቱ ጴጥሮስ ተነሥቶ ፥ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፥ እላንት የኢየሩሳሌም አይሁድ ከውጭም የመጣችሁ ይኸ የምናገረው በሁላችሁ ዘንድ ተቀባይነት እንደሚያገኝ እተማመናለሁ ፤ ስለዚህም አድምጡኝ ብሎ የሐዋርያትን በመንፈስ ቅዱስ መመላት ስለዚህም በተለያዩ ልሳናት እንደሚናገሩ እንጂ በወይን ሰክረው የሚናገሩ አለመሆናቸውን አስረዳ ። እንዲሁም ይኸ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይመጣ ዘንድ የነበረው ፥ እሥራኤልም በተስፋ ይጠባበቀው የነበር ፥ ስለናንተ ድኅነት ከአብ የተላከውን እናንተ በኃጢአተኞች እጅ አሳልፋችሁ ሰጣችሁት ፤ ሰቀላችሁትም ፤ ገደላችሁትም ፤ ነገር ግን እርሱ ተነሣ ሞት ይዞ አያስቀረውምና ። እንዲሁም ወደ ላከው አባቱ በዐረገ ጊዜ የተናገረውን ተስፋ በመፈጸም መንፈስ ቅዱስን ላከ ፤ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን ።

አሁንም እናንተ ንስሐ ግቡ ፤ በክርስቶስም ስም ተጠመቁ ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ጸጋ ትወስዳላችሁ ብሎ በተናገረው መሠረት ፫ ሺህ ሰው አምኖ ተጠመቀ ።





www.ethiopianorthodox.org

፩/ የቤተ ክርስቲያን መሠረት ፤ ቀድም ብሎ ጀኙ ቤተ ሰብ እየተባሉ የሚጠሩ ነበሩ ፤ አሁን በጴጥሮስ ስብከት ፫ሺህ ሰዎች ሲያምኑ፥እንዲሁም እንደገና ፭ሺህ ሰዎች ሲያምኑ ፰ሺህ ፩፻፳ ቤተ ሰብ ለመሆን የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን መሠረት ተጣለ ።

ይኸ በሐዋርያት ላይ የወረደው መንፈስ ቅዱስ ለአዲስ አማኒዎች ሁሉ ሲሰጥ የሚኖር የማያቋርጥ ሀብት ነው ፤ በጠቅላላ አነጋገርም መንፈስ ቅዱስ ከቤተ ክርስቲያን ለዘለዓለሙ ሳይለይ ለሁሉም ሲሰጥ ይኖራል። ቤተ ክርስቲያንን ከስሕተት የሚጠብቃት፥ ወደ እውነት ሁልጊዜ የሚመራት ይኸው መንፈስ ቅዱስ ነው ።

እነዚህ ቤተ ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩ ፰ሺህ ሕዝበ ክርስቲያን ከሐዋርያት ጋር በጸሎትም በሌላ ሥራም ይተጉ ነበር ። ዘየዕለቱ ወደ ቤተ መቅደስ እየሄዱ ይጸልዩ ነበር፤ በአንድ ላይም ይበሉ፥ይጠጡ ነበር፤ንብረታቸውም በአንድ ላይ ስለነበር ይኸ የእኔ ነው፤ያሚን ያንተ ነው አይባባሉም ነበር ። ዘየዕለቱ የሚያምኑት ሁሉ ከነርሱ ጋር ይጨመሩ ነበር ፤ እግዚአብሔር ጸጋውን ስለሰጣቸው በጸሎት ፀምስ ጋና ይተጉ ነበር ። በሕዝቡም ፊት መወደድ መፈራትም ነበራቸው ። በመካከላቸውም ቂም ተንኰል ከቶ አልነበረም፤ የደስታ መንፈስ ነበራቸው፤ የመተሳሰብ የወንድማማችነትም መንፈስ ነበራቸው ።

የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ይኸን የመሰለ መሠረት ይኸንም የመሰለ አቋም ነበራት ፤ በመንፈስ ቅዱስ የተመሠረተች ስለሆነ መለያየት ከቶ አልነበረም ።



ምዕራፍ ፪ የሐዋርያት ተአምራት ፤

ሐዋርያት ኃይልን ከመንፈስ ቅዱስ እንዳገኙ፥ ወዲያው ልዩ ልዩ ተአምራትን ማድረግ ጀመሩ ፤ ጌታ አስቀድሞ ሲያስተምራቸው «ያመኑትንም ይኸች ተአምራት ትከተላችዋለች ፥ በስሜ ሰይጣናትን ያወጣሉ ፤ በአዲስ ቋንቋም ይናገራሉ ፤ እባብይይዛሉ፥ የሚገድል ነገር ቢበሉም ቢጠጡም አይጎዳቸውም፤ እጃቸውንምበድውያን ላይ ይጭናሉ፤እነርሱም ይፈወሳሉ» (ማር.፲፮.፲፯) ሲል ተናግሮት የነበረው ሁሉ ተፈጸመላቸው ። ስለዚህ በየኼዱበት ፥ ጥላቸው የአረፈበት፥ልብሳቸው የነካው፥ በቃላቸው የተናገሩት በሽተኛ ሁሉ ይድን ጀመር ።

፩/ የመጀመሪያው ተአምር ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ አንድ ቀን ለጸሎት ወደቤተ መቅደስ ሲገቡ፥ በቤተ መቅደሱ መግቢያ በር ተቀምጦ የሚለምን ሽባ የሆነ አንድ ድውይ አገኙ ፤ እርሱም ገንዘብ ይሰጡኛል ብሎ ተስፋ አድርጎ ምጽዋት ምጽዋት አላቸው ።

እርሱም ዝም ብለውት ሊያልፉ አልፈቀዱምና ወርቅና ብር የለኝም፤ያለኝን ግን እርሱን እሰጥሃለሁና በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥ ሲል ጴጥሮስ ተናገረውና ወዲያው ቀኝ እጁን ይዞ አስነሣው። ሐ.ሥራ ፫. ፩—፯



www.ethiopianorthodox.org

ይኸን ትልቅ ተአምር ያየው ሕዝብ ሁሉ አድ
ናቆቱን ለሐዋርያት በመስጠቱ ጴጥሮስ ደስ አላለ
ውምና «እንዴት እኛ በሥልጣናችን ያደረግነው ይመ
ስል ታደንቁናላችሁ? ይኸ ተአምር ሊሆን የቻለው
እናንተ ጠልታችሁ ተመቅኝታችሁም በገደላችሁት
በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማመን የሆነ ነው፤እናንተም
በእርሱ ስም ብታምኑ ትድናላችሁ ሲል ተናገረ ።

፱/ የጴጥሮስና የዮሐንስ መታሠር ፤ ጴጥሮስና
ዮሐንስ ምንም ጥፋት ሳያጠፉ ድውይ በመፈወሳቸው
ብቻ በካህናት በኩል አልተወደዱም ነበር፤ ተአምር
አድራጊዎች እንዲያዙና እንዲታሠሩ ተደረገ ። በማ
ግሥቱ የካህናት አለቃና የሕዝብ ሽማግሌዎች ተሰ
በሰቡና ጴጥሮስንና ዮሐንስን በመካከላቸው አቁ
መው ይኸ የምትሠሩት ሥራ በምን ኃይል በማንስ
ስም ነው ሲሉ ጠየቋቸው ። ጴጥሮስም እናንተ የሕ
ዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች ይኸ የተደረገው ተአምር
እናንተ ሰቅላችሁ በገደላችሁት በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም እንደሆነ የታወቀ ይሁን ። እኛ ምንም ከራሳችን
አውጥተን የሠራነው ፥ ያደረግነውም ነገር የለም አላ
ቸው፥ድኅነትበማንምዘንድ አልሆነም፤ ወደፊትም አይ
ሆንም፤ የሕይወት ራስ እርሱ ብቻ ነውና ። ስለዚህ
ያለፈው አለፈ ባለማወቅ አድርጋችሁታልና ንስሐ
ግቡ ተመለሱም አላቸው ።

የካህናት አለቃና የሕዝቡ ሽማግሌዎች ነገሩ
ከበዳቸውና የሚመልሱት አጡ ፤ ግን እርስ በራሳ
ቸው ተመካከሩና በኢየሱስ ስም ሁለተኛ እንዳታስ
ተምሩ ብለው አሰናበቷቸው ። ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርን ወይስ እናንተን ልንሰማ ይገባል ፤
እስኪ እናንተ ፍረዱ፤ አሏቸው፤ እኛ በአየነውና በሰ
ማነው እንመሰክራለን አሏቸው ። ከዚህ በኋላ ምክር
ሰጥተው ለቀቋቸው ።

፲/ የሐዋርያት መገረፍ ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ
በጌታ ዘንድ የተደረገላቸውን ተአምራት በካህናቱ
በኩል ግን ያለውን ቅናትና የተሰጣቸውን ማስጠን
ቀቂያ ለወንድሞች ሁሉ በነገሯቸው ጊዜ እግዚአብ
ሔርን ሁሉም አመሰገኑት ፤ ሁሉም በድፍረት ይና
ገሩ እግዚአብሔርንም ያመሰግኑ ተአምራትንም ይሠሩ
ጀመር ። ይኸም የሐዋርያት ዝና በሁሉ ዘንድ በተ
ሰማ ጊዜ ሁሉም በሽተኛውን እየያዘ ይመጣ በሐዋር
ያትም እግር ያስቀምጥ ፥ ሁሉም ወደ ትምህርታቸው
ይሮጥ ጀመር (የሐ.ሥራ ፭.፲፪—፲፯) ።

ይኸም ሁናቴ በካህናቱ አለቃ ፥ በሕዝቡም ሽማ
ግሌዎች በተሰማ ጊዜ አልተደሰቱም ነበርና ምን ማድ
ረግ እንዳለባቸው ምክር ያዙ ፤ ስለዚህም በመላ ሐዋ
ርያትን ይዘው ወደ እሥር ቤት አስገቧቸው ። የእግዚ
አብሔር መልአክ ደግሞ በሌሊት የእስር ቤቱን በር
ከፍቶ አወጣቸውና በሉ ሂዱና በመቅደሱ አስተ
ምሩ አላቸው ። ሐዋርያትም እንደታዘዙት ወደመቅ
ደስ ሂደው በድፍረት ሲያስተምሩ ተገኙ ።

የካህናቱ አለቃ የጉባኤ ሰዎችን ሁሉ ጠራና እሥ
ረኞች እንዲመጡ ውሳኔም እንዲሰጣቸው አዘዘ ፤
መልእክተኞቹም ከእሥር ቤት እንደደረሱ እሥረኞ
ቹን አላገኟቸውም ፤ ስለዚህ ወደላኳቸው ተመልሰው

ጠባቂዎቹ በውጭ ቆመው ይጠብቃሉ ፤ ደጁም ተቀልፎ አገኘን ፤ እሥረኞቹ ግን በውስጡ የሉም ሲሉ ነገሯቸው ። ነገሩ ገርሟቸው ሲደነቁ አንድ ሰው መጥቶ እነዚያ ትናትና ያሠራችኋቸው ሰዎች ቤመቅደስ ቆመው ያስተምራሉ ብሎ ነገራቸው ። ከዚያ ሄደው እንዲያመጧቸው ጭፍሮቻቸውን ላኩ ፤ ሐዋርያትም ተይዘው ከሸንጎ ሲደርሱ ወቀሳና ጥያቄ ቀረበላቸው እንዲህ ያለ፣ ከዚህ ቀደም በናዝሬቱ በኢየሱስ ስም እንዳታስተምሩ ቍርጥ ቃል አልነገርናችሁም ነበርን ? እነሆ አሁን ከተማዋን ሁሉ በትምህርታችሁ መላችኋት የዚያን ሰው ደም ታመጡብን ዘንድ ትወዳላችሁን ? አሏቸው ። ጴጥሮስና ሌሎችም ሐዋርያት በድፍረት መለሱላቸው እንዲህ ሲሉ ፤ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር እንታዘዛለን ! የእግዚአብሔር ቃልንም እንሰማለን ። ይኽን በሰሙ ጊዜ ግን ጥርሳቸውን አፋጩ ፤ ሊገድሉአቸውም ወደዱ ።

በዚህን ጊዜ በጉባኤው ተደማጭነት፣ በሕዝቡም ዘንድ ክብር የነበረው ገማልያል የተባለ የሕግ ምሁር ሐዋርያትን ወደ ውጭ እንዲያደርጓቸው አዘዘና ለጉባኤው እንዲህ አለ ፤ እናንተ ሰዎች ተጠንቀቁ እነዚህ ሰዎች ትምህርታቸውም ሥራቸውም ከሰው እንደሆነ ያልፋል ይጠፋል ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ግን ከነፋስ ጋር እንደምንጣላ እንዳንሆን እንወቅ ፤ ስለዚህ በምንወስደው ውሳኔ እንጠንቀቅ ።

ሰዑ ፤ ከዚህ ቀደም በራሳቸው ኃይል ተነሥተው ራሳቸውንም ከፍ ከፍ ያደረጉ ተከታዮችም እስከ ማስከተል ደርሰው የነ በሩ ብዙዎች ነበሩ ፤ ነገር ግን ከእ



ዚአብሔር ያልሆነ ነገር ነውና እነርሱም ሞቱ ፤ ተከታዮቻቸውም ተበተኑ፤ ጠፉ ፤ ሲል የማያዳግም ምክርና ማስጠንቀቂያ ስለሰጠ ሐዋርያትን እንደገና ጠርተው ገርፈው፣በኢየሱስ ስም እንዳያስተምሩ አዘው ለቀቋቸው ። ሐዋርያት ግን ወደ አዳራሽ ገብተው፣ ግብር በልተው እንደወጡ እየተደሰቱ ወጥተው በበለጠ ማስተማር ጀመሩ ።

## ምዕራፍ ፫ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ኑሮ ፤

ሐዋርያት በድፍረት በማስተማራቸው ፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ስለሞላባቸው በብዙዎች ዘንድ ሞገስን አገኙ፤ በየዕለቱም ብዙዎች አማኒዎች እየተጨመሩ ቤተክርስቲያን ማደግ፣በቍጥርም መበርከት ጀመረች። ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን የሆኑት ከአይሁድ ብቻ ስለነበር ለክርስትናው አገልግሎት የሚውል የተጻፈ መጽሐፍ ፣ የተሠራም ክርስቲያናዊ ቀኖና ስላልነበር፣በጠቅላላው አማንያኑ ሁሉ ከአይሁድ ሥርዓች አልተላቀቁም ነበር ፤ ስለዚህ በየሳምንቱ ቅዳሜ በምኵራብ እየተገኙ ከአይሁድ ጋር ይጸልዩ ይማሩም ነበር ፤ ይሁን እንጂ ማታ ማታ ክርስቲያኖች በግል ሰዎች ቤት እየተሰበሰቡ ይማሩ ፣ ይጸልዩ ፣ ማዕድም ይቆርሱ ነበር ፤ ለመሰብሰቢያም አመች የነበሩት ቤቶች የማርቆስ እናቷ የማርያም ቤት፣ ይኽም እንደ መጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን የሚቈጠር ነው ፤ እንዲሁም በኋላ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የሆነ የያዕቆብ ቤትና ሌሎችም ነበሩ ። ከዕለት ወደ ዕለት ክርስቲያኑ እየበዛ ሲሄድ ግን የተባሉት ቤቶች ሊበቁ አልቻሉም ።



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኖች በተሰበሰቡጊዜ ሐዋርያትያስተምሩት የነበር የክርስቶስን ትምህርት ፥ ተአምራት ፥ ከሙታ ንም ተለይቶ መነሣት ሲሆን፥ከብሉይ ኪዳን ደግሞ አስቀድሞ ስለርሱ የተጻፉትን ክፍሎች ያነቡ ይተረ ጕሙም ነበር ። 1

ክርስቲያኖች ወዲያውኑ ከአይሁድ የሚለዩበት ሁለት ዓይነት ሥርዓት ሠሩ ፤ ፩ኛው አጋፔ (ፍቅር) የሚባል ሥርዓት ነው ፤ ይኸም ሁሉም ተሰብስቦ የፍ ቅር አንድነት ማዕድ እንዲሳተፍ፥ ወንድማማችነትን፥ አንድነትን ለመግለጥና ለማጠንከር የተደረገ ተግባር ነው ። በዚህ ማዕድ ግን ማንም እንዳይለይ ቢለይ ግን ልዩነቱን ማሳየቱ መሆኑን ያመለክት ነበር ። ፪ኛ ቍርባን፤ ይኸውም በመጨረሻው ዕለት ጌታ ያሳያቸ ውን ምሥጢረ ቍርባንን እየተሰበሰቡ መፈጸም ፥ ሁሉም በአንድነት መቍረብ ነበር ። ክርስቶስ እንዳ ደረገው ኅብስቱን አዘጋጅተው ከብሉይ ኪዳን አን ንድ ክፍል አንብበው መዝሙር ዘምረው ባርከው ፈትተው ለሁሉ ያድሉት ፅዋውንም እንዲሁ አድር ገው ይሰጡ ነበር ።

ይህን በሚፈጽሙበት ጊዜ አምኃ ቅድሳት( የፍ ቅር መሳሳም) እንደ ልዩ መታወቂያ ሁኖ ይፈጸም ነበር ። ሁሉም በንጽሕና ሁነው፥ ለኃጢአት ማስተ ሥርያ እንደሚሆን አምነው ይፈጽሙት ነበር ። ይኸ የቍርባን ሥርዓት ግን እየቆየ በየዕለቱ መሆኑ ቀርቶ በየሳምንቱ እሑድ መሆን ጀመረ ።



www.ethiopianorthodox.org

ወደዚህ ሥርዓተ ማኅበር ለመግባት አስፈላጊ ነጥቦች ሁነው የተገኙት፥በጌታ በኢየሱስ ስም ማመ ንና መጠመቅ፥እጅም ጭኖ መጸለይና መንፈስቅዱስን መቀበል ፥ በቍርባን ጊዜ መገኘት ነበር። ጌታ ከዐረገ በኋላ ሐዋርያት ክርስቶስን መምህር፥ መምህራችን በሚለው ስም አይጠቀሙም ነበር ጌታ ፥ ጌታችን በማለት እንጂ ።

እንደዚህ ብለው አምነው ወደ ክርስትናው የገ ቡት ሁሉ ደስታ በፊታቸው ተሥሎ ፥ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸው ፥ ንጽሕናን ገንዘብ አድርገው ፥ የወንድማማችነት ፍቅርንና ትሕትናን ይዘው ይገኙ ነበር ። እያንዳንዱ ክርስቲያን የተለየ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነበረው ፤ አንዱ የማስተማር፥ሌላው ድውይን የመፈወስ፥ሌላው ደግሞ ትንቢት የመናገር(የሐ፥ሥ ራ ፲፩፥፳፰) ሁሉም በደስታ በየተሰጣቸው ዕድል ይፈ ጽሙት፥ ቤተ ክርስቲያንንም ያገለግሉበት ነበር ። እርስ በራሳቸውም ይጠራሩበት የነበረው ቃል ወንድ ሞች ቅዱሳን ፥ አማንያን፥ የጌታ ደቀመዛሙርት በሚ ባሉት ቃላት ወዘተርፈ ነበር (የሐ. ሥራ፥፩፥፲፭፤ ፮፥፩. ፪.፯ ፤ ሮሜ.፩. ፯ ፤ ኤፌ. ፩.፩)። ክርስቲያን የሚለው ቃል ግን ቆይቶ የወጣ ነው ፤ ይኸም አረማውያን ክር ስቲያኖችን ለይተው መስኳቸው ያወጡት ስም ነው (የሐ፥ሥራ፥፲፩.፳፯) ።

<u>ምዕራፍ ፬ የሰባቱ ዲያቆናት ምርጫ ፤</u>

ክርስቲያኑ ሕዝብ እየበዛ በመኼዱ ጕሣውም ከአይሁድ ብቻ ሳይሆን ብዙ ከአረማውያንም የገቡ

ስለሆነ ሁሉንም በአንድ መንገድ ለማስተዳደር ችግር በመሆኑ በመካከላቸው ወኀዘግብ ተፈጠረ ። ሐዋርያት ግን ነገሩ ከፅለት ወደ ዕለት እያደገ መሄዱን ተረድ ተው፤ሁሉንም ሰብስበው ፥ የኛ ዋናው ሥራችን «ሑሩ ወመሀሩ» ያለውን አምላካዊ ቃል መፈጸም ነው ፤ እንግዲህ ይህን ትተን አበዛ ሁነን ምግብ በማስተን ተን ጊዜያችንን እናጠፋም፤ስለዚህ ሁሉን ሊያገለግሉ ይችላሉ የምትሏቸውን ፍጹም እምነት ከመንፈሳ ዊነትጋር ያላቸውን የአስተዳደርም ችሎታ ያላቸውን ፯ ዲያቆናት ምረጡልን አሏቸው ። የሐዋርያትም ሐሳብ በሁሉ ዘንድ ተቀባይነትን አገኘና ሁሉም ደስ ብሎት ወዲያውኑ ፯ ሰዎች መረጡ ።

ለመጀመሪያም እስጢፋኖስን መረጡ፤ እርሱም ሊቀ ዲያቆናት የሚሆን ሰው፤አዋቂ በሃይማኖቱፍጹም የሆነ ፥ መንፈስ ቅዱስ የመላበት ሰው ነበር ። ቀጥለውም ፊልጶስን ፥ ጵሮኮሮስንም ፥ ኒቃሮናንም ፥ ጢሞናንም ፥ ጰርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበ ረውን የአንጾኪያውን ሰው ኒኮላወስን መርጠው ስድስቱንም ለሐዋርያት አቀረቡ ።

ሐዋርያትም ለዲቁና አገልግሎት እንደምርጫ ቸው ለማገልገል እንዲችሉ እግዚአብሔር ምርጫ ውን እንዲቀበልላቸው እጃቸውን ጭነው ጸለዩባ ቸው ። በዚህን ጊዜ እስጢፋኖስና ሌሎች ዲያቆናት በሥሪዓ ቤት ፥ ሌሎች ሐዋርያት ደግሞ በስብከት፣ በጸሎትም ከመሥራታቸው የተነሣ አዲሱ ሥርዓተ ማኅበር ከፍ ከፍ አለ ፤ ምእመናን በቍጥር በዙ፤ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ መታወቅ ጀመረች ።



ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ በመታየቷ ፡ ምእመና ንም በመብዛታቸው በሐዋርያት ዘንድ ሲያስደስት፣ አይሁድን ግን በጣም አሳዘናቸው ፤ ስለዚህ ሌላ እር ምጃ ለመውሰድ አሳስቧቸው ነበር። ስለዚሁ በእስ ጢፋኖስ ላይ በጠላትነት ተነሡበት ።

እስጢፋኖስም በሃይማኖት የጸና፡መንፈስ ቅዱስን የተመላ፡ተአምራትንም ለማድረግ የበቃ፡የታወቀሰው ስለነበር፥ አድሁድ ቀኑበትና የእርሱን ሕይወት ያጠ ፋን እንደሆነ አማንያኑ ሁሉ ይበተናሉ በማለት በእ ርሱ ላይ ክስና የሐሰት ምስክር አስነሡበት ፤ ሕዝቡ ንም አነሣሡበት፤ስለዚህ አጣድፈው ለሞት አጸቁት ።

እስጢፋኖስ ግን በሐሰት የተመሰከረውን በማ ፍረስሰፈትምህርትንና የምስክርነት ቃሉን በድፍረት ሲሰጥ አይሁድ በድንጋይ ደብድበው ገደሉት ። እርሱ ግን በሚደበደብበት ጊዜ በጕልበቱ ተንበርክኮ በታ ላቅ ድምፅ አቤቱ ይኽን ኃጢአት አድርገሀ አትቍ ጠርባቸው ብሎ ዘለፍ አለ ፤ ሞተም ። ያመኑ ደጋግ ሰዎች የእስጢፋኖስን አካል አንሥተው፣ ታላቅ ኀዘን አድርገው ቀበሩት ፤ ብዙዎች አማንያን ግን ፈሩና ከኢየሩሳሌም እየወጡ በየሀገሩ ተበተኑ፤ ከሐዋርያት በቀር ፤ በቤተ ክርስቲያንም የመጀመሪያ ስደት የሚ ባለው ይኽ ነበር ።

ውስጡ ግን ጥበበ እግዚአብሔር ነው ፤ ምክን ያቱም ሁሉም በየሄደበት በመንፈሳዊ ቅናት ይሰብክ ያስተምር ነበርና ፤ በአንዲት ቤት ፤ በአንድ ቦታ



www.ethiopianorthodox.org

፥ወስኖ የነበረው ሁሉ በተለያየ አገር፥በተለያየም ቦታ፥ ሲሰብክ፥ክርስትናውም በዚያው ልክ ሊስፋፋ ቻለ ።

## ምዕራፍ ፩ የዲያቆኑ ፊልጶስ ወንጌላዊ ሥራ ፤

ከኢየሩሳሌም ከመጡት ወደ ልዩ ልዩ አገርም ከተሰደዱት አንዱ ከእስጢፋኖስ ጋር በዲቁና የተመረጠው ፊልጶስ ነበር። እርሱም ወደ ሰማርያ ወርዶ እየተዘዋወረ ሲያስተምር ብዙ ኃይል ተደረገለት ፤ ለትምህርቱም ብዙ ተቀባይነትን አገኘ ። አጋንንትም ይታዘዙለት ከሰዎችም ይወጡለት ነበር ፤ ድውያንንም ይፈውስ አንካሶችንም ያድን ነበር ። ሕዝቡም በደስታ ትምህርቱን ሲቀበልለት አንድ መሠርይ ስሙን ሲሞን የሚሉት በዚያች አገር የሚኖር፥በሥራዩ የታወቀ፥ ልዩ ልዩ የምትሐት ምልክትን እያደረገ ሕዝቡን አስደንቆት ይኖር ነበር ። የሰማርያ ሰዎችም ወንዱም ሴቱም በክርስቶስ አምኖ ሲጠመቅ እርሱም አመነ፥ተጠመቀም፥ ከዚያ በኋላ ከፊልጶስ አይለይም ነበር ።

በኢየሩሳሌም የነበሩ ሐዋርያት በሰማርያ ትልቅ የስብከት በር መከፈቱን ሰምተው ያንም የእግዚአብሔርን ቃል አክብረው መቀበላቸውን ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወደ ፊልጶስ ላኳቸው፤እነርሱም ከዚያ ደርሰው ሲጸልዩ መንፈስ ቅዱስ በሕዝቡ ላይ ወረደላቸው፤ ሲሞንም ይኸን በአየ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በገንዘብ ሊገዛ ፈለገና ሐዋርያትን ጠየቃቸው ። ጴጥሮስ ግን ገንዘብህ ከአንተ ጋር ለጥፋት ይሁንህ የመን



ፈስ ቅዱስ ጸጋ በገንዘብ አይሸጥምና አለው ። እነርሱም ይኸን የመሰለውን ተግባር ፈጽመው ወደ መጡበት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ።

## ፪/ የኢትዮጵያ ጃንደረባ እምነት ፤

ፊልጶስ በዚህ መልክ በሰማርያ ሲያስተምር የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ ከኢየሩሳሌም ወደ ደቡብ በምታወርደው ወደጋዛም ወደ ምትወስደው መንገድ ሂድ አለው ። እርሱም በትእዛዙ መሠረት ሲሄድ በዚያ አንድ የሕንደኬ ንግሥት በጀርወንድ የሆነ ኢትጵዮያዊ አገኘ፤ይኸም ሰው ጃንደረባ ነበር ፤ የንግሥቲቱ የንብረቷ ሁሉ ኃላፊ የሆነ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሰግድ መጥቶ የነበር፤ ሲመለስ አገኘው ።

የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ እያነበበ በሠረገላ ሁኖ ሲሄድ፥ መንፈስ ቅዱስ«ይኸን ሠረገላ ተከተለው»ሲል ለፊልጶስ ነገረው።ፊልጶስም ወደ ጃንደረባው ሲቀርብ ሲያነብ ሰማው ። ፊልጶስም ይኸን የምታነበውን ታውቀዋለህን አለው ። ጃንደረባውም ያስተማረኝ ሳይኖር እንዴት ለማወቅእችላለሁአለው። ያነበው የነበረው ክፍልም «እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ ፤ እንደ በግ ጠቦትም በሸላቾች ፊት ዝም እንዲል እንዲሁ አፉን አልከፈተም ፤ በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፤ትውልዱንም ማንይነግርለታል ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና»የሚልነበር (የሐ. ሥራ፥ ፰/፴፪—፴፫ ፤ ኢሳ/፶፫/፯) ። ጃንደረባውም በመንፈስ ቅዱስ ተቃኘና እንዲያስረዳው ፊልጶስን ለመነው ፥ እባክህ ንገረኝ፤ ነቢዩይኸን ክፍል ስለማን ተናገረው?ስለራሱ



www.ethiopianorthodox.org

ነውን ወይስ ስለ ሌላ አለው ። ፊልጶስ ግን የማስተማሪያ ዕድል ስላአገኘ መነሻውን ይኸን ክፍል አድርጎ ፀጠቅላላ ስለ ኢየሱስ ሕይወት ነገረው ፤ ማለት አስቀድመው ነቢያት በትንቢት ሳልርሱተናገሩ፤ ጻፉም፤ በዘመኑ ፍጻሜም እርሱ ራሱ ሰው ሁኖ መጣ ፤ ስለ ሰውም ወጣ፤ወረደ፤አስተማረ፤ድውይን ፈወሰ፤ ሙትን አስነሣ ብዙ ተአምራትንም አደረገ ። በመጨረሻው አይሁድ በመስቀል ሰቅለው ቢገድሉት፣በሦስተኛው ቀን ተነሣ ፤ በክብርና በምስጋናም ወደ ሰማይ ዐረገ ። ዛሬምእኛየምንዞረውየምናስተምረውምይኸንናይኸን የመሰለውን ለሰው ሁሉ ለመንገር ነው ፤ በርሱ ያመነ በስሙም የተጠመቀ ይድናል ብሎ በማጓጓት ወደ እምነቱ ስለሳበው ጃንደረባው ሳያመነታ እነሆ ውሀ እዚህ አለ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማነው ፤ ወይስ ምንድን ነው? ሲል ጠየቀው።ፊልጶስም ነገር ሳያስረዝም በፍጹም ልቦናህ ማመን ብቻ ነው ፤ የሚያምን ይችላል አለው ። በዚህን ጊዜ ጃንደረባው «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ» ሲል ከፍተኛውን የእምነት ኑዛዜ ቃል ተናገረ ። ሠረገላውም እንዲቆምለት አዘዘና ሁለቱም ወደ ውሃው ወረዱ ፤ ፊልጶስም አጠመቀው ፤ ከውሃው ሲወጡ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው፤ተሠወረውም ። ጃንደረባው ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ተነሣሥቶ እንደ አመነ እንደተጠመቀም ጸጋ መንፈስ ቅዱስንም እንዳገኘ አምኖ ተደስቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ (የሐ. ሥራ ፰/ ፳፮—፵) ።



## ምዕራፍ ፯ የሐዋርያት ለስብከት መበተን

ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ በሐዋርያት ላይ በኢየሩሳሌም ብዙ ችግር አልተፈጠረባቸውም ፤ እነርሱም መከራው የተለያየም የበዛም ቢሆን እንደችግር ባለመቍጠር በመሥራታቸው ምእመናኑአሁንም የበዙ፡ ቤተ ክርስቲያኗ የጸናች ሆነች ። ሐዋርያትም እስከ ዓመት ድረስ ከኢየሩሳሌም ሳይወጡ፣ሳይበተኑ በዚያው ይገኙ ነበር ። ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን በአንዳንድ ቦታ አልፎ አልፎ ቢታዩም እየተመለሱ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር፤በመጨረሻው ግን ሁሉም ሐዋርያት ወደተለያየ አገር ሲበተኑ በኢየሩሳሌም የቀሩ እነማን እንደነበሩ አይታወቅም፣ምክንያቱም ሁሉንም በተለያየ አገር ተበትነው እናገኛቸዋለንና ።

ሐዋርያት በአንድነት ሳሉ የመጀመሪያውን ሲኖዶስ በ፶ ዓ/ም በኢየሩሳሌም እንዳደረጉና ውሳኔ ለሁሉ እንዳስተላለፉ እናገኛለን ። ከዚህ በኋላ ግን ሙሉ ሁነው በአንድ ቦታ ተሰብስበው አናገኛቸውም ግን በየተገኙበት አገር እንዴት እንደሆኑና ፀገሩንም በማንሳት እንደሚከተለው እንተርካለን ።

፩/ ቅ/ ጴጥሮስ ፤ ከጰራቅሊጦስ በዓል ጀምሮ ዋናው ተናገሪና መስካሪ ቅ/ጴጥሮስ ነው፤ ሳይፈራም፣ ሳያፍርም በግልጥ ያስተማረ እርሱ ነው ። እንዲሁም ወደ ቂሣርያ ሄዶ ቆርኔሌዎስን ከቤተ ሰቡ ጋር ያስተማረ፣ ያጠመቀ፣ እርሱ ነው ። ወደ ሰማርያ ከዮሐንስ ጋር ወርዶ ያስተማረ፣ ተአምራትንም ያሳየ ፣ ሲሞን መሠርይንም የገሠጸ እርሱ ነው ። ለመጀመሪያ ወደ



www.ethiopianorthodox.org

እንጾኪያ ሂዶ እንዳስተማረ ይነገራል ፤ ስለዚህ የአ
ንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መሥራች እርሱ እንደሆነ
ይነገራል ።

እንዲሁም ወደ ሮማ ሂዶ እንዳስተማረና የሮ
ማን ቤተ ክርስቲያን እንደመሠረተ በዚያም የቁል
ቁሊት እንደተሰቀለና በሰማዕትነት እንዳረፈ ይነገ
ራል ፤ ጴጥሮስ ፪ አጠቃላይ መልእክቶችን ጽፏል ።

፲. ወንድሙ እንድርያስ ፥ ከጰራቅሊጦስ በዓል
በኋላ በዚህ ቦታ ታየ አይባልም ግን በቤተ ክርስቲያን
ትውፊት እንደሚነገረው የቢዛንቲን ቤተ ክርስቲያን
መሥራች እንደ ሆነ በዚያም ሲሰብክ በሰማዕትነት
እንዳረፈ ይነገራል።እንዳንዶችም እስከ ራሺያ ድረስ
ሂዶ እንደሰበከ የራሺያም ቤተ ክርስቲያን መሥ
ራች እርሱ እንደሆነ የሚናገሩ አሉ ።

፫፥ ዮሐንስ ወንጌላዊ ፥ ዮሐንስ ከጴጥሮስ ጋር
ሳይለይ በኢየሩሳሌም በብዙ ቦታዎች እናገኘዋለን ፤
በሰማርያ አብረው ሲኖሩ ሲያስተምሩእናገኛቸዋለን፤
ዮሐንስ የቅድስት ማርያም ባለ አደራ ጠባቂስለሆነ፥
ከፍልስጥኤም ምድር ለብዙ ጊዜ እንዳልወጣ ይነገ
ራል ፤ አንዳንዶች እንደሚሉት ግን እመቤታችንንም
ወደ ኤፌሶን እንደወሰዳት፥ እርሱም በዚያ ሲሰብክ
እንደኖረ ይናገራሉ ። ይሁን እንጂ እመቤታችን በኢየ
ሩሳሌም ዐርፋ በጌቴሴማኒ ተቀብራለች ። እርሱ ግን
በኋላ ወደ ኤፌሶን እንደ ሄደ፥ በዚያም ብዙ ዘመን
እንደኖረ ይነገራል ። ለ፹፩ ዓመት ግን በግዞት በፍ
ጥሞ ደሴት ኑሯል ፤ በዚያም ራእዩን ጽፎ ወጥቷል ።



ዮሐንስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሥራች
ነው ፤ ብዙ ጊዜም ያሳለፈባት አገር ኤፌሶን ናት ፤
ወንጌሉንም፥ ፫ቱንም መልእክቶች በዚያው እንደጻፈ
ይነገራል ።

፬/ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ፤ ይኸ ሐዋርያ ከሁሉ
ቀደም ብሎ፥ከእስጢፋኖስ ቀጥሎ በሰማዕትነት ያረፈ
ነው ። ሄሮድስ በቤተ ክርስቲያን ላይ እጁን አጥብቆ
ጫነ፥ጭቆናም አበዛ ፤ ማለት ክርስቲያኖችን ያሠቃይ
ጀመረ ፤ በዚህም መሠረት ሐዋርያውን ያዕቆብን
ያዘና በሰይፍ አስገደለው ።

፭/ ማቴዎስ ፤ ይኸ ወንጌላዊ ከጰራቅሊጦስ
በዓል በኋላ እንዴት እንደነበር የወንጌሉን ታሪክ በተ
ረከንበት ተናግረናል ። ሆኖም ለብዙ ጊዜ በፍልስ
ጥኤም ምድር ቆይቷል ፤ ወንጌሉንም የጻፈው በዚ
ያው ነው፤ በኋላ ግን ሕንድ ወደ ተባለ አገር እንደሄደ
ይነገራል ፤ ሕንድ የተሰኘችው ሀገር ግን የዛሬይቱ
ኢትዮጵያ ናት ፤ በፋርስ ቋንቋ ሒንዱ ማለት ጥቁር
ማለት ነውና ። የጃንደረባውን ንግሥትንም ሕንደኬ
ሕንዳዊት ይላታል ፤ ፍሬምናጦስንም የሕንድ ኤጲስ
ቆጶስ ይለዋልና፤ስለዚህ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ወንጌ
ልን አስተምሯል በማለት ሰቆራጥስ ፥ ሶዞሜኖስ ፥
ቴዎድሮስ ፥ የተባሉ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
ጸሐፊዎች የማቴዎስን ሀገረ ስብከት ስም ጠርተው
ኢትዮጵያ ብለው ጽፈዋል ። እነዚህም የቤተ ክርስ
ቲያን ታሪክ ጸሐፍት ይኸን ለማለት የቻሉት የአው
ሳብዮስን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መሠረት በማድ



www.ethiopianorthodox.org

ረግ ነው ፤ እርሱም በኢትዮጵያ ቅ/ማቴዎስ እንደሰ በከ ይናገራልና ።

፯/ ቶማስ ፤ ወደ ፋርስና ወደ ዛሬይቱ ሕንድ ድረስ ሂዶ እንዳስተማረ ይነገራል ፤ ዛሬም የቶማስ ክርስቲያኖች ወይም የቶማስ ቤተ ክርስቲያን እየተ ባሉ የሚጠሩ አሉና ።

፰/ በርተሎሜዎስ ፤ ይኸም ሐዋርያ ማቴዎስ ወደ ሄደበት አገር ሂዶ እንደ አስተማረ አውሳብዮስ ይናገራል ፤ ይኸም ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አስ ተምሯል ማለት ነው ። (አውሳ) እንዲሁም በአርማ ንያ እንደሰበከ ይነገርለታል ።

፱/ ፊልጶስ ፤ ስምዖን ቀነናዊ ፤ ማትያስ ፤ የእ ነዚህ ሐዋርያት ሀገረ ስብከት እስከ አሁን አይታወ ቅም ።

፲/ የጌታ ወንድሞች ያዕቆብና፤ ይሁዳ እነዚሀና ሌሎችም የጌታ ወንድሞች እየተባሉ የሚጠሩ አሉ ፤ እነዚሀም የዮሴፍ ልጆች ሁነው ከጌታ ጋር አብረው ስላደጉ፣ እመቤታችንም በዮሴፍ ቤት ስለኖረች፣ ጌታ ከነዚሀ ከዮሴፍ ልጆች ጋር አብሮ ስላደገ ወንድሞቹ ይባላሉ ።

እነዚህም ዘግይተው በክርስቶስ እንዳመኑ ይነገ ራል (ዮሐ./፯.፭) ፤ ሁኖም ያዕቆብ ትልቅ ሐዋርያና የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የሐዋርያትም ሁሉ ሰብሳቢ ሁኖ ኑሯል ።



ይኸ ያዕቆብ በስሙ የሚጠራ አንድ አጠቃላይ መልእክት ጽፏል ፤ ይኸም መልእክት በስደት ለሚ ገኙት ፲፪ቱ ነገደ እሥራኤል ሁሉ የሚደርስ ነው ። በጽኑዕ ገድል፣ በትሕርምት የሚኖር፣ የሚሰብክ፣ በጎ አድራጎትንም ለሁሉ የሚያደርግ ትልቅ የቤተ ክር ስቲያን አባት ሐዋርያ ነበር ። አይሁድ በቅንዓት ተነሥተው ገደሉት፤ በዚያው በኢየሩሳሌም በሰማ ዕትነት ዐርፏል ።

ወንድሙ ይሁዳም በዚያው በፍልስጥኤም ሠራ፣ አስተማረ ፤ በስሙ የሚጠራውንም መልእክት ጻፈ ።

## ምዕራፍ ፯ የቅዱስ ጳውሎስ መጠራት ፤

፩/ ትውልዱ፣ በኋላ ጳውሎስ የተባለው የሳውል ትውልድ ከነገደ ብንያም ነው ፤ የሃይማኖት ክፍሉም ፈሪሳዊ እንደ ነበረ ራሱ መስክሮ ጽፏል(ሮሜ. ፲፩/፲፬) ዜግነቱ ደግሞ ሮማዊ ነው ። የተወለደበት አገር የቂልቅያ አውራጃ በምትሆን በጠርሴስ ነው (የሐ. ሥራ ፳፩. ፴፱)። ሳውል ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ ጥያቄ ማለት ነው ።

ይኸ ሳውል ፩መሠረቱ አስተዋይ አእምሮ ፤ የመረዳትም ኃይል ያለው ሰው ነበር ። ወላጆቹ በል ጅነቱ ከቂልቂያ ወደ ኢየሩሳሌም ወስደው ሕግ ይማ ርላቸው ዘንድ ለታላቁ የሕግ መምህር ለገማልያል ሰጡት (የሐ/ ሥራ ፳፪.፫)።ዕብራውያን ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ ልዩ ልዩ ተግባረ እድ እንደሚያስተምሯ ቸው ሳውልንም ከቀለም ትምሀርት ሌላ ድንኳን መስ ፋት አስተምረዉት ነበር (የሐ. ሥራ ፳፪.፫፣) ።



www.ethiopianorthodox.org

ይኸ ሳውል ለአባቶች ሕግ በጣም ቀናተኛነበር ስለዚህም ከአባቶቹ ሃይማኖት ውጭ የሆኑትን የክርስትና ትምህርት የሚያስተምሩትን አጽንቶ ይጠላ ነበር ።

ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ከነበረው ጥላቻ ለመራቅ ወደ ልዩ ልዩ ሀገር ቱበትነው ለማስተማር የሞከሩትንም እያሠረ ወደ ኢየሩሳሌም እያመጣ ለማስፈረድ ቍርጥ ሐሳብ አድርጎ ከሊቀ ካህናቱ የማስገደጃ ደብዳቤ ተቀብሎ ወደ ደማስቆ ሄደ ።

፪/ ሳውል በተአምራት እንዳመነ ፤ በደማስቆ የነበሩትን ክርስቲያኖች ለማሠቃየት ሲገሰግስ ሰንብቶ፣ከከተማው ለመግባት ትንሽ ሲቀረው፣በጠራራው ፀሐይ ላይ ድንገት መብረቅ ብልጭ አለና ዐይኑን እንጸባረቀው ፤ ሳውልም ከመሬት ወደቀ ፤ ዐይኖቹም ታወሩ (የሐ.ሥ. ፱—፳፰፡፳፱/ ፫—፲፪)።ከሰማይ ደግሞ «ሳውል፤ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ» የሚል ድምፅ ሰማ።ሳውልም ጌታ ሆይ አንተ ማነህ? ሲል ጠየቀ ። ጌታም «እንተ የምታሳድደኝ የናዝራዊ ኢየሱስ ነኝ» አለው ። ሳውልም ጌታ ሆይ አሁን ምን ድንእንዳደርግ ትፈልጋለህ?ሲል ጠየቀው ። ጌታ ግን ወደ ከተማው ግባ በዚያ የምታደርገውንና የምትድነበትን ታገኛለህ አለው ። ከወደቀበትም ተነሥቶ አብረዉት በነበሩ ሰዎች እየተመሩ ወደ ከተማ ገባ ።

አብረዉት የነበሩ ሰዎች ግን ድምፁን ይሰሙ ነበሩ እንጂ ያዩት ነገር ከቶ አልነበረም ።



ሳውልም ከከተማው ገብቶ ለ፫ ቀናት ያህል እህል ሳይበላ ፥ ውሀም ሳይጠጣ ሰነበተ ። በዚያ ከተማ የጌታ ደቀመዝሙር የሆነ ሐናንያ የተባለ ሰው ነበር ፤ ለእርሱም ጌታ በሕልም ሳውልን እንዲያጠምቀው ነገረው ። ሐናንያ ግን ጌታ ሆይ ይኸሰውክርስቲያኖችን ሁሉ የሚያሳድድ እንደ ነበር አውቃለሁ እንዴት እቀርበዋለሁ አለው። ጌታም በአሕዛብ ዘንድ ስሜን ይሸከም ዘንድ ምርጥ ዕቃ አድርጌዋለሁና አትፍራው አለው ። በዚያን ጊዜ ደግሞ ሐናንያ የሚያዘውን ሁሉ እንዲፈጽም ለሳውል በራእይ ተገለጠለት ። በኋላም ሐናንያ እየጠየቀ ሳውልከለበት ቤት ድረስ ሂዶ ወንድሜ ሳውል፤ሲል በእጁ ያዘው፤በዚህንጊዜ ሳውል ከዐይኑ እንደ ቅርፊት ያለው ለቆ ወደቀለት፥አጠመቀውም፤ በዚህን ጊዜ ቶጽናና ፤ ተነሥቶም እህል በላ፥ ውሀም ጠጣ ።

ሳውልም ወዲያውኑ የክርስቲያን ትምህርት ልማር ሳይል ፥ ወይም ትናንት ያፈርሰው የነበረውን ግሬ ይገነባል ይሉኛል ሳይል፥ሳያመነታም፥ወዲያውኑ ስለ ክርስቶስ ይመሰክር ያስተምርም ጀመር ። ወደ ዓረብ ምድረ በዳ ሂዶም ለ፫ ዓመት ያህል ሱባዔ ገብቶ ራሱን ይመረምር ከእግዚአብሔርም ጋር ይነጋገር ጀመር (ገላት. ፩—፲፪) ።

ከዓረቢያ ተመልሶ እንደገና ደማስቆ ገብቶ ስለ ክርስቶስ በከፍተኛ ቅናት ሲያስተምር በድፍረትም ሲናገር፤በደማስቆ ይገኙ የነበሩ አይሁድ በጥላቻ ተነሡበት፤ ሊገድሉትም ይሹ ጀምር፤ስለዚህም የደማስቆን በር በመዓልትም በሌሊትም አጽንተው ይጠብቁ ጀመር፤ ሳውል ሲወጣና ሲገባ ይዞ ለመግደል ። ደቀ



www.ethiopianorthodox.org

መዛሙርቱ ደግሞ በቅርጫት አድርገው፥ በመስኮት አውጥተው በሌሊት ሰደዱትና ከሞት አመለጠ ።

ሳውልም ከደማስቆ ወጥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደና በዚያ የሚገኙትን ሐዋርያት ለመገናኘት ፈቀደ ፤ ሐዋርያት ግን ቀድሞ ይሠራው የነበረውን ክፉ ሥራ ስለሚያውቁ፥ ደፍረው ሊገናኙት አልፈቀዱም። በርናባስን አግኝተው በክርስቶስ ማመኑን እንደነርሱም በቅንዓት ስለክርስቶስ ማስተማሩን እስኪናገር ድረስ።

በዚያም በኢየሩሳሌም በመንፈሳዊ ቅናት ሲያስተምር ቀድሞ የሚያውቁትም ባልንጀሮቹ የነበሩ ሊገድሉት ይፈልጉት ጀመር። ከዚያም ሐዋርያት ወደ አገሩ ወደ ቂልቅያ አውራጃ ወደ ጠርሴስ እንዲሄድ አደረጉ ።

፫/ <u>የጳውሎስ የስብከት ዘዴ</u> ፤ ጳውሎስ እንዲሁ እንዳገኘ የሚናገር ሰው አልነበረም ፤ እርሱ ራሱ ተነቃናቂ በመሆኑ ታላላቅ ከተማዎችን ፥ ሕዝብ የበዛባቸውን እየመረጠ ዕቅድ እያወጣ ይሰብክ ነበር ። እንዲሁም ሕዝቡ ተንቃናቂየሆነውከአንዱወደሌላው አገር ሲሄድ ስለ ክርስቶስና ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊያወራ ሊናገር የሚችለውን በመምረጥ ነበር። እንዲሁም ትምህርቱ እንደቦታውና እንደሁናቴው ይለያይ ነበር ፤ ሁሉም ደስ ብሎት በሚቀበለው መልክ ያስተምር ነበር ። ሀገርን መምረጥ ብቻ ሳይሆን ቦታንም ይመርጥ ነበር ፤ ለምሳሌ በገቢያ ፥ በምኵራብ ፥ በአደባባይ፥ በትያትር ቦታ ሁሉ ሕዝብ የሚገኝበትን በመምረጥ ያስተምር ነበር ። እንዲሁም በየደረሰበት



አገር አስቀድሞ ጠይቆ ያስተምር የነበረው አይሁድን ነበር ። በዚህም መሠረት ከአይሁድ ውስጥ ብዙዎችን አሳምኗል ፤ ግን የአሕዛብ መምህር እንደመባሉ በይበልጥ ያሳመነው አሕዛብን ነው ። በዚህም መሠረት ክርስትና በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ ብቻ ይገኝ የነበረውን ሳውል በትጋት ከማስተማሩ የተነሣ ከኢየሩሳሌም እስከ እስጳንያ ያሉት 'አገሮች ሁሉ ክርስትናን ተቀብለው ቤተ ክርስቲያንን አቋቁመው ተገኝተዋል ።

እንዲሁም በቃል በየደረሰበት ማስተማር ብቻ ሳይሆን ጳውሎስ በመልእክትም ያስተምር ነበር ። ይኸን ሁሉ አገር ሲዞር ሌሊትም መዓልትም ሳይል ሲሠራ በሰው በኩል የሚረዳው ነገር ከቶአልነበረም፤ በራሱ እጅ ድንኳን ሰፍቶ፥ያንን ሸጦ በሚያገኘው ገንዘብ ራሱንም ሌላውንም ይረዳ ነበር እንጂ (፩ኛ ቆሮ.፬.፲፪፤፪ኛ ቆሮ. ፲፩.፯፤የሐ.ሥራ.፳.፴፬፤፩ኛ ተሰ.፪.፱) ። እንዲህ አድርጎ ሲሠራ ቆይቶ ሊሞት ሲል የመጨረሻውን የኑዛዜ ቃል እንዲህ ሲልአስተላለፈ። «መልካሙን ገድል ተጋደልኩ ፤ሩጫዬንም ጨረስኩ፤ ሃይማኖቴንም ጠበቅሁ ፤ እንግዲህስ ያ ጻድቅ ፈራጅ ዋጋዬን ይከፍለኛል፤ ለኔም ብቻ አይደል መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ እንጂ »(፪ኛ ጢሞ. ፬. ፯—፰) ።

፬/ <u>የቅ/ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞ</u> ፤ ጳውሎስ ክርስትናን እንደተቀበለ የክርስቶስ ወንጌልን ለማስተማር ብዙዎች ሀገሮችን ዞሯል ፤ እነዚህም ፫ቱ የሐዋርያነት ጉዞ እየተባሉ ይጠራሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

፩/ ጉዞ ፤ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፵፭ ዓመት በርናባስንና ማርቆስን አስከትሎ ከአንጾኪያ ወደ ቆጵሮስ ወረደ፤ በዚያም ሰላሚናጳፉ በሚባሉት በዶሴቷ ታላላቅ ከተማዎች አስተማረ ። በዚያም ከትምህርቱ ከተአምራቱ የተነሣ ጳውሎስ የሚለውን ስም አገኘ፤ ጳውሎስ ማለትም ብርሃን ማለት ነው ። ጳውሎስ በትምህርቱ በተአምራቱ ዓይነ ሥጋን ዓይነ ነፍስንም ያበራ ነበርና ። ይኸንም ስም የሰጠው ሰርግዮስ ጳውሎስ የተባለ ሰው ነው ፤ እርሱም የሀገሯ ሹም የነበር ነው (የሐ.ሥራ. ፲፫. ፯)።ከዚህ ዕለት በኋላ ስሙ ጳውሎስ ሁኖ ከቆጵሮስ ወደ ታናሿ እስያ ሄደ ፤ ወደ ጵንፍልያ ሲደርስ ማርቆስ ልጅ በመሆኑ መከራውን ተሰቀቀና ተመለሰ ። ጳውሎስና በርናባስ ግን ወደ ፍርግያ ወደ አንጾኪያም ደረሱ፤በዚያም በየምኵራቡ እየገቡ ቃሌ ንግግር እያደረጉ ሕዝቡ እስኪደነቅ ያስተምሩ ነበር ። ከዚያም አልፈው ኢቆንዮን፥ደርቤን ፥ ልስጥራ ወደሚባሉት አገሮች ደረሱ በነዚህም በደረሱባቸው አገሮች ሁሉ ብዙ አማንያንን አገኙ ። ከዚህ በኋላ ደግሞ በሄዱበት አገር እድርገው ቀድሞ ያሳመኑትን እያጽናኑ ወደ አንጾኪያ ተመለሱ ።

፪/ ጉዞ ፤ በዚህ ጉዞ ጊዜ ደግሞ እርሱ ያሳመናቸውን ሲላሳን፥ጢሞቴዎስን፥ሉቃስን ይዞ በ፶፫ዓ.ም. ከአንጾኪያ ተነሥቶ ፍርግያ፥ቢታንያ፤ሚስያ የሚባሉትን የታናሽ እስያ አገሮች እያስተማረ ወደ አውሮፓ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሻግሮ ፊልጵስዮስ ፥ ተሰሎንቄ ቤርያ ፤ አቴና ፥ ቆሮንቶስ የተባሉትን በዘመኑ ታላላቅ የነበሩትን ከተማዎችን አስተማረ ። ከቆሮንቶስ በኋላ ወደ ኤፌሶን ሄደ፤ ከዚያም ወደ አንጾኪያ ተመለሰ ። በዚህም ጊዜ ብዙ አሳምኖ ብዙ ቤተ ክርስቲያንን አቋቁሞ ተመልሷል ።

፫/ ጉዞ ፤ በዚህ ጊዜ ሉቃስን ፥ ጢሞቴዎስን ፥ ቲቶን ፥ አስከትሎ በ፶፮ ዓ/ም ከአንጾኪያ ተነሥቶ ገላትያ ፥ ፍርግያ የተባሉትን የታናሽ እስያ አገሮችን እያስተማረ ኤፌሶን ደረሰ ። በኤፌሶን ግን ፪ ዓመት ተኩል ቆየ ። ከዚህ በኋላ ወደ ጢሮአዳ ሄደ ፤ ከዚያም ወደ መቄዶንያ ለ፪ኛ ጊዜ ተሻገረ፤ቀድሞ ያስተማራቸውን አገሮች እያስተማረ፥ያቋቋማቸውንም አብያተ ክርስቲያን እየጎበኘ፥እስከ ዕልዋሪቆን ድረስ ሄደ ሮሜ.፲፭. ፱) ።

ከዕልዋሪቆን ተነሥቶ፥ በቆሮንቶስ አድርጎ ወደ መቄዶንያ ተመለሰ፤በዚያም በጢሮአዳ አድርጎ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ። ይኸም የመጨረሻ ጉዞው ነበር ። ይኸንም የመጨረሻውን ጉዞ ለማከናወን ፩ ዓመት ያህል ፈጅቶበታል ። ኢየሩሳሌም ሲደርስ ግን ችግር ሊገጥመው ነው ፤ ምክንያቱም በየሀገሩ እየዞረ ሲያስተምር የጠሉት አይሁድ በመቅደስ ገብቶ ሲያዩት ተመቅኝተው ይዘው እየደበደቡ ሊገሉት ሲሉ የሮማ ጭፍራዎች ደርሰው አዳኑት ። ቢሆንም ክሱ ቀጠለና በይግባኝ ወደ ሮማ መሄድ ግድ ሆነበት ። ስለዚህ ምንም ጥፋት ሳይገኝበት ስለ ክርስቶስ ስም እሥረኛ ሁኖ ከብዙ እሥረኞች ጋር በትልቅ ቍጥጥር ወደ ሮማ ሄደ።በ፷፪ ዓ/ም ሮም ገባና ነገሩ ቀላል በመሆኑ የቁም እሥረኛ ሁኖ እንዲቀይ ተወስኖለት ቤት፥ተከራይቶ ፥ የመጣለትን ሁሉ እየተቀበለ፥ ያስተምር ነበር ።




www.ethiopianorthodox.org

ቆይቶ ግን ከዚሀ ክሉ ነፃ ወጥቶ እንደገና ፪ኛ ሐዋርያዊ ጉዞ እንዳደረገ ይተረካል ፤ ሁኖም የታወቁት እነዚሀ ፫ቱ ብቻ ናቸው ። ከዚሀ በኋላ ግን የመጨረሻ ዕረፍቱ ሆኑና የክርስቲያን መግረፊያ እየተባለ በሚጠራው በኔሮን ትእዛዝ በሰይፍ እንዲገደል ሁኖ፣በዚያው በሮማ በሰማዕትነት ዓርፏል ። ጳውሎስ ቀን እያስተማረ፣ ሌሊት ድንኳን እየሰፋ ከመሥራቱ የተነሣ ዓይኑ ደክሞ ነበር ። እንግልትም በዝቶበት ነበር ፤ ግን ሳይሰለች ምስክርነቱን በብዛት ሰጠ ። ከዚሀም ጋር ለሁሉ መልእክት እየጻፈ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለግል ሰዎች ፣ ለተለዩ ከተማዎች ይልክ ነበር ፤ እነዚሀም የሐዲስ ኪዳን የትምህርት ክፍል ሁነው የተመደቡ ፲፬ መልእክታት ናቸው ።

## ምዕራፍ ፰ ልዩ ልዩ ደቀመዛሙርት ፤

በዚሀ ጽሑፍ ስማቸው ያልተጠቀሱ ሀገረ ስብከታቸውም ያልታወቀ ብዙዎች ደቀ መዛሙርት ነበሩ ፤ ሁሉም በመንፈሳዊ ቅንዓት ስለ ክርስቶስ ሠሩ ፤ መሰከሩ ፤ ሕይወታቸው ግን በዚያው ስላለፈ የት እንደወደቁ እንኳን ሳይታወቁ ቀሩ ፤ ፸፪ አርድእት የሚባሉ ነበሩ ፤ ከሐዋርያት የማይለዩ የት እንደ ሄዱ እንዴት እንደወደቁ አይታወቅም ። ከነርሱ ውስጥ ቍጥር ናቸው የሚባሉ ማርቆስና ሉቃስ ወንጌልን የጻፉ፣የተለየ ምልክት ያላቸው ስለሆነ ስለነርሱ በመጠኑ ይተረኩ.ቸዋል ። (በወንጌላቸው ላይ ያለውን ተመልከት) ።



እንግዲህ ወንጌልን ዳር እስከዳር ያዳረሱ የጌታ ሐዋርያት ለብከት ብቻ እይደለም ፡ እነዚህ ፸፪ አርድእትም በየሀገሩ እንደተበተኑና እንደሰበኩም የታወቀ ነው ።እንዲሁም በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት ጽተበተኑት ፰ሺህ ክርስቲያን ውስጥ አብዛኛው በየሄደበት አገር ሲሰብክ ተገኝቷል ፤ ለምሳሌ ዲያቆን ፊልጶስ በሰማርያ የሠራውን እናውቃለን ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ጀንደረባን እንዳጠመቀ ተረድተናል ። እንዲሁም ሁሉ ራቅ እያለ እየሄደ የሰበከ፣ያስተማረ፣ በዚያውም ያረፈ ሐዋርያ ይገኛል ።

ከዚህም ሁሉ ይልቅ ወዲያውኑ የሚያምኑት ሁሉ ሰባኪዎች እየሆኑ ከመነሣታቸው የተነሣ ከሀገራቸው ራቅ ብሎም በመሄድና በማስተማራቸው በትንሹ ጊዜ ጥንታዊ የነበረውን ሃይማኖት እየደመሰሰ ክርስትናው በሰፊው ይነገር ጀመር።እንዲያውም በሐሰት አምልኮት እየተመለኩ የነበሩት ሁሉ በክርስትናው ፊት ቦታ በማጣታቸው ጣዖት አምላኪዎች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አካል ሆኑ ።

በክርስቲያኖች እውነተኛ ምስክርነት፣እውነተኛም ትምህርት የሚመለከታቸው ዓለም ሁሉ የነርሱን ፍለጋ ለመከተል ወደደ ፤ ስለዚህ ከዕለት ወደ ዕለት ክርስቲያን እየበዛ፣ሃይማኖቱ እየጸና፤በሮማግዛት የሚያንጸባርቀው ሃይማኖት ክርስትናው ሆነ ።

## ምዕራፍ ፱ የሴቶች አገልግሎት በቤተክርስቲያን

የክርስትና ሃይማኖት በጎሣ በጾታ የማይወሰን በመሆኑ በተለይም ክርስቶስ ከተከታዮቹ አብዛኛ



www.ethiopianorthodox.org

ዎቹ ሴቶች በመሆናቸው ክርስቶስና የክርስትና ሃይማኖት እንደባለውለታ ሁኖ በሴቶች ይረዳ ጀመር።

በክርስቶስ ጊዜ በገንዘባቸው ፥ በጉልበታቸው ያገለግሉ የነበሩ ሴቶችን ወንጌላውያን ገልጠው ተናግረውላቸዋል (ማቴ.፳፯.፶፭ ፤ ማር.፭.፵—፵፩፤ሉቃ.፳፫.፳፯) ። እነዚህ ሴቶች በመስቀልም ጊዜ እንኳን ያልተለዩ ናቸው።እንዲሁም ከመቃብሩ ባለመለየት ሲመላለሱ፥ ከሐዋርያት ቀድመው ጌታን ያገኙና ለደቀመዛሙርቱም እንዲነግሩ የታዘዙ ናቸው (ማቴ.፳፰.፩—፲ ፤ማር ፲፮.፩—፰ሉቃ ፤ ፳፬፡፩—፲) ። የእነዚህ የቅዱሳት አንስት መጀመሪያዋ ቅድስት ማርያም ናት ፤ እርሷ በነፍስም በሥጋም ቅድስት ከመሆኗ የተነሣ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ለመውለድ በቃች፤ በዚህም የሴቶች ሁሉ መመኪያ፥መጀመሪያ ሆነች።በኋላም ከክርስቶስ ሳትለይ የቅዱሳት አንስት መሪ በመሆን ወጣች፥ወረደች፡ ልጅዋ ወደ ሰማይ እስከዐረገበት ዕለት ሳትለይ ሠርታለች ።

የሰማርያ ሕዝብ በክርስቶስ ለማመን ምክንያት የሆነችው የሰማርያ ሴት ናት፤የሠራሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ ብላ ጣርታ ያመጣች (ዮሐ፬.፳፱)።

በሐዋርያት ጊዜ ቤትዋን ለነርሱ መሰብሰቢያ ያደረገች፥ንብረቷን ለወንጌል ትምህርት ያበረከተች የማርቆስ እናት ማርያም ነበረች(የሐ.ሥ. ፲፪. ፲፪) ።

የአቂላ ሚስት ጵርስቅላ በብዙ ነገር ከጳውሎስ የማትለይ የነበረች ናት(የሐ.ሥራ.፲፰.፪፤ ፩ኛ ቆሮ.፩.፲፩) ። የክንክራኦስን ቤተ ክርስቲያን ታገለግል



የነበረች ፊቤን ብዙ አገልግሎትን ያበረከተች ናት። (ሮሜ ፲፯/፩)።እነዚህ ሁሉ ለወንጌል ትምህርትና ለበጎ አድራጎት ከወንዶች ሐዋርያት ባለመለየት የሠሩ ናቸው ። ሴቶች ልጆች በማስተማር፥ ትንቢት በመናገር የነበሩ ሥነ ሥርዓት ያላቸው እንደነበሩ በፊልጶስ ልጆች ልንረዳ እንችላለን (የሐ.ሥራ.፳፩.፱) ።

ይኸን ሁሉ የተረዳው ሐዋርያው ጳውሎስ ሴቶቹ አገልጋዮች ለመሾም ብትፈልግ (ዲያቆናዊት) ፷ ዓመት የሆናቸውን መሾም አለብህ ሲል ለጢሞቴዎስ ገልጦ ጽፏል (፩ኛ ጢሞ.፭.፱—፲፫)። ይኸም የሚያመለክተው ዛሬም ስለወንጌል ትምህርት ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሴቶች መሥራት የሚገባቸው መሆኑን ነው ።

የሐዋርያት ዘመን ስለክርስትና ይኸን የመሰለ መልክ ነበረው፤በሃይማኖት ፥ በጎሣ፥ በጾታ ልዩነት ሳይኖር ሁሉም ስለክርስቶስ ፍቅር ስለወንጌል ክብር እንዲያስብ ፥ እንዲናገር ፥ እንዲሠራ ያደርገው ነበር ።

## ምዕራፍ ፲ የክርስትናው በዓለም መስፋፋት ፤

በዚሁ በ፩ኛው መቶ ዓመት ክርስትናው በዓለም ለመዳረስ ለመስፋፋትም ቻለ ፤ ክርስቲያኑም ሕዝብ ከጊዜ ወደ ጊዜ በቊጥር በዝቶ ተገኘ ።

ምንም በያንዳንዱ ሀገር ስንት ሐዋርያት፥እነማን እንደ ሄዱ ግልጥ ሁኖ ባይታወቅም ከአውሮፓ ወደ ሚበልጠው ክፍል ከመካከለኛው ምሥራቅም እስከ ሕንድ እንዲሁም ከአፍሪካ እንደ ግብጽ፥ኢትዮጵያ ፥ ቱኒስያ ፥ ሊብያ ፥ ኖብያ ያሉትና እነዚህን የመሳሰሉት



www.ethiopianorthodox.org

አገሮች በዚሁ በ፩ኛው ምእት ዓመት ክርስትናው ለመግባት ወንጌል ለመስበክ ተችሏል ።

ይኸን ወንጌላዊ ሥራ በቀላሉ ለማዳረስ ያስቻሉ ልዩ ልዩ ምክንያቶች አሉ ፤ እነርሱም ፤

፩/ የሐዋርያትና የተከታዮቻቸው ቀራጥ አሠራር ነው ፤እነዚህም ሰዎች ከሥጋዊ አስተሳሰብየራቁ፣ በመንፈስ የጠለቁ በመሆናቸው ፣ ሳይፈሩ ሳያፍሩ በማስተማራቸው የሚያያቸው የሚሰማቸው ፣ ሁሉ በአድናቆት ትምህርታቸውን ለመቀበል ቻለ ።

፪/ የሚናገሩት እውነት ፣ የሚሠሩት በእውነት በመሆኑ በሐሰት የሚመለኩት ሁሉ በእውነት ስለተጋለጡ ሁሉም ወደ እውነት አዘነበለ ፤ የክርስትናውን እውነተኛነት አረጋገጠ ፤ ስለዚህ ሳያመነታ ከጣዖት አምልኮ ወደ እውነተኛው ሃይማኖት፣ከአረማዊነት ወደ ክርስትናው ለመግባት ቀና ሆነለት ።

፫/ <u>የቋንቋው አንድ መሆን ፣ በ</u>ዚያን ጊዜ ከሞላ ጎደል የሥልጣኔ ቋንቋ ሁኖ ይነገር የነበረው የአስተዳዳሪዎችም የሮማውያን የይፋ ቋንቋቸው ግሪክኛ በመሆኑ በአስተርጓሚ ፣ በመሪ ከማይረገው ውዝግብ ርቆ በቀጥታ ሁሉም በሚሰማው ቋንቋ ወንጌል በመነገሩ በቶሎ ተቀባይነትን ለማግኘት ችሏል ።

ከታላቂ እስክንድር አቸናፊነት የተነሣ ግሪኮች በሁሉ ስለተበተኑ ሁሉም ግሪክኛ ይናገር ነበር ፤ እንዲሁም የፍልስፍና ቋንቋ በመሆኑ ሁሉ ይቀበለው ነበርና ።



፬/ <u>የአስተዳደር አንድነት</u> ፤ በዚያን ጊዜ የታወቀውን ዓለም ይገዙ የነበር ሮማውያን ነበሩ ፤ ሥርዓታቸው ሕጋቸው አንድ በመሆኑ ሀገሩም ሁሉ በአንድ ገዥ በመገዛቱ ሐዋርያት ወደ ማንኛውም ሀገር ለመዘዋወር ችግር ስላልነበራቸው እንደልባቸው እየገቡ እየወጡ ማስተማር ችለዋል ፤ ስለዚህ ለትምህርታቸው ሰፊ ተቀባይነትን አገኙ ፤

፭/ <u>የአምልኮ ጣዖት ደካማነት</u> ፤ ከመሠረቱ ጀምሮ እምላክ የፈቀደው፣ በጽሑፍም ያስተላለፈው ሃይማኖት አይሁዳዊ ነበር ፤ እርሱ እውነተኛ ሁኖ ይስጥ ስለነበር በፍልስጥኤም ምድር ክርስትና ብዙ ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም ፤ በየቦታው የነበረው አምልኮ ጣዖት ግን መሠረት የሌለው ፤ በጽሑፍ የዋለ ሃይማኖታዊ አስረጅ ስለሌለው በቀላሉ የተገነባ ነበርና በቀላሉ ለመፍረስ ቻለ ።

ይኸ ሁሉ ተደምሮ ለወንጌል ትምህርት ምክንያት ሆነ ፤ ይሁን እንጂ ከዚህም ሁሉ ምክንያት ይልቅ የአምላክ ፈቃድ መሆኑ ነው ፤ ስለዚህ ወንዱም ፣ ሴቱም ፣ ትንሹም ትልቁም ሕይወቱን ለወንጌል ትምህርት በመስጠት ስለሠራ ክርስትናው በሁሉ ዘንድ ሊዳረስ እንደቻለ ልንረዳ ይገባናል ። በዚያን ጊዜ ስለ አዲሱ ሃይማኖት ማለትም ስለ ክርስትናው በየትኛውም ሸንጎ ውይይት ይደረግ ነበር ፤ በዚያም አጋጣሚ ሳይፈሩና ሳያፍሩ ስለ ክርስትናው ሃይማኖት የሚናገሩ የሚመሰክሩ ነበሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

ክርስትናው የሰው ልጅ የሆነው ሁሉ ሃይማኖት እንደሆነ በማመን ሁሉም ለመማር ፥ ለማስተማር ፥ ይረባረብ ጀመር ። ስለዚህ ሐዋርያት ባልደረሱበት አገር እንኳን ነጋዴዎች ፥ መንገድ ተጓዥዎች ወደ የደረሱበትአገር በተለይም ወደየትውልድ ሀገራቸው ሲገቡ ስለክርስትናው ሃይማኖት በመናገራቸው ሊጠይቃቸው የመጣውን ሰው ሁሉ እያሳመኑ ይሰዱ ነበር ።

የኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባ ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ ፥ የወንጌል ሰባኪ ሁኖ እንደኖረ በዚህም ምክንያት የቤተ መንግሥቱ አካባቢና ታላላቅ ባለሥልጣኖች ክርስትናውን ተቀብለው እንደነበር ይታመናል ። እንግዲህ ከመንገደኞች መካከል እንደዚህ ያለ አጋጣሚ በብዙ ቦታ እንደሚገኝ የታመነ ነው ።

እንዲሁም ፍሬምናጦስ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት የቻለው ተጓዡን አጎቱን ሜሮፓዊስን ተከትሎ ወጥቶ ነው ። ይኸም ፍሬምናጦስ ጳጳስ ከመሆኑ በፊት የክርስትናው አስተማሪ ሁኖ ቤተ ክርስቲያንን አቋቁሞ አምልኮቱን ይፈጽም እንደነበር የታወቀ ነው ።

ይኸን በመሰለ መልክ ለንግድ ፤ ለጨኸት (ይግባኝ) ለመንግሥትም ሥራ ሕዝብ ሁሉ ወደ ሮምና እርሷን ወደመሳሰሉ ታላላቅ ከተማዎች ይሄድ ይመለስ ስለነበር ፤ በተለይም በንግድ ምክንያት ከአንዱ ወደ ሌላው የሚሄደው ሕዝብ ሁሉ ስለ



ክርስትና እየሰማ ራሱም አምኖ ፥ ተጠምቆ ፡ እየተመለሰ ፥ እርሱም ተመልሶ እየሰበከ ፥ ባልታሰበ ግምት ክርስትናው በዓለም በቶሎ ሊደርስ ቻለ ።

ዛሬም የክርስትናው ነገር ለካህን ብቻ የሚተው ተግባር አይደለም ፤ አባትና እናት ልጆቻቸውን ፡ የቤት አሳዳሪዎች ፥ የቤት ሠራተኞቻቸውን ፥ የአንድ የግል ማኅበር ዓባላቱን መስበክ ፥ ማስተማር ፥ ስለክርስቶስና ስለቤተ ክርስቲያኑ መናገር ፥ መመስከር ግዴታ ይሆንበታል ።

እንዲሁም በየቤተ ክርስቲያኑ የሰበካ ጉባኤው እንዲጠናከር ፥ የሰንበት ትምህርት ቤት እንዲቋቋም ክርስቲያናዊ ድርጅት ሁሉ በትክክል እንዲሠራ ፥ ወጣት ሽማግሌ ፥ ወንድ ፥ ሴት ፥ ካህን የጨዋ ልጅ ሳይል ሁሉም የሚሠራበት ሃይማኖታዊ ግዴታው መሆኑን ሁሉም ሊረዳው ያሻል ።

ተፈጸመ ።



www.ethiopianorthodox.org